ማውጫ

ገጽ

መግቢያ

ክፍለ ትምህርት አንድ

1. እኛነታችን.....................................................................................1

1.1 ምግብ.......................................................................................1

1.2 እኛ ጤናማ ነን.............................................................................19

1.3 የግል ንጽህናችንን መጠበቅ .............................................................29

1.4 የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች ......................................................39

ክፍለ ትምህርት ሁለት

2. ህብረተሰባችን ..............................................................................46

2.1 የህብረተሰባችንን አባላት.................................................................46

2.2 በህብረተሰቡ ውስጥ መኖር .............................................................53

2.3 ህብረተሰባችን ኃይል ያስፈልገዋል .....................................................61

2.4 ምስሎችን ከሸክላ አፈር፣ ከፕላስቲክ ጭቃና ከወረቀት መስራት....................71

ክፍለ ትምህርት ሶስት

3. የአካባቢያችን ተፈጥሮ ሀብት..............................................................87

.......................................................................................................

3.1 የተፈጥሮ ክስተት ..........................................................................87

3.2 የተፈጥሮ ሀብት ..........................................................................104

3.3 በአካባቢያችን የሚገኙ እፅዋት ........................................................126

3.4 በአካባቢያችን የሚገኙ እንስሳት ......................................................145

ክፍለ ትምህርት አራት

**4.** ወረዳችን /ክፍለ ከተማችን/...........................................................163

**4.1** የወረዳችን አቅጣጫዎች ................................................................163

**4.2** የወረዳችን መሬት አቀማመጥ ........................................................168

**4.3** በወረዳችን የሚገኙ መስሪያ ቤቶች ....................................................173

**4.4** የወረዳው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ..................................................189

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ

ክፍለ ትምህርት አንድ

1. እኛነታችን..........1

1.1 ምግብ..........2

1.2 እኛ ጤናማ ነን..........10

1.3 የግል ንጽህናችንን መጠበቅ..........15

1.4 የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች..........21

ክፍለ ትምህርት ሁለት

2. ህብረተሰባችን..........24

2.1 የህብረተሰባችንን አባላት..........25

2.2 በህብረተሰቡ ውስጥ መኖር..........29

2.3 ህብረተሰባችን ኃይል ያስፈልገዋል..........32

2.4 ምስሎችን ከሸክላ አፈር፣ ከፕላስቲክ ጭቃና ከወረቀት መስራት..........35

ክፍለ ትምህርት ሶስት

4. የአካባቢያችን ተፈጥሮ ሀብት..........37

..........

3.1 የተፈጥሮ ክስተት..........38

3.2 የተፈጥሮ ሀብት..........45

3.3 በአካባቢያችን የሚገኙ እፅዋት..........51

3.4 በአካባቢያችን የሚገኙ እንስሳት..........57

ክፍለ ትምህርት አራት

**4.** ወረዳችን /ክፍለ ከተማችን/..........64

**4.1** የወረዳችን አቅጣጫዎች..........65

**4.2** የወረዳችን መሬት አቀማመጥ..........68

**4.3** በወረዳችን የሚገኙ መስሪያ ቤቶች..........70

**4.4** የወረዳው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች..........72

# መግቢያ

የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት በተማሪዎች አካባቢ የሚገኙ ማህበራዊ ተፈጥሮአዊ ገጽታዎችን በተሟላ ሁኔታ ለማወቅ፣ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ለመረዳትና የእነዚህን እውቀት ለሰው ልጅ ጥቅም ለማዋል የሚረዳ ትምህርት ነው። ይህ ትምህርት የህብረተሰብ ሣይንስ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ፣ የኑሮ ዘዴ፣ እርሻ፣ የእጅ ስራ፣ የአካባቢ ትምህርትና የጤና ትምህርትን እውቀት ክህሎት ልምድ፣ ችሎታ፣ ዝንባሌና አመለካከት በማዋሀድና አላስፈላጊ ድግግሞሽን በማስወገድ ለመማር ምቹ በሆነ ሁኔታ የተቀናጀ የትምህርት አይነት ነው። በዚህ መሠረት የ 2 ኛ ክፍል የአካባቢ ሣይንስ ያሉት አራት ክፍለ ትምህርቶች ከላይ በተጠቀሱት የትምህርት ዘርፎች ሊገለፁ የሚችሉ ይዘቶችን በተቀናጀና ለመማር ማስተማር በሚያመች መልኩ እንዲያካትቱ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

ይህ የ 2 ኛ ክፍል የአካባቢ ሣይንስ የመማሪያ መፅሐፍ ለደረጃው የተዘጋጀ ሲለበስ መነሻ ያደረገ ሲሆን በውስጡም የተጠቃለሉትን ይዘቶች፣ የተለያዩ ተግባራትና ክንዋኔዎች ተማሪዎች በሚገባ በመረዳትና በተናጠልም ሆነ በግል በመስራት የእውቀት አድማሳቸውን ለማስፋትና ከትምህርቱ ክህሎትና ዝንባሌ ለማዳበር የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

# ክፍለ ትምህርት አንድ

# 1. እኛነታችን

- በሰውና በሌሎች እንስሳት መካከል ያለው መመሳሰል ምንድነው□
- በሰውና በሌሎች እንስሳት መካከል ያለው ልዩነትስ ምንድነው□
- ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉ ሶስቱ መሠረታዊ ነገሮች ምን ምንድናቸው□

የሰው ልጅ እንደ ሌሎቹ እንስሳት ሁሉ የሚራመድ፣ የሚመገብ፣ የሚዋለድ፣ የሚተነፍስ፣ ወዘተ ባህሪ ያለው እንስሳ ነው። ሰው ከሌሎቹ እንስሳት የሚለየው በቋንቋው በመናገሩ፣ በማሰቡ፣ በማገናዘቡና ሥራውን መስራት በመቻሉ ነው። ሥራን ለመሥራት የሚያስችለውን ሀይልና ጉልበት የሚያገኘው ደግሞ ከሚመገባቸው ምግቦች ነው።

## 1.1 ምግብ

### ቁልፍ ቃላት

- ምግብ
- የተለምዶ ምግብ
- ፍጥረታት
- ይዘት
- ኳሿኳር
- የዓይን ማዝ
- ድድ
- ወርሃ
- ጮቅ
- ዕድገት
- አካል

- ምግብ ምንድነው□
- የምግብ ጥቅም ምን ምን እንደሆነ ግለፁ።

ምግብ ማለት ማንኛውም ሊበላና ሊጠጣ የሚችል ነገር ሆኖ ለሰውነታችን ዕድገት ጠቃሚ የሆነ፣ ሀይልና ሙቀት የሚሰጥ፣ ከተለያዩ በሽታዎች ሊከላከል የሚችል ንጥረ ነገር በውስጡ የያዘ ማለት ነው። ነገር ግን ሊባላና ሊጠጣ የሚችል ነገር ሁሉ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች ይሰጠናል ማለት አይደለም።

? ዘወትር ከምንጠጣው ነገር ውስጥ ምንም የምግብነት ይዘት የሌለው ነገር ምን እንደሆነ በክፍል ውስጥ በቡድን በመወያየት የተስማማችሁበትን ነጥብ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

### 1.1.1 የምግብ ጥቅም

- የምግብ ዓይነቶች በስንት ይከፈላሉ□
- ዓይነታቸውስ□
- የእያንዳንዱን የምግብ ክፍል ጥቅም ግለፁ።

ምግብ ለሰውነታችን

- ዕድገትና ጥንካሬ የሚሰጥ ሲጎዳም እንዲጠገን የሚረዳ ነገር ነው።
- ሀይልና ሙቀት የሚሰጥ፣ የተለያዩ ክፍሎች ሥራቸውን በተቀናጀ ሁኔታ እንዲሰሩና ከተለያዩ በሽታዎችም ራሱን እንዲከላከል የሚረዳ ነው።

የምግብ ዓይነቶች ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነሱም፡-

ሀ) አካል ገንቢና ጠጋኝ፣

ለ) ሀይልና ሙቀት ሰጪ፣

ሐ) በሽታን ተከላካይ ናቸው።

**ሀ)** አካል ገንቢና ጠጋኝ የሚባሉት ምግቦች


- ገንቢና ጠጋኝ ምግቦች የሚባሉት የምግብ ዓይነቶች የተኞቹ ናቸው
- አካል ገንቢና ጠጋኝ ምግቦችን በይበልጥ መመገብ የሚገባቸው የትኞቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው

ገንቢና ጠጋኝ ምግቦች የሚባሉት

ወተት፣ አይብ፣ አሣ፣ የዶሮ ሥጋ፣ እንቁላል፣ የበግ ሥጋ፣ አደንጓሬ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ሽንብራ፣ ምስር፣ ወዘተ ናቸው።

ገንቢና ጠጋኝ ምግቦችን ይበልጥ አዘውትረው መመገብ ያለባቸው ሕፃናትና አዛውንቶች ናቸው። የእነዚህ ምግቦች እጥረትም በተለይ የሕፃናትን እድገት ፍጥነት የሚቀንስና ኳሺኳር የሚባል በሽታ የሚያስከትል ነው።

? ሕፃናትና አዛውንቶች ገንቢና ጠጋኝ ምግቦችን ይበልጥ መመገብ ያለባቸው ለምንድነው



ሥዕል **1/1** ሰውነት ገንቢና ጠጋኝ ምግቦች


- በሥዕል 1/1 ውስጥ ከተጠቀሱት ገንቢና ጠጋኝ ምግቦች ውስጥ ከእንስሳት ክፍልና ከእፅዋት ክፍል የሆኑትን ለይታችሁ ጻፉ።

ለ) ሀይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች፣

- ሀይል ሰጪ ምግቦች በብዛት መመገብ ያለበት የህብረተሰብ ክፍል የትኛው እንደሆነ ከነ ምክንያቱ ግለፁ።
- እነዚህን ሀይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦችን ሁሉም ሰው መመገብ ያለበት በየትኛው ወቅት እንደሆነ ታውቃላችሁ□ ለምን□
- ሀይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች የሚባሉትስ ምንና ምን ናቸው□

የሰው ልጅ የየዕለት ህይወቱን ለመምራት፣ የተለያዩ ሥራዎችንና ተግባራትን ያከናውናል። እነዚህን ክንዋኔዎች ለመተግበርም የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች መንቀሳቀስ አለባቸው። የሰውነት


ክፍሎች እንቅስቃሴም አስፈላጊውን ሀይልና ጉልበት ማግኘት ይፈልጋል። የዚህም ሀይልና ጉልበት ምንጭ የምንመገበው ምግብ ነው።



ሥዕል **1/2** የሰውነት እንቅስቃሴዎች

ሀይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች የሚባሉትም፡-

ማር፣ ዘይት፣ ጮማ ሥጋ፣ ቅቤ፣ ዓሣ፣ ሙዝ፣ ኦቾሎኒ፣ እንሰት፣ ፓስታ፣ የስንዴ ዳቦ፣ ስኳር ድንች፣ ሸንኮራ አገዳ (ስኳር)፣ አቮካዶና የመሣሰሉት ናቸው።





ሥዕል **1/3** ሀይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች

ሐ/ በሽታን ተከላካይ ምግቦች

> - በአንዳንድ የምግብ ዓይነቶች እጥረት ሊከሰቱ የሚችሉ የበሽታ ዓይነቶች ምንድናቸው
>
> ለምሣሌ፡-
>
> - በአዋቂዎች
> - በሕፃናት
> - በሁለቱም በሽታን የሚከላከሉ የምግብ ዓይነቶች ምንና ምን ናቸው

የድድ መድማት፣ ኳሺኳር፣ ወርሃነት፣ እንቅርትና የመሣሰሉት ከምግብ እጥረት ከሚመጡ በሽታዎች ዋነኞቹ ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌሎች በምግብ እጥረት ሊመጡ የሚችሉ በሽታዎችን (ችግሮችን) ለመከላከል የሚረዱን የምግብ ዓይነቶችም፡- እንደ ቃሪያ፣ ካሮት፣ የአበሻ ጎመን፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ቲማቲምና የመሣሰሉት ናቸው።



ሥዕል **1/4** አንዳንድ በሽታ ተከላካይ ምግቦች

ከምንመገባቸው በሽታ ተከላካይ ምግቦች በተጨማሪ የጠዋት ፀሐይ ብርሃን በሕፃንነት ጊዜ ሊከሰት የሚችለውን የእግርና ጀርባ አጥንት ህመምን ይከላከላል። ይህም ማለት ሰውነት የፀሐይ ብርሃንን ካገኘ ለአጥንት ጥንካሬ አስፈላጊ የሆነ ንጥረ ነገር ለራሱ ማዘጋጀት ይችላል ማለት ነው።





ሥዕል 1/5 በፀሐይ ብርሃን እጥረት ምክንያት በሕፃናት ላይ ሊደርስ የሚችል የእግር አጥንት መጣመምና እንዲሁም የገንቢና ጠጋኝ ምግብ (ፕሮቲን ) እጥረት ችግር።

ምግብ የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር፣ ጤናማና ጠንካራ መሆን ይችል ዘንድ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው። ስለዚህ ሕፃናት ጠንካራ፣ ጤናማና የተስተካከለ ዕድገት እንዲኖራቸው እንደየዕድሜያቸው በዓይነትና መጠን ተመጣጣኝ የሆነ ምግብ ሊያገኙ ይገባል። ይህንን ምግብ ካላገኙ ግን፦

- ከዕድሜያቸው በታች የሆነ ዕድገት ይኖራቸዋል።
- ሰውነታቸው ቀስ በቀስ እየቀነሰና እየከሣ ይሄዳል።
- ሀይል ያጡና ደካማ፣ አቅመ ቢስና ልፍስፍስ ይሆናሉ።
- በቀላሉ ለበሽታ ተጋላጭ ይሆናሉ።
- በሚጫወቱበት ጊዜም ከጓደኞቻቸው እኩል ተሯሩጠው መጫወት ያቅታቸዋል። በዚህም ምክንያት ብስጩና ነጭናጫ ይሆናሉ።

### **1.1.2** በተለምዶ የምንመገባቸው ምግቦች

- በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሰዎች በተደጋጋሚ የሚመገቡት የምግብ ዓይነት ምንድነው□
- በአካባቢያችሁ ከምታገኙአቸው የምግብ ዓይነቶች መካከል በይበልጥ ለመመገብ የምትመርጡትን ምግብ ግለፁ።
- በየአካባቢያችሁ ተወዳጅና በህብረተሰቡም በአብዛኛው ተዘውትሮ የሚበላ ምግብ ምን እንደሆነ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

በተለያየ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች እንደየአካባቢያቸው የተለያየ የምግብ ዓይነትን አዘውትረው ይመገባሉ። በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች አዘውትረው የሚመገቡት የምግብ ዓይነት የተለምዶ ምግብ ይባላል።

### **1.1.3** የምግብ ምንጮች

በአከባቢያችሁ የምትመገቡአቸው ምግቦች ከምን ከምን እንደሚገኙ ግለፁ።

ሰው ምግቡን የሚያገኘው ከሁለት ዋና ዋና ምንጮች ነው። እነዚህም ምንጮች፡-

ሀ) እፅዋትና

ለ) እንስሣት ናቸው።

### ሀ**)** ከእፅዋት የሚገኙ ምግቦች

- በአከባቢያችሁ ከእፅዋት የሚገኙ ምግቦች ምን ምን ናቸው□
- ምግቦቹ በምን ዓይነት መልክ ተዘጋጅተው ለምግብነት እንደሚውሉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በዝርዝር አስረዱ።


ከ[illegible]ዋት የሚገኙ ምግቦች፡- እንደጎመን፣ ድንች፣ እንሰት፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ጤፍ፣ ስኳር ድ[illegible]፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ወዘተ ናቸው።

ሥዕል **1/6** ከእፅዋት የሚገኙ ምግቦች

**ለ)** ከእንስሣት የሚገኙ ምግቦች

- በአከባቢያችሁ ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች ምን ምንድናቸው□
- ከእንስሣት የሚገኙ ምግቦች በምን ዓይነት መልክ ተዘጋጅተው ለምግብነት እንደሚውሉ በዝርዝር ግለፁ።

የሰው ልጅ እንሰሣትንና እፅዋትን ከሚመገቡት ውስጥ ትልቁን ቦታ ይይዛል። ሰው ከእንስሳት የሚያገኛቸው የምግብ ዓይነቶችም እንደ እንቁላል፣ ወተት፣ ሥጋ፣ አሣ፣ አይብ፣ ቅቤ፣ ወዘተ ናቸው።




ሥዕል **1/7** ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች

## **1.1.4** የአመጋገብ ሥርዓት

- የአመጋገብ ሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው?
- በአከባቢያችሁ የሚኖሩ ሰዎች ምን ዓይነት የአመጋገብ ሥርዓት እንዳላቸው አስረዱ።
- የመመገቢያ ዕቃቸው ምን ምን እንደሆነ ለመምህራችሁ ግለፁ።

የሰው ልጅ አመጋገብ ራሱን የቻለ ሥርዓት አለው። ይህም የአመጋገብ ሥርዓት እንድየምግቡ ዓይነት፣ ባህል፣ የሥልጣኔ ደረጃ፣ የመመገቢያ ዕቃ፣ ወዘተ ሊለያይ ይችላል።

ለምሣሌ፡- የእንጀራ በወጥ አመጋገብ፣ የፓስታ አበላል፣ የገንፎ አበላል፣ እንዲሁም የሚቀርቡበት ዕቃዎች ጭምር ይለያያሉ።

ነገር ግን ምግብ በምንመገብበት ጊዜ ሊኖር የሚገባው የአመጋገብ ሥነ ሥርዓት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባል።

<u>እነሱም</u>፡-

ሀ) ከምግብ በፊት ማድረግ የሚገባን ሥነ ሥርዓት፣

ለ) ስንመገብ መከተል የሚገባን ሥነ ሥርዓት፣

ሐ) ከምግብ በኋላ ማድረግ የሚገባን ሥነ ሥርዓት ናቸው።

**ሀ)** ከምግብ በፊት ማድረግ የሚገባን ተግባር

- ከምግብ በፊት ማድረግ የሚገቡን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ በዝርዝር ግለፁ።
- ከምግብ በፊት ማድረግ የሚገቡንን ነገሮች ማከናወን ለምን ይጠቅማል?

ምግብ ከመብላታችን በፊት ማከናወን የሚገቡን ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡-

- እጃችንን በንፁህ ውሃና ሳሙና መታጠብ እንዲሁም አፋችንን መጉመጥመጥ፣
- የምንመገበውን ምግብ በንፁህ መመገቢያ ዕቃ አዘጋጅቶ ማቅረብ፣
- በምንመገብበት ጊዜ የሚያስፈልጉንን ነገሮች/ውሃ፣ ወተት፣ ለስላሳ፣ ወዘተ በቅድሚያ አዘጋጅቶ ማቅረብ፣
- ለመመገብ ምቹ በሆነ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ተረጋግቶ ቁጭ ብሎ መመገብ ናቸው።

**ለ.** በምንመገብበት ወቅት ማድረግ የሚገቡን ሥርዓቶች

- በምንመገብበት ጊዜ ማከናወን ያለብን ነገር ምንድነው?
- በምንመገብበት ጊዜ ማከናወን ያለብን ነገር ማድረጋችን ምን ጥቅም አለው?

በምግብ ወቅት ማድረግ ከሚገቡን ቅደመ ተከተሎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡-

- ምግቡ በሚገኝበት ቦታ ሆኖ በስርዓት ተቀምጦ መመገብ፣
- ስንመገብ ትኩረታችንን ወደ ምግቡ ማድረግ፣
- ምግብ ከጎረስን በኋላ አለማውራት፣ አፋችንንም ከፍተን አለማላመጥ፣
- ምግብን በአፋችን ልክ መጥነን መጉረስ፣
- በተለይ አንዳንድ የምግብ ዓይነቶችን ስንመገብ ጥንቃቄ ማድረግ፣

ለምሳሌ፡- የመብነን ባህሪ ያላቸውና ቅባት የበዛባቸው ምግቦች ትን ሊሉን ስለሚችሉ በጥንቃቄ መመገብ፣

- ከፍላጎት በላይም ሆነ በታች አለመመገብ፣
- ከምግብ በኋላ ፈሳሽ ነገር ወተት፣ ውሃ፣ ወዘተ መጠጣት ለምግብ ውህደት አስፈላጊ ስለሆነ መርሳት የለብንም።

## ሐ) ምግባችንን ከተመገብን በኋላ ማድረግ የሚገቡን ሥርዓቶች

- ምግብ ከተመገብን በኋላ ምን ማድረግ እንደሚገባን ለመምህራችሁ አስረዱ።
- ከተመገብን በኋላ ማድረግ የሚገባንን ሥርዓት ማከናወናችን ምን ጠቀሜታ እንዳለው ለመምህራችሁ ግለፁ።

ምግባችንን ከተመገብን በኋላ፡-

- እጃችንን በውሃና ሳሙና መታጠብ፣አፋችንን መጉመጥመጥና ጥርሳችንን በቡሩሽ ወይም በባህላዊ መፋቂያ መፋቅ፣
- የተመገብንበትን ዕቃ አጥቦ ማድረቅና በተገቢው ቦታ ማስቀመጥ፣
- የተወሰነ ጊዜ ዕረፍት ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።



ሥዕል **1/8** የአመጋገብ ሥርዓቶች

**1.1.4.1** ምግብን ተካፍሎ መመገብ

- ምግብን ተካፍሎ መመገብ ማለት ምን ማለት ነው?
- ምግብን ከጓደኞቻቸሁ ጋር አብራችሁ ተመግባችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነ አብሮ መመገብ ምን ዓይነት ስሜት እንዳለው ግለፁ።
- ምግብን ተከፍሎ አብሮ መመገብ ምን ዐይነት ስሜት የሚፈጥር ይመስላችኋል? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

ምግብን ተካፍሎ አብሮ መመገብ ከመልካም ማህበራዊ ግንኙነቶች አንዱና ትልቁ ሲሆን ሌሎችም ማህበራዊ ግንኙነቶች ለምሳሌ፤መግባባት፣ መከባበር፣ መረዳዳትና፣ መፋቀር፣ የበለጠ እንዲጎለብቱና እንዲዳብሩ ያደርጋል። ከፍያለ መፋቀርና መተማመንንም ይፈጥራል።



ሥዕል **1/9** አብሮ መመገብ

ሥዕሉን በመመልከት ምን እንደተገነዘባችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

(?) የማይፋቀርና የማይቀራረብ ሰው አብሮ የሚመገብ ይመስላችኋል?

የማይተማመኑ ጓደኞች አብሮ መመገብ ይችላሉ?

## መልመጃ 1.1

ሀ**)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ምግብ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው ።
2. ከምንበላቸውና ከምንጠጣቸው ነገሮች ጥቂቶቹ የምግብነት ይዘት የላቸውም።
3. ምግቦች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር በሁለት ይመደባሉ።
4. ከምግብ ጠቀሜታዎች አንዱ ሀይልና ሙቀት መስጠት ነው።
5. ገንቢና ጠጋኝ ምግቦችን መመገብ የሌለባቸው ጎልማሶች ናቸው።
6. አንዳንድ በሽታዎች ከምግብ እጥረት የሚመጡ ናቸው።
7. የቆሸሸ ልብስ የለበሰ ተማሪ ደስተኛ አይሆንም።
8. አንድ ተማሪ ልብሱ ብቻ ሣይሆን ሰውነቱና ፀጉሩ ጭምር ንፁህ መሆን አለበት።

መመሪያ ለ**)** ለሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ትክክለኛውን ቃል በባዶ ቦታዎቹ በመሙላት የተሟላ አድርጓቸው።

1. ዘወትር የምንመገባቸው ምግቦች ________________________________ይባላሉ።
2. እንደቃሪያ፣ ሎሚ፣ ብርቱካን፣ ቲማቲም፣ ያሉ ምግቦች የ______________ምድብ ናቸው ።
3. ምግብን ተካፍሎ መመገብ የ_______________________ምልክት ነው።
4. የ__________________ባሕሪይ ያላቸውና____________________ያለባቸው ምግቦች በጥንቃቄ ካልተበሉ ትን ሊሉ ይችላሉ።

መመሪያ ሐ**)** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ገንቢና ጠጋኝ ምግቦችን የያዘ ምድብ የትኛው ነው

   ሀ) ካሮት፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ብርቱካን

   ለ) አደንጓሬ፣ ባቄላ፣ አሣ፣ ወተት

   ሐ) ቅቤ፣ የስንዴ ዳቦ፣ የዶሮ ስጋ፣ አቮካዶ

   መ) ጮማ ስጋ፣ ቆጮ፣ ስኳርድንች፣ ባቄላ

2. ከሚከተሉት ውስጥ የምግብ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ሀይልና ሙቀት መስጠት

   ለ) ሰውነት ማክሳትና ማቀጨጭ

ሐ) በሽታን መከላከል

መ) ሰውነት ማፋፋትና መጠገን

3. በእጅ ንፅህና ጉድለት ሊከሰት የማይችል የጤና ችግር የሆነው?

ሀ) የዓይንማዝ ለ) የተስቦ በሽታ ሐ) የወስፋት በሽታ

መ) የኤድስ በሽታ

4. ከሚከተሉት ውስጥ ከእንስሳት የሚገኝ የምግብ ክፍል ያልሆነው?

ሀ) ዓሣ ለ) ቆጮ ሐ) እንቁላል መ) አይብ

5. ምግብን ተከፍሎ ስለ መመገብ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) መከባበርንና መረዳዳትን ከፍ ያደርጋል።

ለ) ያራርቃል ሐ) መተማመንን ይጨምራል

መ) ጓደኝነትን ያጠናክራል

6. ከሚከተሉት የአመጋገብ ሥርዓቶች መቅደም ያለበት የቱ ነው?

ሀ) ምግብን ቁጭ ብሎ ተረጋግቶ መመገብ፣

ለ) እጅን በንፁህ ውሃና ሣሙና መታጠብ፣

ሐ) የተመገብንበትን ዕቃ አጥቦ ማስቀመጥ፣

መ) ፈሣሽ ነገር መጠጣት፣

7. የአመጋገብ ሥርዓት በ _____________ ይመደባል።

ሀ) በሁለት ለ) በአራት

ሐ) በሦስት መ) በአምስት

8. ከሚከተሉት የአመጋገብ ሥርዓቶች ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ) እየበሉ ማውራት ለ) ከምግብ በፊት ውሃ መጠጣት

ሐ) መጥኖ መጉረስ መ) ሁሉም

9. በምንመገብበት ጊዜ ማድረግ ያለብን ________ ነው።

ሀ) እየሄድን መጉረስ ለ) ቆመን መብላት

ሐ) የጎረስነውን በውሃ መዋጥ

መ) ቁጭ ብለን ተረጋግተን መብላት

10. ከሚከተሉት ውስጥ ከምግብ በኋላ ሥነ ሥርዓት የሆነው ______ ነው።

ሀ) ምግብን ምቹ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ መመገብ

ለ) ትኩረታችንን ወደ ምግባችን ማድረግ

ሐ) ጥርሣችንን በቡሩሽ ወይም መፋቂያ ማፅዳት መ) ሁሉም

መመሪያ መ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በዝርዝር ግለፁ።

1. ሦስቱ የምግብ ጥቅሞች እነማን ናቸው?______________________________
__________________________________________________________

2. ሁለቱን የሰው ልጅ ምግብ ምንጮች ጥቀሱ። ___________________________
__________________________________________________________

3. ሦስቱን የአመጋገብ ሥርዓቶች ዘርዝሩ። _______________________________
__________________________________________________________

4. ከግል ንፅህና ጉድለት ሊመጡ ከሚችሉ የበሽታ ዓይነቶች ቢያንስ ሦስቱን ፃፉ።
__________________________________________________________
___________________________________

## 1.2 እኛ ጤናማ ነን!

ቁልፍ ቃላት

- ትኩሣት
- ትውከት
- መጫጫን
- ተስቦ
- አተት
- ማቅለሽለሽ
- ቁርጥማት

### 1.2.1 ጤና ምንድነው?

- እናንተ ሁሉጊዜ ደስተኞች ናችሁ?
- ከፍቷችሁስ ያውቃል?
- የምትከፉና የምትደሰቱት ምን ስትሆኑ ነው?

ሰው የዕለት ተዕለት ተግባሩን በተሟላ መልኩ ማከናወን የሚችለው የተሟላ ጤንነት ሲኖረው ብቻ ነው። ጤንነት ማለት ውስጣዊና ውጫዊ የአካል ደህንነት ማለት ሲሆን በጥቅሉ የአካልና ማህበረሰብ ደህንነት ማለት ነው።

? ውጫዊ የሰውነታችን ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

### 1.2.2 የጤናማነት ጥቅም

- ጤናማ መሆን ምን ጥቅም አለው?
- ጤናማ አለመሆንስ ምን ጉዳት አለው?

ጤናማ ሰው በእውቀቱና በጉልበቱ ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለህገሩ ጠቃሚ ሥራን ማከናወን ይችላል።

#### 1.2.2.1 ደስተኛ መሆንና አለመሆን


ደስተኛ መሆን

ጤናማ ሰዎች ደስተኞችና ጥሩ ስሜት የሚሰማቸው፣ ጠንካራና ፈጣኖች ሲሆኑ በማንኛውም የዕለት ተዕለት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ በንቃትና በብቃት ይሣተፋሉ።

ደስተኛ አለመሆን

ደስተኛ አለመሆን የጤና ማጣት አንዱ መገለጫው መንገድ ነው። በአጠቃላይ ሕመምተኛ ሰው፡-

- ጥሩ ስሜት አይሰማውም።
- ከጤናማ ሰው የበለጠ ጊዜውን በመኝታ ላይ ያሣልፋል።
- ደስተኛም አይደለም።



ሥዕል 1/10 ጤናማና ታሞ አልጋ ላይ የተኛ ሰው።

? ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?

ስዕሉን በደንብ ተመልከቱና በሰዎቹ ላይ የሚነበበውን ስሜት ለመግለፅ ሞክሩ።

### 1.2.2.2 ህመምተኞችንና አካል ጉዳተኞችን ማክበርና መተባበር

- አካል ጉዳተኛ ማለት ምን ማለት ነው?
- በአካል ጉዳተኛና በህመምተኛ ሰው መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ህመም በተለያዩ ምክንያቶች በውስጣዊም ሆነ ውጫዊ አካል ክፈል ላይ የሚደርስ ወይም ሊደርስ የሚችልና በአብዛኛው በህክምና ሊድን የሚችል ሲሆን አካል ጉዳተኝነት ግን በተፈጥሮ ወይም በአጋጣሚ በሰው ላይ የሚደርስ ወይም ሊደርስ የሚችል የአካል መጉደል ነው። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም አካል ጉዳተኞች ከህመምተኞች የሚለዩት አብዛኞቹ ሥራን መሥራት መቻላቸው ነው። ሁለቱም የህብረተሰብ ክፍሎች ሲያጋጥሙን ታዲያ ከልብ የመነጨ ፍቅር መስጠት አለብን። ከኛ የሚፈልጉት ትብብር ካለም አቅማችን የፈቀደውን ያህል መተባበር ይኖርብናል።

### 1.2.3 ጤናማና ህመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር

ቀደም ሲል እንዳየነው ጤናማና ህመምተኛ ሰዎች የየራሳቸው የሆነ መገለጫ ባህሪይ አላቸው። ይህንንም ሁኔታ ከሚከተለው ሠንጠረዥ ማየት እንችላለን።

| ተ.ቁ | ጤናማ ሰው | ሕመምተኛ ሰው |
|---|---|---|
| 1 | ደስተኛና ተጫዋች ነው። | - ዝምታን ያበዛል፣ አንገቱን ይደፋል። |
| 2 | ቀልጣፋና ፈጣን ነው። | - ብዙ ጊዜውን በመኝታ ማሣለፍ ይፈልጋል |
| 3 | ጥሩ ስሜት የሚሰማው ነው። | - ጥሩ ስሜት አይሰማውም |
| 4 | በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ይሣተፋል። | - በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ያለው ተሳትፎ ዝቅተኛ ይሆናል። |
| 5 | የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ይችላል። | - ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አያደርግም፣ ቢያደርግም የጤናማ ሰው እንቅስቃሴ ዓይነት አይደለም። ሥራን መሥራት ይሣነዋል። |

ሠንጠረዥ 1/1 የጤናማና ህመምተኛ ሰዎች ንፅፅር

#### 1.2.3.1 ህመምተኛን መርዳትና መንከባከብ

ህመምተኛነት የውጫዊ ወይም የውስጣዊ አካል ደህንነት መጓደል ነው። በመሆኑም ህመምተኛ ሰው ፍላጎቶቹን ሁሉ ማሟላት አይችልም። ስለዚህ ህመምተኛው ከኛ የሚፈልገውን መፈፀም አለብን። ይህ ሁኔታ በአንድ መልኩ ሰብአዊ ግዴታችን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ እርካታን ይሰጠናል።



ሥዕል 1/11 ጤናማ ሰው ለህመምተኛ ሰው እርዳታ ሲያደርግ።

ተግባራዊ ጥያቄ **1/1**

ሀ) ቢያንስ ሁለት ዓባላት ያሉበት ሁለት ቡድን መሥርቱና አንደኛው ቡድን የሚያስደስተውን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የማያስደስተውን ነገር መሠረት በማድረግ በድራማ ወይም በጭውውት መልክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።


ለ) ከመካከላችሁ ከቤተሰቡ(ቧ) አባላት መካከል ታሞ የነበረ እንዲጠይቁና ሕመምተኛው (ዋ) ከመታመሙ (ሟ) በፊት የነበረው (ራት) ባህሪይ ከታመመ (ች) በኋላ የታየው የባህሪ ለውጥ ምን እንደሆነ እንዲነግሯቸሁ ጓደኞቻችሁን ጠይቁ።

## **1.2.4** የህመም ምልክቶች

| |
|---|
| እንድ ሰው መታመሙን እንዴት ማወቅ እንደሚችል ግለፀ።<br><br>ለምሣሌ፡-<br><br>- የልብ በሽታ ሲይዘው፣<br>- ጉንፋን ሲይዘው፣<br>- የሣንባ በሽታ ሲይዘው፣ ወዘተ |

በሰውነታችን ውስጥ የጤና መጓደል ሲከሰት እንደ በሽታው ዓይነት የተለያዩ የህመም ምልክቶች መታየት ይጀምራሉ። እነዚህም የጤና መጓደል ምልክቶች

- ማቅለሽለሽ
- ከባድ የድካም ስሜት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- ትውከት
- የራስ ምታት
- ማንቀጥቀጥ
- ማሣከክ
- ትኩሣት (ከፍተኛ የሰውነት ሙቀት)
- የሆድ ቁርጠት
- ክብደት መቀነስ
- ከሌላው ጊዜ የተለየ ላብ
- ቁርጥማት
- ውጋት
- የመጫጫን ስሜት
- መነጫነጭ ወዘተ ናቸው።




ሥዕል **1/12** የበሽታ ምልክቶች

## መልመጃ 1.2

መመሪያ ሀ**)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ጤንነት ማለት የአካልና የማህበረሰብ ደህንነት ማለት ነው።
2. ጤናማነት ምንም ጥቅም የለውም።
3. ህመምተኞች ደስተኞች ናቸው።
4. ጤናማ ያልሆነ ሰው ጊዜን በመኝታ ማሳለፍ ይፈልጋል።
5. ህመምተኞችንና አካል ጉዳተኞችን መርዳት ሰብአዊ ግዴታችን ነው።

መመሪያ ለ**)** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት አንዱ የጤና ማጣት ምልክት ያልሆነው የቱ ነው

   ሀ) ሣቅና ጫወታ      ለ) መነጫነጭ

   ሐ) የምግብ ፍላጎት መቀነስ      መ) ማሣከክ

   ሠ) የሰውነት ሙቀት መጨመር

2. አካል ጉዳተኞች ከህመምተኞች የሚለዩበት መንገድ የቱ ነው

ሀ) ሥራን መሥራት ይችላሉ　　ለ) ሥራን መሥራት አይችሉም

ሐ) ሀ እና ለ　　መ) መልሱ አልተሰጠም

3. ከሚከተሉት የሰውነታችን ክፍሎች ውስጥ ውስጣዊ የአካል ክፍል የሆነው የትኛው ነው□

ሀ) ዓይን　　ለ) ጆሮ

ሐ) ጉበት　　መ) ጣት

### 1.2.5 የህመም ስሜቶች ሲሰሙን ምን ማድረግ ይገባናል□

- የህመም ስሜት ሲሰማችሁ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ።
- የህመም ስሜት ማለትስ ምን ማለት ነው□
- የህመም ስሜቶችስ ይለያያሉ ወይስ አንድ ናቸው□

አንዳንድ የበሽታ ዓይነቶች እጅግ በጣም አደገኞችና በፍጥነት ለአደጋ የሚዳርጉ ናቸው። ሌሎችም ቢሆኑ በሰውነት ውስጥ ከቆዩ ጉዳት ማድረሳቸው ስለማይቀር ወዲያው የጤና መታወክ ምልክቱ እንደተከሰተ በአቅራቢያችሁ ለሚገኝ መምህራችሁ ወይም የቤተሰብ አባል መንገር አለባችሁ። ወዲያውኑም ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ለጤና ባለሙያ ማሳወቅና አስፈላጊውን ህክምና ማግኘት ይገባችኋል።

ይህን አለማድረግ ግን በአንድ በኩል ስንፍና ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ራስን በህመም መጉዳትን እንደሚያስከትል ማወቅ ተገቢ ነው።

ተግባራዊ ጥያቄ **1.2**

ሀ) በቡድን በመሆን አንድ ሀኪም ከመካከላችሁ ምረጡና የቡድኑ አባላት የህመም ስሜቶችን በመከፋፈል ለተመረጠው ሀኪም እንዴት ማስረዳት እንደምትችሉ በድራማ መልክ አሳዩ።

ለ) አንድ ድንገተኛ አደጋ ቢፈጠር ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ በድራማ መልክ አሣዩ።

**መልመጃ 1.3**

በአከባቢችሁ ወደሚገኝ የጤና ጣቢያ ወይም የጤና ባለሙያ ዘንድ በመሄድ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተጠቀሱትን የበሽታ ምልክቶች በተሰጠው ምሣሌ መሠረት ሰርታችሁ (ሞልታችሁ) ለመምህራችሁ አሣዩ።

| ተ.ቁ | የበሽታው ዓይነት | በበሽተኛው ሊታዩ የሚችሉ ምልክቶች |
|---|---|---|
| 1 | ኤች አይ ቪ ኤድስ | |
| 2 | የተስቦ በሽታ | |
| 3 | የጉንፋን በሽታ | |
| 4 | የደም ማነስ በሽታ | |
| 5 | የወባ በሽታ | |
| 6 | የሳንባ ነቀርሳ (TB) በሽታ | ደም የተቀላቀለ አክታ፣ ትኩሣት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ክብደት መቀነስ |
| 7 | የአሜባ በሽታ | |
| 8 | የጨጓራ በሽታ | |
| 9 | የወስፋት በሽታ | |
| 10 | የአስም በሽታ | |
| 11 | የአተት በሽታ | ተከታታይ ተቅማጥና ትውከት |
| 12 | የደም ብዛት በሽታ | |

ሠንጠረዥ 1/2 የበሽታዎች አይነትና ምልቶቻቸው

## መልመጃ 1.4

**መመሪያ ሀ)** ትክክል የሆነውን መልስ ምረጡ።

1. ጤንነት ማለት

   ሀ) አካል ጉዳተኝነት ማለት ነው።

   ለ) የአካልና ማህበረሰብ ደህንነት ማለት ነው።

   ሐ) ውጫዊና ውስጣዊ የአካል ደህንነት ማለት ነው።

   መ) ለ እና ሐ መልስ ናቸው።

2. ከሚከተሉት የጤናማነት መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው

   ሀ) በንቃትና በብቃት ሥራን መሥራት ለ) ደስተኛ መሆን

   ሐ) ደስተኛ አለመሆን መ) ጥሩ ስሜትን ማሣየት

3. ከሚከተሉት የጤና መጓደል ምልክት ያልሆነው የቱ ነው

   ሀ) በጊዜ ተኝቶ በጥዋት መነሣት ለ) ከባድ የድካም ስሜት

   ሐ) የምግብ ፍላጎት መቀነስ መ) ማቅለሽለሽ

4. የህመም ስሜት እንደተሰማን ማድረግ ያለብን ነገር ምንድነው

   ሀ) ወደ ጤና ጣቢያ መሄድ ለ) ለቤተሰብ ማሣወቅ

   ሐ) ለመምህራችን መንገር መ) ዝም ብለን መተኛት

   ሠ) ከ "መ" በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው።

5. ክብደት መቀነስ፣ ደም የተቀላቀለ አክታ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ ከሚከተሉት የየትኛው በሽታ ምልክት ነው

   ሀ) የተስቦ በሽታ ለ) የአሜባ በሽታ

   ሐ) የሳምባ በሽታ መ) የደም ማነስ በሽታ

**መመሪያ ለ)** በ "ሀ" ረድፍ የተፃፉትን በ "ለ" ረድፍ ከተፃፉት ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ጤና | ሀ. የመንፈስ እርካታ |
| 2. የጤና መጓደል | ለ. የማህበረሰብ ደህንነት |
| 3. አካል ጉዳተኞችንና ህመምተኞን መንከባከብ | ሐ. የህመም ስሜት |
| | መ. ደስተኛ መሆን |
| 4. ህመምተኛነት | ሠ. ደስተኛ አለመሆን |
| 5. ጤናማነት | ረ. የህመም ምልክት |

መመሪያ ሐ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. የህመም ምልክቶች ሰውነት በበሽታ መጠቃቱን ጠቋሚዎች ናቸው።
2. ሁሉም የህመም ምልክቶች ተመሣሣይ ናቸው።
3. የሁሉም በሽታ መንስዔ አንድ ዓይነት ነገር ነው።
4. አደጋ ያጋጠመውን ሰው ስናገኝ ዝም ብለን ማለፍ ተገቢ አይደለም።

## 1.3 የግል ንፅህናችንን መጠበቅ

**ቁልፍ ቃላት**

- ፈንገስ
- ባክቴሪያ
- መቀንቀን
- ፕሮቶዟ
- ድቡልቡል የመሬት ትል

| |
|---|
| - የግል ንፅህና ማለት ምን ማለት ነው□<br>- የግል ንፅህናን መጠበቅ ምን ጥቅም አለው□<br>- የግል ንፅህናን መጠበቂያ መንገዶችስ ምንድናቸው□<br>- ምግብ የሚዘጋጅበት አካባቢ ንፁና ፅዱ መሆን የሚገባው ለምንድነው□ |

### 1.3.1 የግል ንፅህናችንን ለምን እንጠብቃለን□

የግል ንፅህና

የግል ንፅህና ማለት ሰው ለሰውነቱ እና ለሚለብሰው ልብስ የሚያደርገው ጥንቃቄ ማለት ነው። የግል ንፅህና መጓደል ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች የሚያጋልጥ ሲሆን ተፈጥሮአዊ ውበታችንንም ይቀንሳል። በመሆኑም የግል ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

የግል ንፅህና መጠበቂያ መንገዶች

- እጅን፣ እግርን፣ ፊትንና ፀጉርን መታጠብ፣
- የእጅና እግርን ጥፍርን መቁረጥ፣
- ገላን መታጠብ፣
- ጥርስን በሚገባ መፋቅ፣
- ልብስን ማጠብና መተኮስ ናቸው።

እጅን መታጠብ

በእጃችን ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ስለምንነካ ንፁህ ያለ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ስለዚህ ሁል ጊዜ ከምግብ በፊትና በኋላ፣ ከመፀዳጃ ቤት መልስና ምግብን ከማዘጋጀት በፊት እጅን በሣሙናና በውሃ መታጠብ አስፈላጊ ነው።

እግርን መታጠብ

እግራችንን የሚያጠቁ ብዙ የበሽታ መንስኤዎች (እንደ ፈንገስ፣ ባክቴሪያ) ያሉ አሉ። በተጨማሪም በጫማ ውስጥ የዋለ እግር በሙቀትና አቧራ አማካኝነት ሽታ ሊፈጥር ይችላል። ስለዚህ ሁል ጊዜ ማታ ማታ ከመተኛታችን በፊት እግራችንን መታጠብና ካልሲያችንንም ማጠብ እንደሚገባ መረሣት የለበትም።

ፀጉርን መታጠብ

ፀጉራችን ከውበታችን መገለጫዎች መካከል አንዱ ነው። ፀጉር በተፈጥሮው ቆሻሻ (አቧራ) የመሣብ ችሎታ ስላለው ቶሎ ይቆሽሻል። ሲቆሽሽ ደግሞ ያሣክከናል ውበቱንም ይቀንሣል ወይም ያጣል።

ስለዚህ ፀጉራችንን በየሦስት ቀኑ መታጠብና በየዕለቱ ማበጠር ሲያድግም ማሣጠር (ማስቆረጥ) አስፈላጊ ነው።

የእጅና የእግር ጥፍርን መቁረጥ

ጥፍሮቻችን ሲያድጉ ቆሻሻን አቅፎ የመያዝ ባህሪይ አላቸው። ይህ ቆሻሻ ደግሞ ጥሩ የበሽታ አምጪ ጀርሞች መኖሪያና መራቢያ ስለሆነ ጥፍሮቻችንን በአዲስ ምላጭ ወይም ሌላ ሰው በማይጠቀምበት የጥፍር መቁረጫ ቆርጦ ማሣጠር ከጤንነት መጠበቂያ መንገድ አንዱ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

የጥርስ ንፅህናን መጠበቅ

- የጥርስ አገልግሎት ወይም ጥቅም ምንድነው?
- ቢያንስ ሦስት የጥርስ ጥቅሞችን ጥቀሱ።

ጥርስ ብዙ አገልግሎት ያለው የሰውነት ክፍል ሲሆን ከነዚህም ጥቂቶቹ፡-

- ምግብን ለማኘክ (መፍጨት ወይም ለማድቀቅ) ያገለግላል።
- የተፈጨውን (የደቀቀውን) ምግብ ከምራቅ ጋር እንዲዋሃድ ያደርጋል።
- ንግግርን አስተካክሎ ለመናገር ይጠቅማል።

- ንፅህናው የተጠበቀ ጥርስ ውበትም ነው።

የጥርስ ንፅህና መጠበቂያ መንገዶች፣

- ምግብ ከመብላታችን በፊት በውሃ በመጉመጥመጥና ከምግብ በኋላ ደግሞ በሚገባ መፋቅና በውሃ መጉመጥመጥ (ማጠብ)።
- አልፎ አልፎ በጥርስ ማጽጃ ሣሙና ማጠብ የጥርስን ደህንነት ይጠብቃል። ጥሩ ያልሆነ የአፍ ጠረንንም ይቀንሣል።

## መልመጃ 1.5

**ሀ)** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከምግብ በፊት እጃችንን መታጠብ፡-

    ሀ) ለአመጋገብ ይመቻል　　　ለ) ምግብን ያጣፍጣል

    ሐ) ጤንነታችንን ለመጠበቅ ይጠቅማል　　　መ) ለ እና ሐ

2. ምግብን ስንመገብ ማውራት፡-

    ሀ) ትንታን ሊያስከትልብን ይችላል　　　ለ) ምግብ እንዳያንቀን ይረዳል

    ሐ) ቶሎ እንዳንጠግብ ያደርገናል　　　መ) ምግብ እንዳይጣፍጥ ያደርጋል

3. ከምግብ በኋላ እጃንንና አፋችንን መታጠብ፡-

    ሀ) አያስፈልግም

    ለ) የምግቡ ሽታ እንዲጠፋ ያደርጋል

    ሐ) የምግብ ትርፍራፊ በእጃችንና በአፋችን ውስጥ እንዳይቀር ያደርጋል።

    መ) ሁሉም ልክ ነው።

4. ሁልጊዜ ጥፍራችንን መቁረጥ፡-

    ሀ) እጃችንን ስንታጠብ ቆሻሻው ቶሎ እንዲለቅ ይረዳል።

    ለ) ለአመጋገብ አይመችም

    ሐ) የአመጋገብ ሥርዓታችን አይፈቅድም

    መ) መልሱ አልተሰጠም

መመሪያ ለ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. እየተንቀሣቀሱ መመገብ ጥሩ የአመጋገብ ሥርዓት ነው።
2. ምግብ በልተን እጃችንን አለመታጠብ ምንም ችግር የለውም።
3. ከምግብ በፊት እጅን መታጠብ አንዱ የጤንነት መጠበቂያ መንገድ ነው።
4. ከመመገባችን በፊት እጃችንን የምንታጠበው እጃችን ብዙ ነገር ስለሚነካ ነው።

ገላን መታጠብ

- ገላችንን ለምን እንታጠባለን
- እናንተ ገላችሁን በሣምንት ስንት ጊዜ ትታጠባላችሁ
- ከመታጠባችሁ በፊትና ከታጠባችሁ በኋላ ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ ግለፁ።

ሰውነታችን ሥራ ሥንሰራ፣ የተለያዩ እንቅስቀሴዎችን ስናደርግ፣ መንገድ ስንሄድ ወዘተ በውስጡ ከሚፈጠሩት ቆሻሻዎች የተወሰኑትን የሚያስወግደው በቆዳችን ላይ በሚገኙ ትናንሽ ቀዳዳዎች በኩል ነው። ይህንንም ቆሻሻ በየጊዜው ካልታጠብነው የሰውነታችን ጠረን (ሽታ) እንዲለወጥ ያደርጋል።

በሌላም በኩል ይህ ሁኔታ ሰውነታችንን እንዲቀነቅነን፣ እንዲያስከከን ወይም ምቾት እንድናጣ ያደርገናል። ስለዚህ በሣምንት አንድ ጊዜ ገላችንን መታጠብ ለጤንነታችን አስፈላጊ ነው።



*ሥዕል* **1/13** *የግል ንፅህና መጠበቂያ መንገዶች*

የልብስ ንፅህናን መጠበቅ

- የምንለብሰው ልብስ ከምን ከምን እንደሚሰራ ግለፁ።
- ልብስ ለምን ለምን እንደሚጠቅም በዝርዝር ግለፁ።

ልብስ ሰውነታችንን እንደየወቅቱ ሁኔታ ከብርድ፣ ከፀሐይና ከነፋስ ከመጠበቁም ሌላ ለሰውነታችን ውበት ይሰጣል። ልብሶቻችን በሁለት መንገድ ይቆሽሻሉ። አንደኛው ከውስጥ በኩል ከሰውነታችን በሚወገዱ ቆሻሻዎች ሲሆን፣ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከውጪ በኩል በሚመጡ አቧራማ ነገሮች በቀላሉ ቶሎ ቶሎ መቆሸሻቸው ነው።

የቆሸሹ ልብሶች ደግሞ ለተለያዩ እንደቅማልና ቁንጫ ላሉ ደም መጣጭና በሽታ አስተላላፊዎች ምቹ መኖሪያና መራቢያ ይሆናሉ ወይም ናቸው። በመሆኑም ልብሶቻችንን ቶሎ ቶሎ ካላጠብን ለተለያዩ በሽታዎች ልንጋለጥ እንችላለን።

ለምሣሌ፦ ቅማል የተስቦ በሽታን በማስተላለፍ ትታወቃለች። ስለዚህ ሁልጊዜ በየሣምንቱ ገላን ታጥቦ፣ የትምህርት ቤት ልብስን አጥቦ መጠቀም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።



ሥዕል **1/14** የልብስ ንፅህና መጠበቂያ መንገዶች

ከግል ንፅህናችን በተጨማሪ ምግቦቻችን የሚዘጋጁበት አካባቢ እንዲሁም የምነመገብበት ዕቃ ንፅህናው በሚገባ የተጠበቀ መሆን አለበት። በተጨማሪም የበሽታ መንስኤዎችና የበሽታ መንስኤ አስተላላፊዎች ለምሣሌ፦ ዝንብ የምግብ እቃ ያለበትና ምግብ በሚዘጋጅበት ቦታ መድረስ የለባቸውም።

#### **1.3.1.1** እኛ የግል ንፅህናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት ችግር ይፈጠርባቸዋል

- ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችሉ የበሽታ ዓይነቶችን ጥቀሱ።
- ከጠቀሳችሁት የበሽታ ዓይነቶች ውስጥ የግል ንጽህናን ካለመጠበቅ ሊመጡ የሚችሉት የትኞቹ እንደሆኑ ለይታችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ።

ከግል ንፅህና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች አብዛኛዎቹ በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፉ ናቸው። ስለዚህ እኛ ንፅህናችንን ካልጠበቅንና በዚህም ምክንያት በተለያዩ ከግል ንፅህና ጉድለት በሚመጡ በሽታዎች ከተጠቃን በሽታውን በቀላሉ ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ስለምንችል ከራሳችን አልፈን በሽታውን ወደ ሌሎች ሰዎችም ማስተላለፍ እንችላለን ማለት ነው።

ለምሣሌ፡- ጉንፋን ከግል ንፅህና ጉድለትና ከአካባቢ ንጽህና ጉድለት የሚመጣና በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን የዓይን ማዝ ደግሞ ከግል ንጽህና ጉድለት የሚመጣ በሽታና በዝንቦች አማካኝነት በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፍ በሽታ ነው።

### **1.3.2** የግል ንፅህናን ባለመጠበቅ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች

- ከግል ንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ በሽታዎች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ተናገሩ (ግለፁ)

የግል ንጽህናችንን መጠበቅ ከሚሰጠን እርካታና ምቾት በተጨማሪ ከግል ንጽህና እጥረት ከሚመጡ በሽታዎችም ይጠብቀናል። የግል ንጽህናችንን ካለመጠበቅ ከሚመጡ በሽታዎች መካከልም ጥቂቶቹ እንደ እከክ፣ የዓይን ማዝ (ትራኮማ)ና የወስፋት በሽታ ተጠቃሾች ናቸው። የእነዚህ በሽታዎች መንስኤና የህመም ምልክቶችም የሚከተሉተ ናቸው።

| የበሽታው ዓይነት | መንስኤው | የህመም ምልክቶች |
|---|---|---|
| የዓይን ማዝ | ፕሮቶዛ የተባለ ተህዋስ ክፍል | የዓይን መቅላት፣ መሞጭሞጭ የአይን ጠርዝ ነጭ ወፍራም ፈሳሽ ነገር ማውጣት፣ |

| | | |
|---|---|---|
| እከክ | የሰውነት ቆዳ መቆሸሽ | ማሣከክ፣ መቀንቀን ምቾት ማጣት |
| ወስፋት | የድቡልቡል መሬት ትል እንቁላል ከምግብና ውሃ ጋር መዋጥ | ማቅለሽለሽ፣ ግርጣት፣ አቅም ማነስ፣ የደም ማነስ፣ ወዘተ |

ሠንጠረዥ 1/3 የግል ንፅህናን ባለመጠበቅ ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎች መንስኤና ምልክቶቻቸው

### **1.3.3** ኤድስ በደም የሚተላለፍ በሽታ

- ኤድስ ምንድነው
- የኤድስ መንስኤስ ምንድነው
- የኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ናቸው
- የኤድስ መከላከያ መንገዶችን በዝርዝር ግለፁ።

የኤድስ በሽታ /ህመም/ የሰውነትን ራሱን ከበሽታ የመከላከል አቅም የሚያዳክም በሽታ ነው። መንስኤውም ኤች አይ ቪ የተባለ ተህዋስ /ቫይረስ/ ነው። ሰውነታችን በተፈጥሮ በሽታን የመከላከል ችሎታ አለው። ነገር ግን አንድ ሰው በኤድስ በሽታ ከተያዘ ሰውነቱ በሽታን የመከላከል አቅም ያጣል ወይም ይቀንስበታል። ስለዚህ በቀላሉ ለሌሎች በሽታዎች ይጋለጣል ማለት ነው።

የኤድስ በሽታ ምልክቶች

ከኤድስ በሽታ ምልክቶች ውስጥ ለምሣሌ፡- የክብደት መቀነስ፣ ተከታታይ ትኩሣት፣ የማያቋርጥ ሣል፣ ከፍተኛ የሆነ ተቅማጥ፣ የአፍ መቁሰልና የሳንባ በሽታ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የኤድስ መተላለፊያ መንገዶች

ኤድስ የሚተላለፈው በደም ንክኪ ነው።

የኤድስ በሽታ መከላከያ መንገዶች

| |
|---|
| የኤድስ በሽታ መከላከያዎች ምን ምን ናቸው? |

ከኤድስ በሽታ መከላከያ መንገዶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- ማንኛውንም የደም ንክኪ የሚፈጥር ነገር ማስወገድ፣
- ሌሎች በተጠቀሙበት ስለታም ነገር/ምላጭ/፣ ሹል ነገር/መርፌ/፣ የጥርስ መፋቂያ ቡሩሽ አለመጠቀም ናቸው።

**1.3.1.1.** አንድ ሰው በአደጋ ላይ የሚገኝ ከሆነ ለትላልቅ ሰዎች በአስቸኳይ መንገር አለባችሁ።

| |
|---|
| - አደጋ ምንድነው?<br>- አንድ ችግር ያጋጠመውን ሰው ብታገኙ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ። |

አደጋ አንድን ሰው ለችግር የሚዳርግ ነገር ማለት ነው። ስለዚህ አንድ ሰው በአደጋ ላይ መሆኑ ከታወቀ በአስቸኳይ ለሌሎች ሰዎች በማሳወቅ ግለሰቡ/ቧ/ ለችግሩ/ሯ/ መፍትሄ እንዲያገኝ/ድታገኝ/ ማድረግ ተገቢ ነው።

**1.4.** የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች

| |
|---|
| - ቀደም ሲል የተማራችሁትን የግል ንጽህና አጠባበቅ ዘዴዎችን ምን ያህል ታስታውሳላችሁ? የምታስታውሷቸውን በዝርዝር ለመምህራችሁ ግለፁ።<br>- ጥሩ የሆነ የአካባቢ ንጽህና ምን ጠቀሜታ አለው? |

ዋና ዋናዎቹ የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡-

- ሰውነትን መታጠብ፣

- ጥርስን ሁል ጊዜ ከምግብ በኋላ መፋቅና ማፅዳት፣
- የታጠቡ ልብሶችን መልበስ፣ የመኖሪያ ቤትን ጽዳት መጠበቅ፣
- የትምህርት ቤት ግቢንና የመማሪያ ክፍሎችን ንጽህና መጠበቅ፣
- ሁል ጊዜ መፀዳጃ ቤትን መጠቀም፣
- የሰውንና የእንስሳትን መኖሪያ መለየት፣
- ቆሻሻን የትም አለመጣልና ለቆሻሻ መጣያ የተዘጋጁ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች መጠቀም።በተጨማሪም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥየሚገኘውን ማንኛውንም ቆሻሻ በማንሳትና በተገቢ ቦታ በማስቀመጥ ጥሩ የመማሪያ አካባቢ እንዲሆን ማድረግ ናቸው።

### **1.4.1.** ለሌሎች ጤንነት ኃላፊነት እንዳለብን ማወቅ

| |
|---|
| ለሌሎች ሰዎች ጤንነት ኃላፊነት እንዳለብን እንዴት ማሳየት እንዳለብን በዝርዝር ግለፁ። |

ለሌሎች ሰዎች ጤንነት ኃላፊነት እንዳለብን ከምናሳይባቸው መንገዶች አንዱ በተላላፊ በሽታ መጠቃታችንን እንዳወቅን ወደ ለሎች እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ማድረግ ሲሆን ከነዚህ ጥንቃቄዎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- የሣንባ በሽታ፣ ኢንፉሌንዛ፣ ጉንፋን የመሳሰሉት በትንፋሽ የሚተላለፉ በሽታዎች ሲይዙን አክታን በየቦታው አለመትፋት፣ ንፍጣችንን የተናፈጥንበትን ሶፍት ወረቀት በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል ወይም የሰው እግር ወደ ማይደርስበት ቦታ ማድረግና የበላንበትንና የጠጣንበትን ዕቃ በሚገባ ሳይፀዳ ሌሎች እንዳይጠቀሙበት ማድረግ፣
- ሲያስነጥሰንና ሲያስለን አፋችንን አጠገባችን ካሉት ሰዎች ዞር ማድረግ፣ በእጃችን አፋችንን መከለል፣
- ሆዳችን ሲያመን መፀዳጃ ቤትን ብቻ መጠቀም፣
- መታመማችንን እንዳወቅን ቶሎ ብለን ወደ ሐኪም ቤት ሄደን መመርመርና መታከም ናቸው።

- ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን የጤና አጠባበቅ ዘዴን፦

1 ኛ. በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የሚገኙትን ማንኛውንም ቆሻሻ በማንሳትና በተገቢው ቦታ በማስቀመጥ ጥሩ የሆነ የመማሪያ አካባቢ ማድረግ አለባቸው።

2 ኛ. የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም በሥዕል ጥሩ የግል ንጽህና የሚያሳዩ ፖስተሮችን በመስራት ለሌሎች ትምህርቱን በማስተላለፍ ሁሉም የአካባቢውን ንጽህና እንዲጠብቅ ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ሥዕል **1/15** ተማሪዎች ት/ቤታቸውን ሲያፀዱ

*ሥዕል* **1/16** *ተማሪዎች የግል ንጽህናን የሚያሳዩ ፖስተሮችን በት/ቤትና አካባቢያቸው ሲለጥፉ*

## *መልመጃ* 1.6 /*የክለሳ ጥያቄዎች*/

*መመሪያ ሀ*) *ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።*

1. የሰውነትን ከበሽታ ራሱን የመከላከል አቅም ያደክማል።

   ሀ) የወባ በሽታ  ለ) የኤድስ በሽታ

   ሐ) የወስፋት በሽታ  መ) የጉንፋን በሽታ

2. ጥሩ የግል ጤና አጠባበቅ ልምድ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ቆሻሻን ጓሮ መድፋት  ለ) መፀዳጃ ቤትን መጠቀም

   ሐ) ጥፍርን መቁረጥ  መ) የመኖሪያ ቤትን ፅዳት መጠበቅ

3. በግል ንፅህና ጉድለት የሚከሰት በሽታ ነው።

   ሀ) አሜባ  ለ) ወስፋት

   ሐ) እከክ  መ) የዓይን ማዝ

   ሠ) ሁሉም

4. ከሚከተሉት ውስጥ የጥርስ ጥቅም ያልሆነው፡-

   ሀ) ንግግርን ማስተካከል  ለ) ምግብን መፍጨት

   ሐ) ውበት መስጠት  መ) ምግብን መዋጥ

5. ፊትን ባለመታጠብ የሚከሰት በሽታ ነው?

ሀ) አሜባ　　　　　　　　　　ለ) የዓይን ማዝ

ሐ) ኤድስ　　　　　　　　　　መ) ወስፋት

6. ከሚከተሉት የእንስሳት ተዋጽኦ ያልሆነ ምግብ የቱ ነው?

ሀ) አይብ　　　　　　　　　　ለ) ፍርፍር

ሐ) ወተት　　　　　　　　　　መ) እንቁላል

7. የሰውነታችንን ንጽህና ባለመጠበቅ የሚከሰት በሽታ የቱ ነው?

ሀ) የደም ማነስ በሽታ　　　　　　ለ) የጉንፋን በሽታ

ሐ) እከክ　　　　　　　　　　መ) ሁሉም

መመሪያ **ለ)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. በምግብ እጥረት የሚከሰት በሽታ በተህዋሲያን ከሚከሰት ይለያል።
2. አሜባ በተበከለ ምግብና ውሃ የሚከሰት በሽታ ነው።
3. የኤድስ በሽታ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት አይተላለፍም።
4. ሹልና ስለታም ነገሮች በጋራ በመጠቀም ኤች አይ ቪ አይተላለፍም።
5. የሳንባ በሽታ በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ አይደለም።
6. ካሮት ከበሽታ ተከላካይ ምግቦች አንዱ ነው።

**ሐ)** በ“ሀ” ረድፍ የተፃፉትን በ “ለ” ረድፍ ከተፃፉት ጋር አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. የወስፋት በሽታ መንስኤ ነው | ሀ) ኳሻኳር |
| 2. በገንቢ ምግብ እጥረት ምክንያት በህፃናት ላይ የሚከሰት በሽታ | ለ) ወረሃነት |
| | ሐ) ጮቅ |
| 3. የምግብነት ይዘት የሌለው ግን ምግብን ለማብላላት የሚያስፈልግ ፈሳሽ | መ) ውሃ |
| | ሠ) እንቅርት |

4. በፀሐይ ብርሃን እጥረት በሕፃናት ላይ የሚከሰት የእግር አጥንት መጉበጥ

5. በእግር ጣቶች መካከል በሚያድግ ፈንገስ የሚከሰት በሽታ

ረ) ድቡልቡል የመሬት ትል

ማጠቃለያ

- ምግብ ማለት ማንኛውም ሊበላና ሊጠጣ የሚችል ነገር ነው።
- ምግብ ለሰውነታችን እድገትና ጥንካሬ፣ ሀይልና ሙቀት ለመስጠትና እንዲሁም የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከል ይጠቅማል።
- የምግብ ዓይነቶች ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር በሦስት ዋናዋና ክፍሎች ይመደባሉ።

እነርሱም፡-

- ገንቢና ጠጋኝ
- ሀይልና ሙቀት ሰጪ እንዲሁም
- በሽታን ተከላካይ ናቸው።
- በአንድ አካባቢ ሚኖሩ ሰዎች አዘውትረው የሚመገቡት ምግብ የተለምዶ ምግብ ይባላል።
    - ሰው ምግቡን የሚያገኘው ከሁለት ዋናዋና ምንጮች ሲሆን እነርሱም፤
        - እፅዋትና
        - እንስሳት ናቸው።
- የሰው ልጅ የአመጋገብ ስርአት እንደ የምግቡ ዓይነት፣ ባህል፣ የሥልጣኔ ደረጃና የመመገቢያ ዕቃ ይለያያል።
- የአመጋገብ ሥርዓት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነርሱም፡-
- ከምግብ በፊት
- በምግብ ወቅትና
- ከምግብ በኋላ የአመጋገብ ስርዓቶች ናቸው።
- ምግብን ተካፍሎ መመገብ የመልካም ማህበራዊ ግንኙነት መሠረት ነው።
- ጤንነት ማለት የአካልና ማህበረሰብ ደህንነት ማለት ነው።
- ጤናማ መሆን ለራስና ለሀገር ጠቃሚ ሥራን ለመሥራት ይረዳል።
- ጤናማ ሰዎች ጥሩ ስሜት የሚሰማቸው፣ ደስተኞችና የዕለት ተዕለት ተግባራዊ ሥራ ላይ በንቃትና በብቃት የሚሳተፉ ናቸው።
- ህመምተኞች ጥሩ ስሜት የማይሰማቸውና ብዙ ጊዜያቸውን በመኝታ የሚያሳልፉ ናቸው።

- ህመምተኞችንና አካል ጉዳተኞችን ማክበርና መተባበር ተገቢና የሚያስመሰግን ነው።
- ህመምተኞችን መርዳትና መንከባከብ አስፈላጊ ነው።
- የህመም ምልክቶች የሰውነታችን ጤና መጓደል ምልክቶች ናቸው። እነዚህም የህመም ምልክቶች፡-
    - ማቅለሽለሽ
    - የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣
    - ትውከት፣
    - ማሣከክ፣
    - ትኩሣት፣
    - የሆድ ቁርጠት፣
    - ውጋት፣ ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው።
- የህመም ስሜቶች እንደተሰሙን ወደ ጤና ተቋም ሄዶ መታከም በሽታው ሥር ሰዶ ጉዳት እንዳያደርስ ያደርጋል።
- የግል ንጽህና ማለት ሰው ለሰውነቱ እና ለሚለብሰው ልብስ የሚያደርገው ጥንቃቄ ማለት ነው።
- የግል ንጽህና ጉድለት ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች ያጋልጣል፤ ውበትንም ይቀንሳል።
- ዋና ዋናዎቹ የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶችም፡-
    - እጅን ከምግብ በፊትና ከመጸዳጃ ቤት መልስ መታጠብ፣
    - የእጅንና የእግርን ጥፍር መቁረጥ፣
    - ገላን መታጠብ፣
    - ጥርስን ዘወትር ከምግብ በኋላ መፋቅና ማጽዳት፣
    - ልብስን ማጠብና መተኮስ ናቸው።
- ከግል ንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች በቀላሉ ወደ ሌሎች መተላለፍ የሚችሉ ናቸው።
- ከግል ንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ጥቂቶቹ፡-
    - እከክ
    - የዓይን ማዝ/ትራኮማ/

- ወስፋት ናቸው።

- ኤድስ በደም ንክኪ የሚተላለፍ የደም በሽታ ሲሆን መንስኤውም ኤች አይ ቪ የተባለ ቫይረስ ነው።
- ኤድስ ሰውነት ራሱን ከበሽታ የመከላከል አቅምን የሚያደክም በሽታ ነው።
- ለሌሎች ጤንነት ኃላፊነት እንዳለብን ከምናሳይባቸው መንገዶች ውስጥ ተላላፊ የሆነ በሽታ ሲይዘን ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ መጠንቀቅና ቶሎ ህክምና መውሰድ ነው።
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን የግል ንጽህና አጠባበቅ ዘዴን የት/ቤታቸውን ፅዳት በመጠበቅና ስለ ጥሩ የግል ንጽህና የሚያሳዩ የተለያዩ ፖስተሮችን በመስራት ትምህርቱን ለአካባቢው ህብረተሰብ ማስተላለፍ አለባቸው።

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

# 2. ህብረተሰባችን

## 2.1 የህብረተሰባችን አባላት

| |
|---|
| ህብረተሰብ ስንል ምን ማለት ነው□ ለመምህራችሁ ንገሩ። |

**ቁልፍ ቃላት**

- መንደር
- ህብረተሰብ
- መብት

ህብረተሰብ ማለት በአንድ አካባቢ ወይም መንደር የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። በአከባቢያችን የሚገኙ ሰዎች ወላጆቻችን፣ ዘመዶቻችን፣ ጎረቤቶቻችን፣ የመንደራችን ነዋሪዎች፣ እንዲሁም እኛን ጨምሮ የህብረተሰቡ አባላት ነን።

| |
|---|
| የህብረተሰባችንን አባላት እንዴት መመደብ እንችላለን□ ተወያዩበት። |

### 2.1.1 የህብረተሰብ አባላትን መመደብ


በአንድ አካባቢ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ ጎልማሳና ሽማግሌ እንዲሁም ሴቶችና ወንዶችን እናገኛለን። እነዚህ በጠቅላላ የህብረተሰባችን አባላት በመባል ይታወቃሉ።

? እድሜን መሠረት በማድረግ እናንተ በየትኛው የህብረተሰብ አባላት ውስጥ እንደምትመደቡ ለመምህራችሁ ግለፁ□

ፆታን መሠረት በማድረግ እራሳችሁን በየትኛው የህብረተሰብ ምድብ ትመድባላችሁ□

የህብረተሰባችንን አባላት በሚከተሉት መንገዶች መሠረት መመደብ እንችላለን። እነሱም፡-

1. እድሜን መሠረት በማድረግ፣
2. ፆታን መሠረት በማድረግ፣



ህፃን ወጣት ጎልማሳ ሽማግሌ

ሥዕል 2/1 የህብረተሰባችን አባላት

እድሜንና ፆታን መሠረት በማድረግ ህብረተሰብን መመደብ

የህብረተሰባችንን አባላት እድሜን መሠረት በማድረግ ህፃን፣ ወጣት፣ ጎልማሳና አዛውንት በማለት መመደብ እንችላለን።

? የቤተሰቦቻችሁን አባላት እድሜን መሠረት በማድረግ መድቡ። ከመደባችሁም በኋላ ምን ያህል የቤተሰብ አባላት በተለያዩ ምድቦች እንደተገኙ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

የቤተሰቦቻችሁን አባላትም ሆነ በአካባቢያችን የሚገኙ ሰዎችን እድሜን መሠረት በማድረግ መመደብ እንደምንችል ተመልክተናል። በተጨማሪም የህብረተሰባችን አባላት ፆታን መሠረት በማድረግ ወንድና ሴት በማለት መመደብ እንችላለን።

የቤተሰቦቻችሁን አባላት ፆታን መሠረት በማድረግ መድቡ። ከመደባችሁም በኋላ ምን ያህል ወንድና ሴት እንዳሉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

አንድ ሰው በእድሜው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ ወይም ምድብ ይተላለፋል። ይህም ሲባል፡-

- ህፃን የነበረው/ችው ወጣት ይሆናል/ትሆናለች።
- ወጣት የነበረው/ችው ጎልማሳ ይሆናል/ትሆናለች።
- ጎልማሳ የነበረው/ችው አዛውንት ይሆናል/ትሆናለች።

እያንዳንዱ የህበረተሰባችንም አባላት በህብረተሰባችን ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው።

ተማሪዎች፡- ህፃናት በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

ህፃን መሆን ያለውን ጠቀሜታና ጉዳት በማስመልከት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

### 2.1.2 ምን አይነት መብቶች አሉን?

- ህፃናት ለመኖር፣ እራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከልና ለእድገታቸው ምን ምን ያስፈልጋቸዋል? ወይም ሊሟሉላቸው ይገባል?
- በክፍል ውስጥ ከሚማሩ ጓደኞቻችሁ መካከል ስም የሌለው ተማሪ አለ?
- ለእያንዳንዳችሁ የግል መጠሪያ ስም ማን አወጣላችሁ? ስም ባይኖራችሁ ምን ይሰማችኋል?



ሥዕል 2/2 መብቶቻቸው የተጠበቀላቸው ህፃናት

ህፃናት ከተወለዱ በኋላ ስም ይወጣላቸዋል። ስሙ ለህፃናት መለያ ሆኖ ያገለግላል። ህፃናት ይህን የመጠሪያ ስም እንደ መለያ ሆኖ ስለሚያገለግላቸው ስም የማግኘት መብት አላቸው። ስማቸውን መጠሪያ በማድረግ ይጠቀሙበታል።

(?) ትምህርት ቤት ስትገቡ ትምህርት ቤቱ ስማችሁን ጠይቆ እንደመዘገባችሁ ታስታውሳላችሁ□ ክፍል መምጣታችሁ የሚታወቀው እንዴት ነው□ የተወለዳችሁበትን አካባቢ መጠሪያ ስም ታውቃላችሁ□ ምን ይባላል□

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ ሀገር ናት። በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ አካባቢ የተወለደ ህፃን ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ መኖርና ማደግ ይችላል። አንድ ህፃን የተወለደበት አገር ውስጥ የፈለገበት አካባቢ (ቦታ) ሄዶ የመኖርና የማደግ መብት አለው።

አንድ ህፃን እድሜው ለትምህርት ሲደርስ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ገብቶ የመማር ሙሉ መብቶች አሉት።

ልጆች ከአቅም በላይ የሆነ ከባድ ሥራ መሥራት የለባቸውም። ነገር ግን ከትምህርት ቤት መልስና በእረፍት ጊዜያቸው ማጥናት፣ ከዚያም በመላላክና ቀላል ሥራዎችን በመሥራት ወላጆቻቸውን ማገዝ አለባቸው።



ሥዕል 2/3 ህፃናት በጥናት ላይ

ህፃናት ለሰው ልጅ ለመኖር የሚስፈልጉትን መሠረታዊ ፍላጎቶች ማለትም ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የማግኘት መብት አሏቸው። ማንኛውም ህፃን ጤናው የተጠበቀና መልካም ዜጋ እንዲሆን ሊሟላለት ከሚገባቸው መብቶች አንዱና ዋነኛውም መሠረታዊ ፍላጎቱ ነው።

በአጠቃላይ ህፃናት የበርካታ መብቶች ባለቤቶች ናቸው። በተለይም ህፃናት የሚፈልጉት ነገሮች እንዲሟሉላቸው ያስፈልጋል። በተጨማሪም የህፃናት መብቶች፡-

- ፍቅርና እንክብካቤ ማግኘት፣
- የግል ስምና ዜግነት ማግኘት፣
- የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት፣
- የትምህርትና የጤና አገልግሎት ማግኘት፣

- በሠላምና በወንድማማችነት ማደግ፣
- በአደገኛ ሥራ ያለመሰማራት መብት፣
- ከዘር፣ ከቀለም፣ ከኃይማኖትና ከፆታ ልዩነቶች የመጠበቅ መብት አላቸው።

በመሆኑም ህፃናት ከላይ የተዘረዘሩ መብቶቻቸውን ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው። ይህንንም ጠንቅቀው ከተረዱ በኋላ መብቶቻቸው የሆኑ ነገሮችን ሲያጡ መጠየቅና ማግኘት ይገባቸዋል።

?

በትምህርት ቤት ውስጥ ምን አይነት እንክብካቤ እየተደረገላችሁ እንደሆነ በዝርዝር ለመምህራችሁ አስረዱ።

ሌሎች የህፃናት መብቶች የሆኑትን መምህራችሁን ጠይቁና ተወያዩ።

መብታችሁ ባይጠበቅላችሁ የት ሄዳችሁ መብታችሁን ማስከበር እንዳለባችሁ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

## መልመጃ 2.1

መመሪያ፡- ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በመረዳት ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ወይም ስህተት ከሆነ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. የህብረተሰባችንን አባላት እድሜን መሠረት በማድረግ መመደብ እንችላለን።
2. አንድ ሰው በእድሜው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ ወይም የእድሜ ምድብ ይተላለፋል።
3. ህፃናት የመጠሪያ ስም የማግኘት መብት አላቸው።
4. በአንድ አካባቢ የተወለዱ ህፃናት ወደ ሌላ አካባቢ ሄደው የማደግና የመኖር መብት አላቸው።
5. አንድ ህፃን ልጅ እድሜው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር መብት አለው።
6. ህፃናት ከባድ ሥራን መስራት ይችላሉ።
7. የህብረተሰባችንን አባላት እድሜን መሰረት በማድረግ ወንድና ሴት በማለት መመደብ እንችላለን።

ለ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ በባዶ ቦታዎቹ ላይ ሙሉ።

1. የህብረተሰባችንን አባላት እድሜን መሰረት በማድረግ ________________ ________፤ __________ና ______________ በማለት መመደብ እንችላለን።
2. የህፃናት መብት የምንላቸውን ዘርዝሩ።

   ሀ. ________________ መ. ________________

   ለ. ________________ ሠ. ________________

   ሐ. ________________ ረ. ________________

3. የህብረተሰብ አባላትን ፆታን መሠረት በማድረግ ____________ ና__________ __________ በማለት መመደብ እንችላለን።

### 2.2 በህብረተሰብ ውስጥ መኖር

<u>ቁልፍ ቃላት</u>

- ዕቅድ
- ፕሮግራም
- ክበብ
- ንድፍ
- ምስል

- በህብረተሰቡ ውስጥ መኖር ሲባል ምን ማለት ነው□
- በአካባቢያችሁ ምን ምን የመልካም ማህበራዊ ግንኙነቶችን አይታችሁ ታውቃላችሁ□

ሰው ከሰው ጋር ሲኖር በተለያዩ መንገዶች ይገናኛል። በስራ፣ በመኖሪያ ሰፈር፣ በገበያና በመሳሰሉት ሁኔታዎች በሰዎች መካከል ግንኙነቶች ይፈጠራሉ።

ከሰዎች ጋር መግባባት፣ መረዳዳት፣ መከባበር፣ መፋቀር፣ ወዘተ ሲኖረን በህብረተሰብ ውስጥ መልካም ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር እንችላለን።

ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር የሚኖራችሁ መልካም ግንኙነት ለምን ይጠቅማል□ ተወያዩበት።

### **2.2.1** የእለት እንቅስቃሴን ማቀድ

- በየዕለቱ ለምታከናውኗቸው ተግባራት እቅድ አላችሁ□

እቅድ ማለት አንድን ነገር በፕሮግራም መሠረት መሥራት ማለት ነው። አንድን ሥራ ለመሥራት መቼ እንደምንሰራ የጊዜ ዕቅድ ማውጣት አለብን። ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ በቁጠባ ለመጠቀም የገንዘብ ዕቅድ ያወጣሉ። ዕቅድ ሳይኖራቸው የሚሰሩ ከሆነ ጉልበታቸው ያልቅና ይደክማሉ። ስለዚህ አንድን ሥራ ከመስራታችን በፊት ዕቅድ ማውጣት ይጠበቅብናል።

ጊዜን በዕቅድ መጠቀም

ቀጥሎ የተመለከተውን የሁለት ጓደኛሞች ውይይት ተመልከቱ።

ዱካሞ፡- ጊዜሽን እንዴት ትጠቀሚያለሽ□

ደራሮ፡- ከጠዋት እስከ ማታ ያለውን ጊዜ የትምህርት፣ የጥናት፣ የጨዋታ፣ የቤት
ሥራ፣ የምግብ፣ የመኝታና የሥራ ጊዜ በማለት በዕቅድ አውጥቼ
እጠቀማለሁ።

ዱካሞ፡- እንዴት ነው እንዲህ አድርገሽ የከፋፈልሽው□

ደራሮ፡- የበለጠ እንዲገባህ የራሴን እቅድ ላሳይህ።

- ጧት ከ 12፡30 እስከ 1 ሰዓት ከእንቅልፌ ተነስቼ ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን እበላለሁ።
- ከ 1፡00 እስከ 2፡00 ሰዓት ከጓደኞ ጋር በመሆን ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።
- ከ 2፡00 እስከ 6፡15 ሰዓት ትምህርት ቤት እቆያለሁ።
- ከ 6፡30 እስከ 7፡30 ምሳዬን እበላለሁ።
- ከ 7፡30 እስከ 8፡00 ሰዓት እረፍት አደርጋለሁ።
- ከ 8፡00 እስከ 9፡00 ሰዓት ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ።
- ከ 9፡00 እስከ 10፡30 ሰዓት የቤት ሥራዬን እየሰራሁ አጠናለሁ።

ዱከሞ፡- እንዴት ጥሩ ነው□ አንቺ ለካ ጥሩ ውጤት የምታመጪው እንደዚህ እያጠናሽ ነው□ ለመሆኑ አንቺ ነሽ እንዴ እቅዱን ያወጣሽው□

ደራሮ፡- አባቴና እኔ ነን ያወጣነው።

ዱከሞ፡- በቃ እኔም ከአባቴ ወይም ከእናቴ ጋር ሆኜ የአንቺን አይነት እቅድ አወጣለሁ። እናም ጎበዝ እሆናለሁ።

ከላይ በተገለፀው ውይይት ምን ትምህርት አገኛችሁ□

እናንተስ ጊዜያችሁን እንዴት ለመጠቀም አቅዳችኋል□

ጊዜን በዕቅድ መጠቀም ማለት በአንድ ቀን ውስጥ የምናከናውናቸውን ተግባራት በሰዓት ከፋፍሎ ሥራ ላይ ማዋል ማለት ነው።

ጧት ከመኝታችሁ ተነስታችሁ ማታ እስከምትተኙ ድረስ ያለውን ክንውን በቅደም ተከተል ጻፉ። ማንኛውንም ነገር ለማከናወን በዕቅድ የተከፋፈለ ጊዜ ያስፈልጋችኋል።

ጎበዝ ተማሪዎች ጠዋት ተነስተው ከትምህርት ሰዓት ቀድመው ወደ ትምህርት ቤት ይደርሳሉ። የሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ሥርዓት አክብረው ትምህርታቸውን ይከታተላሉ። የትምህርት ሰዓትን አክብሮ እስከ መጨረሻ ክፍለ ጊዜ መማርም የጎበዝ ተማሪዎች ተግባር ነው።

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/1 ፡-** የጊዜ አጠቃቀም

ዓላማ፡- ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ አዘገጃጀት።

አስፈላጊ ነገሮች፡-

- የሥዕል ወረቀት
- እስክሪብቶ ወይም እርሳስ
- ማስመሪያ

አሰራር/ አዘገጃጀት

- በቀን ውስጥ ያለንን ጊዜያት ቀጥሎ እንደተቀመጠው መከፋፈል።
- በቀን ውስጥ የምናከናውናቸውን ተግባራት የመኝታ ጊዜ፣ የምግብ፣ የጥናት፣ የጫወታ፣ የቤት ሥራ፣ የሥራና የትምህርት ጊዜ በማለት መመደብ፣
- የመደብናቸውን ጊዜያት ተግባራትን ከታች እንደሚታየው ሰንጠረዥ በማዘጋጀት በሰንጠረዡ ውስጥ በማስገባት ክፍለ ጊዜንና ስራን ትይዩ ማስቀመጥ።

| የዕለቱ ቀናት | በእለቱ የሚከናወኑ ተግባራት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመኝታ ጊዜ | የምግብ ጊዜ | የጥናት ጊዜ | የጨዋታ ጊዜ | የቤት ሥራ ጊዜ | የሥራ ጊዜ |
| 1፡00 – 6፡30 | | | | | | |
| 6፡30 – 7፡00 | | | | | | |
| 7፡00 – 8፡30 | | | | | | |
| 8፡30 – 10፡30 | | | | | | |
| 10፡30– 12፡00 | | | | | | |
| 12፡00 – 2፡00 | | | | | | |
| 2፡00 – 4፡00 | | | | | | |

ሠንጠረዥ **2/1** የዕለት ተእለት ውሎእችንን ለማከናወን የሚጠቅም የጊዜ ሠሌዳን ማዘጋጀት

### **2.2.2** እራስን የማስተዳደር ክህሎት

- ለህፃናት ልብሣቸውን ወላጆቻቸው እንደሚያለብሷቸው ምግባቸውንም እንደሚያበሏቸው አስተውላችኋል□ እናንተም ህፃን በነበራችሁበት ወቅት ወላጆቻችሁ ያለብሷችሁ እንደነበር ታስታውሳላችሁ□
- አሁን ልብሳችሁን መልበስ ችላችኋል□
- ትምህርት ቤት በራሳችሁ መምጣት ችላችኋል ወይስ ሌሎች ሰዎች ያመጧችኋል□

ልጆች እያደጉ ሲሄዱ የሚፈልጉትን ነገር እራሳቸው መሥራት ይጀምራሉ። ጠዋት ተነስተው ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት ፊታቸውንና እጃቸውን ይታጠባሉ። ቁርስ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከበሉ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ።

ከትምህርት ቤት ስትመለሱ ደብተራችሁንና ብዕራችሁን ማን ይጠብቅላችኋል□

? በቤት ውስጥ ማንም ሳይረዳችሁ የምትሰሩትን ስራ በዝርዝር ጽፋችሁ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

### **2.2.3** በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ መሆን

በመንደራችሁ የሚኖሩ ሰዎች በጋራ በመሆን የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ□

እያንዳንዱ ሰው በግሉ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል። እነዚህ ግለሰቦች በጋራ በመሆን ቡድን ይመሰርታሉ። ይህ የተመሰረተው ቡድን የተለያየ ዓላማ ይኖረዋል። ይህ የቡድን አስተዋጽኦ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴ አካል ይሆናል።

በአከባቢያችን የሚገኙ ማህበረሰቦች የተለያዩ ተግባራትን በጋራ በመሆን ያከናውናሉ። <u>ለምሳሌ</u> በጋራ በመሆን እርሻ ያርሳሉ፣ መንገድ ይሰራሉ፣ የአከባቢን ጽዳት ይጠብቃሉ፣

ችግኞችን ይተክላሉ። ይህ አይነቱ ተግባር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

ተማሪዎች በህብረተሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል። ስለሆነም እናንተም እንደ ማህበረሰቡ አባላት የሣምንት ወይም የወር እቅድ በመንደፍ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ሚናችሁን ልታጎሉ ይገባል።



ሥዕል 2/4 የአካባቢ ህዝብ በጽዳትና በችግኝ ተከላ ዘመቻ ላይ

? እናንተ በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ፧

በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ክበባት እንደሚገኙ ዘርዝሩ።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተለያዩ ክበባት ይገኛሉ። ለምሳሌ የፀረ- ኤድስ ክበብ፣ የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ፣ የልጃገረዶች ክበብ፣ የስፖርት ክበብና የመሳሰሉት ይገኛሉ።

በክበባት ውስጥ መሳተፍ ለምን ይጠቅማል□ መምህራችሁን ጠይቁ።

ክበባቶች ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። የጎበዝ ተማሪ አንዱ መገለጫው በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚገኙ ክበባት ውስጥ መሳተፍ ነው። ክበባት ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች ከመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት በተጨማሪ በህብረተሰብ ውስጥ ስለሚኖራቸው ጉልህ ድርሻ ግንዛቤ እንዲይዙ ይረዳቸዋል።

እናንተ የየትኛው ክበብ አባላት ናቸሁ□ የክበቡስ አላማ ምን ምንድነው□ በትምህርት ቤታችሁ ክበባትን እንዴት ማቋቋም እንደሚቻል ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

እያንዳንዱ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ ሲኖር ቢያንስ የአንድ ክበብ አባል በመሆን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት። ምክንያቱም እውቀትና ክህሎት በክፍል ውስጥ በሚሰጥ ትምህርት ብቻ ሊገኝ አይችልምና።

## መልመጃ 2/2

መመሪያ፡- ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ሰው ከሰው ጋር ሲኖር በተለያዩ መንገዶች ይገናኛል።
2. ሰዎች ገንዘባቸውን በቁጠባ ለመጠቀም የገንዙብ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል።
3. ገንዙብን ስናገኝ ያየነውን ሁሉ ነገር መግዛት አስፈላጊ ነው።
4. ጊዜን በዕቅድ መምራት እጅግ ጠቃሚ ነው።
5. የጊዜ ዕቅድ የሌላቸው ተማሪዎች ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው።

መመሪያ፡- ለ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ።

1. ________________________________ማለት አንድን ነገር በፕሮግራም መሥራት ማለት ነው።
2. አንድን ሥራ ከመስራታችን በፊት የሚያስፈልገን የ____________________ ______________________ ዕቅድ ማውጣት ነው።
3. በአንድ ቀን ውስጥ የምናከናውናቸውን ተግባራት በሰዓት ከፋፍሎ ሥራ ላይ ማዋል የሚስችለን የ ______________________ ዕቅድ ሲኖረን ነው።

## **2.3** ህብረተሰባችን ኃይል ያስፈልገዋል


### **2.3.1** የኃይል ፍላጎት

| |
|---|
| በአከባቢያችሁ ለተለያዩ ተግባራት (ለምሳሌ ምግብ ለማብሰልና ለብርሃን) የምትጠቀሙበትን ኃይል ከየት እንደምታገኙ ለመምህራችሁ ንገሩ። |

በቤታችሁ ውስጥ ምግብ ለማብሰልና ቤታችንን ለማሞቅ ኃይል እንጠቀማለን። የረጠቡ ልብሶችን በፀሀይ ኃይል ማድረቅ እንችላለን። በአከባቢያችን የምናገኛቸው የእህል ወፍጮዎች፣ የቡና መፍጫዎች፣ ለመጓጓዣነት የምንጠቀምባቸው ተሽከርካሪ መኪናዎች፣ ሞተር ሳይክሎች፣ አውሮፕላኖችና መርከቦች ሲንቀሳቀሱና ሲሰሩ ኃይልን ይጠቀማሉ። እነዚህ ለመጓጓዣነት የምንጠቀምባቸው ከቤንዚንና ከናፍጣ ኃይላቸውን በማግኘት ይንቀሳቀሳሉ። አብዛኛው መሣሪያዎች የኤሌክትሪክን ኃይል ይጠቀማሉ።

### **2.3.2** የኃይል ምንጮች

| |
|---|
| የኃይል ምንጮች የምንላቸው ምን ምን ናቸው**?** |




ሥዕል **2/5** የኃይል ምንጮች

ኃይልን ከተለያዩ ምንጮች ልናገኝ እንችላለን። የኃይል ምንጮች የምንላቸው ማገዶ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ናፍጣ፣ ቤንዚን የፀሐይ ብርሃን፣ ነፋስ፣ ወራጅ ውሃና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ የኃይል ምንጮች በሶስት መመደብ እንችላለን። እነሱም

## ሀ) የሀገር ውስጥ የኃይል ምንጮች

የሀገር ውስጥ የኃይል ምንጮች የምንላቸው በቤታችን ውስጥ ምግብ ለማብሰል፣ ቤታችንን ለማሞቅና ለመሳሰሉት ተግባር የምንጠቀምባቸው ናቸው።

ለምሳሌ፡- ማገዶ (እንጨት)፣ የድንጋይ ከሰል

## ለ) የመጓጓዣ የኃይል ምንጮች

እነዚህ የኃይል ምንጮች በብዛት ለመጓጓዣነት የምንጠቀምባቸው መኪናዎች ሲንቀሳቀሱ እንዲሄዱ የሚረዳቸው የኃይል ምንጮች ናቸው።

ለምሳሌ፡- ናፍጣና ቤንዚን

## ሐ) የተፈጥሮ የኃይል ምንጮች

የተፈጥሮ የኃይል ምንጮች ከተፈጥሮ የምናገኛቸው ሆነው እኛ እንደአመቺነቱ በቀጥታ ወይም ወደ ሌላ መልክ ቀይረን የምንጠቀምባቸው የኃይል ምንጮች ናቸው።

ለምሳሌ፡- የፀሐይ ብርሃን፣ ነፋስ፣ ወራጅ ውሃ

ኤሌክትሪክ የኃይል ምንጭ አይደለም ነገር ግን ከተፈጥሮ የኃይል ምንጮች ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ ተቀይሮ የምናገኘው ኃይል ነው።

አንድን ሥራ ለመስራት ለሰው ልጅም ኃይል ያስፈልገዋል። ኃይልን ከተለያዩ ነገሮች እንደምናገኝ ተመልክተናል። ሰውነታችን ለመንቀሳቀስና ሥራ ለመሥራት ኃይል ያስፈልገዋል። ሰውነታችን ኃይል የሚያገኘው ከምንመገበው ምግብ ነው።

ተማሪዎች! ኃይል ለምን እንደሚጠቅመንና የኃይል ምንጮች የሚባሉትን በጥቅሉ ከላይ ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን የኃይል ምንጭ በዝርዝር እንመለከታለን።

## ማገዶ

| |
|---|
| በአከባቢያችሁ ሰዎች ምግባቸውን ለማብሰል ምን ይጠቀማሉ?<br>ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ። |

አብዛኛው በአገራችን የሚኖሩ ሰዎች ምግብ ለማብሰል የማገዶ እንጨት፣ ከሰል ወይም ኩበትን በማንደድ ይጠቀማሉ። የማገዶ እንጨትን ለመጠቀም ወይም ከሰል ለማዘጋጀት ዛፎች ይቆረጣሉ። በሚቆረጡ ዛፎች ምትክ ሌላ ዛፎችን መትከል አስፈላጊ ነው።

በፀሀይ ወቅት በግቢያችሁ ወይም በትምህርት ቤታችሁ ዛፍ ስር ተቀምጣችሁ ታውቃላችሁ? ምን ይሰማችኋል?

ዛፎች ተቆርጠው ካለቁ በአከባቢያችሁ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳቶች ምን ምንድናቸው?

ዛፎች ተቆርጠው እንዳያልቁ ምን ምን መደረግ እንዳለበት ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

የፀሐይ ብርሃን

ልብሳችሁን አጥባችሁ በፀሐይ ላይ ስታሰጡ ምን ይሆናል□

ፀሀይ የሙቀት ኃይል አላት። እርጥብ የሆነ ልብስ በፀሐይ ላይ ሲሰጣ ይደርቃል። ከፀሐይ የምናገኘው የሙቀት ኃይል እርጥበት ልብስን ከማድረቅ ሌላ በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጠናል።

ከፀሐይ የምናገኘው የሙቀት ኃይል እርጥብ ልብስን ከማድረቅ ሌላ ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ለመምህራችሁ ንገሩ።

የንፋስ ኃይል

| |
|---|
| ንፋስ በሚነፍስበት ወቅት በአከባቢያችሁ የሚገኙ ዛፎች ቅጠሎቻቸው ሲንቀሳቀሱ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? |

ንፋስ በሚነፍስበት ወቅት የለበሳችሁት ልብስ፣ በአካባቢ የሚገኙ ዛፎች፣ አቧራና የመሳሰሉ ቁሳቁሶች ይንቀሳቀሳሉ። እነዚህ ነገሮች እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርጓቸው ኃይል የንፋስ ኃይል በመባል ይታወቃል።

የንፋስ ኃይል እንዴት መጠቀም እንደምንችል ከመምህራችሁ ጠይቃችሁ ተረዱ።

የናፍጣና የቤንዚን ኃይል

መኪና ለመንቀሳቀስ ኃይል ያስፈልገዋል። መኪና ቤንዚን ወይም ናፍጣ ከጨረሰ ይቆማል። ናፍጣ ወይም ቤንዚን ተጨምሮበት ሲነዳ መንቀሳቀስና መሄድ ይጀምራል።

በቤት ውስጥ ናፍጣና ቤንዚንን ለምን እንደምንጠቀም ወላጆቻችሁን ጠይቁና በተረዳችሁበት ነጥብ ላይ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ ።
በምሽት ጊዜ በቤታችሁ ውስጥ ለብርሃን የምታበሩት ምንድ ነው?

በአንዳንድ ቤቶች ውስጥ የኤሌክትሪክ መብራት ይጠቀሙ ይሆናል። በሌሎች ደግሞ ኩራዝ፣ ፋኖስ ወይም ማሾ ይበራል።

ኩራዝ፣ ፋኖስና ማሾ እንዴት ብርሃን ሊሰጡ ይችላሉ?

? የኤሌክትሪክ መብራት አምፑል ብርሃን እንዴት እንደሚሰጥ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ተወያዩበት።

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/2** የነዳጅ ኃይል

ዓላማ፡- ናፍጣ ኃይል እንዳለው መፈተሽ።

አስፈላጊ ቁሳቁሶች

- ሁለት ኩራዞች
- የኩራዝ ክር
- ናፍጣ
- ክብሪት

አሠራር

- በሁለቱም ኩራዞች ውስጥ ክር መጨመር።
- አንደኛው ኩራዝ ውስጥ ናፍጣ በመጨመር በደንብ መክደን።
- ሁለተኛው ኩራዝ ውስጥ ናፍጣ ሳይጨምሩ በደንብ ከድኖ ማዘጋጀት።
- የሁለቱን ኩራዞች ክሮች ክብሪት በመጫር ማያያዝ።



ሥዕል **2/6** በናፍጣ ኃይል ኩራዝ ሲበራ

ስለዚህ ናፍጣ ብርሃን ሊሰጥ የሚችል ኃይል አለው።

ተግባራዊ ክንዋኔ 2/3 የባትሪ ድንጋይ ኃይል


ዓላማ፡- የባትሪ ድንጋይ ኃይል እንዳለው መፈተሽ።

አስፈላጊ ቁሳቁሶች

- አንድ የባትሪ አይን
- ግማሽ ሜትር የኤሌክትሪክ ገመድ
- አንድ አገልግሎት የሚሰጥ የባትሪ ገመድ

አሠራር

- ሁለቱን የኤሌክትሪክ ገመድ ጫፎች መላጥና ሽቦዎችን በአንድ በመጠምዘዝ ማዘጋጀት።
- ከታች በስዕሉ እንደተመለከተው የአንደኛውን ሽቦ ጫፍ በባትሪ ዓይን መጠምጠም።
- የባትሪውን ዓይን በባትሪ ድንጋይ እናት ማስቀመጥ።
- ከታች በስዕል በተመለከተው መሠረት ሌላኛውን የሽቦውን ጫፍ በሌላኛው የባትሪ ግርጌ ጋር አገናኝቶ መያዝ።



ሥዕል **2/7** የባትሪ ድንጋይ ጉልበት

የተግባር ጥያቄ

1. የባትሪው ዓይን በሽቦ ስትጠመጥሙት ብርሃን ሰጠ ?
2. የባትሪ ዓይን ከባትሪ ድንጋይ ጋር ስታገናኙት ለምን ብርሃን ሊሰጥ ቻለ?

ስለዚህ የባትሪ ድንጋይ ብርሃን ሊሰጥ የሚያስችል ኃይል አለው።

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/4** የፀሐይ ጉልበት


ዓላማ፡- የፀሐይ ጉልበት ኃይል እንዳለው መፈተሽ።

አስፈላጊ ቁሳቁሶች

- ጎድጓዳ ሳህን
- አንድ ኩባያ ውሃ

አሠራር

- ውሃውን በጎድጓዳ ሳህን ውስጥ መጨመር።
- ውሃ የያዘውን ሳህን ውጪ የፀሐይ ኃይል ባለበት ሥፍራ ለጥቂት ሰዓት አስቀምጦ መጠበቅ።



ሥዕል 2/8 የፀሐይ ኃይል

የተግባር ጥያቄ፡-

1. ውሃው ምን ሆነ
2. ውሃው እንዲሞቅ ያደረገው ምንድነው
3. ብዙ ሰዓት ብትቆዩ ውሃው ምን የሚሆን ይመስላችኋል

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/5** የፀሐይ ኃይል


ዓላማ፡- ፀሐይ የሙቀት ኃይል እንዳላት መፈተሽ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች

- ስስ ወረቀት
- የእጅ ሌንስ

አሠራር

- የፀሐይ ብርሃን ባለበት ቦታ በመሆን ወረቀቱን ከታች ሌንሱን ከላይ በኩል በአስር ሣንቲ ሜትር ከፍታ በስዕሉ እንደሚታየው አድርጎ ለተወሰነ ጊዜ መጠበቅ።



ሥዕል 2/9 በፀሀይ ብርሃን ወረቀትን ማቃጠል

የተግባር ጥያቄዎች፡-

? 1. ወረቀቱ ምን ሆነ

2. ወረቀቱ እንዲቃጠል ወይም እንዲሞቅ ያደረገው ምንድነው

## መልመጃ 2/3

መመሪያ ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. የረጠቡ ልብሶችን በፀሐይ ኃይል ማድረቅ ይቻላል።
2. ለመጓጓዣነት የምንጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች ማገዶን እንደ ኃይል ምንጫቸው ይጠቀሙበታል።
3. ኤሌክትሪክ የኃይል ምንጭ ነው።
4. አብዛኛው በአገራችን የሚኖሩ ሰዎች ማገዶን፣ ከሰልንና ኩበትን እንደ ኃይል ምንጭ ይጠቀማሉ።
5. መኪና ለመንቀሳቀስ ኃይል ያስፈልገዋል።

መመሪያ ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደንብ ከተረዳችሁ በኋላ ትክክለኛውን

መልስ በመምረጥ መልስ ስጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የኃይል ምንጭ ያልሆነው የትኛው ነው

ሀ. ማገዶ ለ. ወራጅ ውሃ

ሐ. የድንጋይ ከሰል መ. መኪና

2. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ኃይል ምንጭ ያልሆነውን ለዩ።

ሀ. ኤሌክትሪክ ለ. የፀሐይ ብርሃን

ሐ. ነፋስ መ. ወራጅ ውሃ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የሀገር ውስጥ የኃይል ምንጭ የምንለው የቱ ነው

ሀ. እንጨት ለ. ከሰል

ሐ. ኩበት መ. ሁሉም መልስ ነው

4. ለመጓጓዣነት የምንጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች የኃይል ምንጭ የትኛው ነው፧

ሀ. ነፋስ

ለ. ወራጅ ውሃ

ሐ. ቤንዚን

መ. መልሱ አልተሰጠም

5. ህብረተሰባችን ኃይል ለምን ያስፈልገዋል፧

ሀ. ምግቡን ለማብሰል

ለ. ለመጓጓዣነት

ሐ. የታጠበ ልብስን ለማድረቅ

መ. ሁሉም መልስ ነው

## 2.4 ምስሎችን ከሸክላ አፈር ከፕላስቲክ ጭቃና ከወረቀት መስራት

### 2.4.1 የንድፍ ስራ


- ሳጥን መሳል ትችላላችሁ□
- በርና መስኮት መሳል ትችላላችሁ□
- ጎጆ ቤት እንዴት እንደሚሳል ታውቃላችሁ□

አንድ ዕቃ ከመሥራታችን በፊት ዕቃውን ወይም ቁሱን የሚመስል ወረቀት ላይ ይሳላል። ይህ በወረቀት ላይ የሚሳለው ስዕል መሰል ሥራ ንድፍ ይባላል።

የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ንድፍ ለማሳየት መስመሮችን መጠቀም ይቻላል። መስመሮቹን በተለያዩ አቅጣጫዎች በመሥራትና በመገጣጠም የቅርፆቹ ንድፍ ይሰራል።

? እርሳስ በመጠቀም በወረቀት ላይ ቀጥታ መስመር ማስመር ትችላላችሁ□

በወረቀት ላይ አግድምና ቁልቁል ቀጥታ መስመሮችን ለማስመር ሞክሩ።




ሥዕል 2/10 የተለያዩ ዓይነት መስመሮች

? ከላይ በሥዕሉ ወደጎን፣ ወደታች (ቁልቁል)፣ በሰያፍና ክብ የተሰመሩ መስመሮችን የሚመስሉትን በመስራት ከጓደኞቻችሁ ጋር አስተያዩ።

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/6** - ቀጥታ መስመር ያለማስመሪያና በማስመሪያ መስራት

ዓላማ፡- መስመሮችን የማስመር ብቃት መለካት።

የሚያስፈልጉ ዕቃዎች፡-

- የተቀረፀ እርሳስ
- አንድ የስዕል ወረቀት
- ማስመሪያ

አሠራር

- እርሳስ ብቻ በመጠቀም በእጃችሁ ቀጥታ መስመር ወደታችና በሰያፍ አስምሩ፣
- በመቀጠል ማስመሪያ በመጠቀም ወደጎን፣ ወደታችና በሰያፍ ቀጥታ መስመር አስምሩ።

የተግባር ጥያቄ

- ያለ ማስመሪያ ያሰመራችሁትን መስመር ለምን ተጣመመ□
- ማስመሪያ ሳትጠቀሙ ቀጥ ያለ መስመር ማስመር እስከምትችሉ ደጋግማችሁ ሞክሩ።

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/7** - ጎነ ሶስት


ዓላማ፡- ቀጥተኛ መስመሮችን በመገጣጠም ጎነ ሶስት መስራት ማስቻል።

የሚያስፈልጉ ዕቃዎች፡-


- የተቀረፀ እርሳስ
- አንድ የስዕል ወረቀት
- ማስመሪያ

አሠራር


- አንድ ቀጥታ መስመር በሰያፍ ማስመር /ከግራ ወደ ቀኝ ከፍ እያለ የሚሄድ/



- ከመስመሩ አናት ጋር በማገናኘት ሌላ ቀጥታ መስመር በሰያፍ መስመር /ከመሃል አናት በስተቀኝ ወደ ታች የሚወርድ/




- ሁለቱን ሰያፍ የተሠመሩ መስመሮችን አንድ ቀጥታ አግድም መስመር በማስመር ማገናኘት፣




የተግባር ጥያቄ

- ስንት ጎን ያለው ቅርፅ ሰራችሁ□
- ማስመሪያ በመጠቀም ከላይ የሰራችሁበት መንገድ ተከትላችሁ ተመሳሳይ ቅርጽ ሥሩ።
- በማስመሪያና ያለ ማስመሪያ ከሰራችሁት ቅርጽ መካከል በቀጥታ መስመር የተሰራው የትኛው እንደሆኑ አወዳድሩ።

ተግባራዊ ክንዋኔ **2/8 -** ጎነ አራት

ዓላማ፡- ቀጥተኛ መስመሮችን በመገጣጠም ጎነ አራትን መሥራት ማስቻል።

የሚያስፈልጉ ዕቃዎች፡-

- የተቀረፀ እርሳስ
- አንድ የስዕል ወረቀት
- ማስመሪያ

አሠራር

- እርሳስ ብቻ በመጠቀም በእጃችሁ ቀጥታ መስመር ወደታችና በሰያፉ አስምሩ፣


ሀ

- በመቀጠል ማስመሪያ በመጠቀም ወደጎን፣ ወደታችና በሰያፍ ቀጥታ መስመር አስምሩ።


ሀ

ለ

- ሁለቱን ቀጥታ መስመሮች በአንድ በኩል ወደታች ቀጥታ መስመር አስምራችሁ አገናኙ።




- በመጨረሻም ያልተገናኘውን ጎን ወደታች ቀጥታ መስመር በማስመር አገናኙ።




ተግባራዊ ጥያቄ፡- ስንት ጎን ያለው ቅርጽ ሰራችሁ□

## 2.4.2 ማስጌጥ

- ጌጣጌጦችን መስራት ትችላላችሁ□
- ማስጌጫዎችን እንዴት መስራት እንችላለን□

ጌጣጌጦችን ወይንም ማስጌጫዎችን ለመስራት በመጀመሪያ ደረጃ መስራት የፈለግነውን ጌጥ ንድፍ በወረቀት ላይ ማስመቀጥ /መሳል/ ያስፈልጋል። ከዚያም በኋላ ማስጌጫዎችን በንድፉችን መሰረት የተለያዩ ክፍሎች መቁረጥ ወይም ማጣጠፍ አለብን።

ጌጣጌጦች ከተለያዩ ነገሮች መስራት ይቻላል። ለምሳሌ ከወረቀት፣ ከሸክላ አፈር ወይም ከአመድና ከፕላስቲክ መስራት እንችላለን።

በወረቀት ጌጣጌጦችን መስራት

- ከወረቀት የሚሰሩ ነገሮችን ስም ዘርዝሩ□
- ከወረቀት የምንሰራቸው ነገሮች ለምን ይጠቅሙናል□
- ከወረቀት የተለያዩ ነገሮችን ለመስራት ምን ምን ያስፈልጋል□





ሥዕል 2/11 ከወረቀት ለሚሰሩ ነገሮች ማከናወኛ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

ለወረቀት ሥራ መቀስ፣ እርሳስ፣ ማስመሪያ፣ ወረቀት፣ ኮላ (ማጣበቂያ)፣ መርፌ፣ ክር /ለማያያዣ/፣ ገመድ /ለማንጠልጠል/ እና እንጨት ያስፈልጋል።

ወረቀት ለመፃፊያ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በተለያየ መልኩ እየተቆረጠና እየተጣጠፈ የተለያዩ ጌጣጌጦችን፣ ፖስታዎችን፣ የደስታ መግለጫ ካርዶችን፣ የቀን መቁጠሪያ የመሳሰሉትን ለመስራት ያገለግላል።

ወረቀትን ለመቁረጥ በጠረጴዛ ላይ ዘርግተን በመጀመሪያ መቁረጥ የምንፈልገው ቦታ ላይ በማስመሪያ እና በእርሳስ በመጠቀም ማስመር አለብን። ልክ በመስመሩ ትክክል በመቀስ በመቁረጥ የምንፈልገውን ቅርጽ እናገኛለን። ወረቀት ስንቆርጥ ሁሉጊዜ መቀስ እንጂ ምላጭ መጠቀም የለብንም። ምክንያቱም ምላጭ ሊቆርጠን ስለሚችል ነው። በተለይም አዲስ ካልሆነ እስከ ሞት የሚደርስ አደጋ ስለሚስከትል ነው።

ደጋግመን በማስመርና በመቁረጥ ተግባር ልምምድ ካደረግን አስተካክለን ማስመርና መቁረጥ እንችላለን።




ሥዕል 2/12 የፖስታ አሰራር ቅደም ተከተል


የወላንዶ አሠራር

1. አንድ ረዥምና ሌላው አጠር ያለ ሁለት ቀጫጭንና ቀላል እንጨቶችን ወስዶ በመስቀል ቅርጽ ማሠር።


2. ቀጭን ሲባጎ በእንጨቶቹ ዙሪያ ማሰር።




3. ፐላስቲክ ወይም ስስና ጠንካራ ወረቀት ከሲባጎው ተረፍ አድርጎ በመቋጠር ትርፉን ፐላስቲክ ወይም ወረቀት አጥፎ በማጣበቂያ ማያያዝ።



4. በረጅም እንጨት ላይ ክር ማሰር።



5. በክሩ /ሲባጎ ላይ ክር ቋጥሮ መያዣ መስራትና እንዲሁም በሌላ ክር ትናንሽ ወረቀቶችን ቀጣጥሎ ከታችኛው ጫፍ ጋር በማሰር ጅራት መሰል ነገር መስራት።

## መልመጃ 2/4

መመሪያ ሀ**)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. የፖስታ አሰራርን መልመድ ከወጪ ያድናል።
2. የተለያዩ የወረቀት ጌጣጌጦች ቤትን ያስውባሉ።
3. በምላጭ መጠቀም ምንም ጉዳት የለውም።
4. በማስመሪያ ማስመርና በመቀስ መቁረጥ ልምምድ ያስፈልገዋል።
5. የወረቀትን ሥራ መለማመድ እጃችንን ያፍታታልናል።

የሸክላ ሥራ


| |
|---|
| በቤታችሁ ውስጥ የሚገኙትን ለመመገቢያነትና ለመጠጫነት የምንገለገልባቸው ቁሳቁሶች ከምን ከምን የተሰሩ ይመስላችኋል□ ከእነዚህ ቁሳቁሶች ውስጥ አንዳንዶቹ ከአፈር እንደተሰሩ ታውቃላችሁን□ |

ሰዎች በቤት ውስጥ ለተለያዩ ተግባሮች የሚጠቀሙባቸው አብዛኞቹ ቁሳቁሶች ከአፈር የተሰሩ ናቸው። ለምሳሌ፡- ሲኒ፣ ብርጭቆ፣ ጡብ፣ ጀበና፣ ገንቦ፣ እንስራ፣ ጋንና የመሳሰሉት የተሰሩት ከአፈር ነው።

እነዚህንና ሌሎች የተለያየ አገልግሎት ያላቸው ቁሳቁሶችን ለመስራት የሚያገለግለን የአፈር አይነት ምን የሸክላ አፈር በመባል ይታወቃል።

? የሸክላ አፈር ምን አይነት አፈር ነው□

የሸክላ አፈር የሚባለው መልኩ ጠቆር ያለና እጅግ በጣም ደቃቅ እና ከፍተኛ ውኃን የመያዝ ችሎታ ያለው የአፈር አይነት ነው። የሸክላ አፈር እጅግ ከፍተኛ ጥቅም ያለው የአፈር አይነት ነው።





ሥዕል 2/13 ከሸክላ አፈር የሚሰሩ ቁሳቁሶች

የሸክላ አፈርን ለሸክላ ሥራ ማዘጋጀት

የሸክላ አፈር ሲዘጋጅ በመጀመሪያ አፈሩ የሚገኝበትን ቦታ በመለየት አፈሩን ቆፍሮ የሸክላው ቁሳቁስ ወደሚሰራበት አካባቢ መውሰድ ነው።

የተቆፈረው አፈር ወደሚፈለግበት ቦታ ከደረሰ በኋላ ደረቅ ቦታ ላይ በመዘረር በፀሃይ አማካኝነት በደንብ እንዲደርቅ ማድረግ ነው። በመቀጠልም በአፈሩ ውስጥ ባዕድ ነገሮችን ለቅሞ ማውጣት ነው። ይህ ከሆነ በኋላ የደረቀውን አፈር በደንብ እስኪልም ድረስ መውቀጥ ወይም መፍጨት አስፈላጊ ነው።



ሥዕል 2/14 የሸክላ አፈር ሲወቀጥ

አፈሩ በደንብ ተወግጦ ወይም ተፈጭቶ ከላመ በኋላ በጠቅጣቃ የሸበ ወንፊት በመጠቀም መንፋት። ከዚያ በኋላ የላመውን ወይም የደቀቀውን አፈር ካልደቀቀው በመለየት ከወንፊቱ

የላላውን አፈር እንደገና መላልሶ በመውቀጥ ወይም በመፍጨት እንዲደቅ በማድረግ ከላመው ጋር ማቀላለቀል።




ሥዕል **2/15** የሸክላ አፈርን በወንፊት ማጣራት

በወንፊት ተጣርቶ የተዘጋጀውን የሸክላ አፈር በሰፊ እቃ ውስጥ በማድረግ ማቡካት ያስፈልጋል። አፈሩንም በደንብ አድርገን በውኃ በማሸት እስኪለጠጥ ድረስ ማሸት ያስፈልጋል።

የቦካው አፈር ደግሞ በሚከተሉት መንገዶች ለስራ ይዘጋጃል። ይኸውም በመጀመሪያ የቦካውን ጭቃ በጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ በተደጋጋሚ በመጣል እንደ ፕላስቲክ ጭቃ እስኪሳብ

ማሸት። በመቀጠልም ድቡልቡል በሆነ እንጨት እየዳመጡ መጠፍጠፍ። በመጨረሻም በስንጥር እንጨት ወይም በቦንዳ እየቆራረጡ ለሥራ አመቺ እንዲሆን ማድቦልቦልና ማዘጋጀት።



ሥዕል **2/16** ጭቃው እየጠፈጠፉ ማዘጋጀት

በቤታችን ውስጥ የሚገኙ ከሸክላ የተሰሩ ቁሳቁሶች በሁለት መንገድ ሊዘጋጁ ይችላሉ። እነዚህ፡-

1 ኛ. የሸክላ አፈር ጭቃን በመጠቅለል መስራት

2 ኛ. የሸክላ አፈር ጭቃን በመጠፍጠፍ መስራት

የሸክላ አፈር ጭቃን በመጠቅለል የሚሰሩ ቁሳቁሶች

ክፍት የሆነ ቅርጽ ያላቸው ቁሳቁሶችን ለመስራት ጭቃውን ማድቦልቦል፣ መጠቅለልና በልኩ በልኩ መቆራረጥ ከዚያም አንዱን በአንዱ ላይ በመደራረብ ውስጡን ክፍት በማድረግ መስራት። በዚህም መልኩ ሲኒ፣ እንስራ፣ ገንቦ፣ ድስትና የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች ማዘጋጀት ይቻላል።



ሥዕል 2/17 የሸክላ ጭቃውን እየጠቀለሉ መስራት

የሸክላ አፈር ጭቃን በመጠፍጠፍ የሚሰሩ ቁሳቁሶች

የሸክላ አፈር ጭቃን በመጠፍጠፍ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንችላለን። ድፍን የሆኑ ቅርጽ ያላቸው ቁሳቁሶችን ለመስራት ጭቃውን መጠፍጠፍና በልኩ በልኩ በመቆራረጥ መስራት እንችላለን። በዚህም መልኩ ጡብ፣ የቡና ረከቦት፣ የሸክላ ምጣድንና የመሳሰሉትን መስራት ይቻላል።

የሸክላ ቁሳቁሶችን ማስጌጥ

| የሸክላ ዕቃን እንዴት ማስጌጥ እንችላለን |
| --- |


የሸክላ ቁሳቁሶች ተሰርተው መጠጥ ካሉ በኋላ በላያቸው ላይ የተለያዩ ጌጣጌጦችን ማውጣት እንችላለን። ጌጣጌጡን በቁሱ ላይ ከመሥራታችን በፊት ለመሥራት የፈለግነውን ጌጥ በወረቀት ላይ መንደፍ ያስፈልጋል።

በሸክላው ዕቃ ላይ ጌጡን ሾል ባለ እንጨት ወይም ስንጥር ነገር እየቧጠጡ መሥራት ይቻላል። ጌጣጌጡ ሲወጣ የተቧጠጠውን የዕቃውን አካል ማስተካከል ያስፈልጋል።



ሥዕል 2/18 የሸክላ ዕቃን ማስጌጥ

? በቡድን በቡድን በመሆን በአከባቢያችሁ የሸክላ አፈርን በማፈላለግ ጀበና፣ ኩባያ፣ ድስትና የቡና ረከቦት በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ።




ሥዕል 2/19 ከሸክላ አፈር ኩባያ የመሥራት ቅደም ተከተል

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## 3. የአካባቢያችን ተፈጥሮ ሀብት

### 3.1 የተፈጥሮ ክስተት

ቁልፍ ቃላት

- ክስተት
- ወቅት
- መለኪያ
- መጠን
- ጊዜ
- ተዋፅኦ
- ህብረቀለም

| |
|---|
| ክስተት ማለት ምን ማለት ነው□<br><br>የተፈጥሮ ክስተት ማለትስ□ |

ክስተት፡- በሰው የስሜት ህዋሳት በግልፅ ሊዳሰስ፣ ሊሰማ ወይም ሊታይ የሚችልና በዚህ የተነሣ በሰው አእምሮ ውስጥ የሚፈጠረውን ምስል የሚያሳይ ነገር ነው።

የተፈጥሮ ክስተት፡- በተፈጥሮ በድንገት ወይም በተደጋጋሚ ጊዜን ጠብቆ በመቀያየር የሚፈፀም ነገር ማለት ነው። ምሣሌ፡- ቀንና ሌሊት።

? የክስተት አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ግልፁ።

#### 3.1.1 የተፈጥሮ ክስተትን መመልከት

የተፈጥሮ ክስተት የሚባሉት፡- ቀንና ሌሊት፣ ወቅቶች፣ ድርቅ፣ የውሃ ሙላት፣ ቀስተዳመና፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የመሳሰሉት ናቸው።

ቀንና ሌሊት

| |
|---|
| በቀንና ሌሊት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው |
| አንድነታቸውስ ምንድነው |

ቀን

ቀን የሃያ አራት ሰዓት ግማሽ ብርሃንማ ጊዜ ነው። ፀሐይ ብርሃኗን የምትሰጥበት፣ ሞቃትና የተለያዩ ድምፆች የሚሰሙበት ጊዜ ነው።

ሌሊት፡- የሃያ አራት ሰዓት ግማሽ ጨለማማ ክፍልና የፀሐይ ብርሃን የማይታይበት፣ በአብዛኛው ቀዝቃዛና ጸጥታ የሰፈነበት ጊዜ ነው። ቀንና ሌሊት ጊዜን ጠብቀው የሚተካኩ የተፈጥሮ ክስተት ከሆኑት ነገሮች አንዱ ናቸው።

ወቅት

| |
|---|
| ▪ ወቅት ማለት ምን ማለት ነው |
| ▪ ወቅቶች ማለትስ |

ወቅት የጊዜ ክፍፍል ሲሆን የራሱ የሆነ መገለጫ ያለውና የተፈጥሮ ክስተት የሚንፀባረቅበት ጊዜ ነው። ወቅቶች ማለት ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት የተለያዩ ጊዜያት ከነተፈጥሮ ክስተታቸው ማለት ነው። ለምሣሌ፡- በዓመት ውስጥ አራት ወቅቶች አሉ። እነሱም፡- በጋ፣ በልግ፣ ክረምትና ፀደይ ናቸው።

ክረምታና በጋ

| |
|---|
| - የክረምትና በጋ ልዩነታቸው ምንድነው |
| - ዝናባማ የሚሆነው የትኛው ነው |
| - ፀሐያማ የሚሆነውስ |

ክረምት

ክረምት ከአራቱ ወቅቶች አንዱ የሆነ የተፈጥሮ ክስተት ነው። በአብዛኛው ሰማዩ በደመና የሚሸፈንበት፣ የዝናብ መጠኑ ከፍ የሚልበትና ምድር በአረንጓዴ እፅዋት የምትሞላበት ወቅት ሲሆን ይኸውም ከሰኔ አንድ እስከ ነሐሴ ሰላሳ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ወይም የሚያካትት ነው።

በአጠቃላይ በክረምት ወቅት መሬቱ ጭቃማ ይሆናል። ወንዞች በውሃ ይሞላሉ፣ ምንጮች መፍሰስ ይጀምራሉ። ተክሎች ይለመልማሉ። ገበሬው ዘር የሚዘራበት ጊዜ በመሆኑ የተለያዩ የአዝርዕት አይነቶች የሚታዩበትና ዕርጥበታማ ወቅት ነው።

በጋ

በጋ ከታህሳስ አንድ እስከ የካቲት ሰላሣ ያለው ወቅት ሲሆን የሚከተሉት ባህሪያት አሉት። እነሱም፡- የፀሐይ ሙቀት መጨመር፣ በክረምት የጨቀየው መሬት መድረቅ፣ የወንዞች ሙላት መቀነስ፣ ገበሬው ሰብሉን ሰብስቦ ወደ ቤቱ የሚያስገባበትና ደረቃማ ወቅት ነው።

ድርቅ

ድርቅ በበጋው መራዘም የተነሣ በዝናብ እጥረት የሚከሰት የተፈጥሮ ክስተት ነው። በዚህም የተነሣ እፅዋቶች የሚደርቁበት፣ የቤትም ሆነ የዱር እንስሳት ለከፍተኛ ጉዳት የሚዳረጉበትና የሰውንም ልጅ ለከፍተኛ የምግብ እጥረት የሚዳርግ ክስተት ነው።



ሥዕል 3/1 ድርቅ የሚያስከትለው ጉዳት

- ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ□
- የድረቅ መንስኤ ምን እንደሆነ ወላጆቻችሁን ወይም ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ መልሱን በጽሁፍ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡላቸው።

የጎርፍ መጥለቅለቅ

- የጎርፍ መጥለቅለቅ ማለት ምን ማለት ነው□
- መንስኤውስ□
- የሚያስከትለው ጉዳትስ ምንድነው□

የጎርፍ መጥለቅለቅ ማለት ፡- የሰብል፣ የቡቃያና መኖሪያ ሰፈር በውሃ መሸፈንን የሚያካትት ክስተት ማለት ነው። መንስኤውም ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ለረጅም ሰዓታት መዝነብና በዚህም የተነሳ በሚፈጠረው ከፍተኛ የጎርፍና የወንዞች ሙላት ነው። የጎርፍ መጥለቅለቅ ከድርቅ ባልተናነሰ ሁኔታ በሰውና በእንስሳት እንዲሁም በምግብ ሰብል ላይ ጉዳት የሚያደርስና አልፎ አልፎ የሚከሰት ክስተት ነው።

ቀስተዳመና

- ቀስተ ዳመና ምንድነው□
- እንዴትስ ይፈጠራል□
- ስንት ቀለማትስ አሉት□
- ቀለማቱስ ምንድናቸው□

ቀስተዳመና በሰማይ ላይ የሚፈጠር ህብረቀለም ነው። በአብዛኛው ሰማይ ሲዳምንና ካፊያ ሲኖር ይፈጠራል። የሚፈጠረውም የፀሐይ ብርሃን በውሃ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ ነው። ቀለማቱም፡- ቀይ፣ ብርቱካንማ፣ ብጫ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊና ወይን ጠጅ ናቸው።



ሥዕል 3/2 ቀስተደመና

**መልመጃ 3.1**

መመሪያ ሀ**)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት

የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ቀስተ ዳመና በዑደት የሚከሰት የተፈጥሮ ክስተት ነው።
2. የፀሐይ ብርሃን በሌሊት ሊገኝ ይችላል።
3. ቀንና ሌሊት ከተፈጥሮ ክስተት አይመደቡም።
4. የተፈጥሮ ክስተት በዑደት ወይም በአጋጣሚ የሚከሰት ነገር ነው።
5. ክረምትና በጋ የወቅቶች አካል ናቸው።

መመሪያ ለ) በ "ሀ" ሥር የተፃፉትን በ "ለ" ስር ከተፃፉት ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. እርጥበታማ ወቅት | ሀ. በዝናብ እጥረት የሚከሰት |
| 2. የጊዜ ክፍፍል | ለ. ዝናብ በውሃ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ |
| 3. ቀስተዳመና | የሚፈጠር |

4. ደረቃማ ጊዜ ሐ. ክረምት

5. ድርቅ መ. ወቅት

ረ. በጋ

መመሪያ ሐ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በዝርዝር ግለፁ።

1. አልፎ አልፎ የሚከሰቱት የተፈጥሮ ክስተቶች የትኞቹ ናቸው?
2. በዑደት ከሚከሰቱት የተፈጥሮ ክስተቶች ሁለቱን ጥቀስ/ሺ/።
3. የቀንና ሌሊት ልዩነቶችን በማነፃፀር ግለፁ።
4. ድርቅና የጎርፍ መጥለቅለቅ እንዴት እንደሚከሰቱ በማነፃፀር ግለፁ።
5. የቀስተ ዳመናን ሥዕል ቀዩን ቀለም በማስቀደም በቅድም ተከተል ሠርተህ/ሽ/ አሣይ/ዪ


**3.1.2** የህይወት ምዕራፎች /ደረጃዎች/

/መወለድ፣ ማደግ፣ መሞት/

- የህይወት ምዕራፍ ማለት ምን ማለት ነው?
- መወለድ፣ ማደግና መሞት የተፈጥሮ ክስተት ነውን?
- ለዘር መብቀል የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድናቸው?
- ቢራቢሮ ምንድናት?
- ቢራ ቢሮዎች እንዴት ይራባሉ?

ህይወት ያላቸው ነገሮችን ህይወት ከሌላቸው የሚለየው አንዱ መራባት መቻላቸው ነው። የተራባውም የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን በማለፍ እንደገና ይራባና በመጨረሻ አርጅቶ ይሞታል። የሕይወት ምዕራፍ ማለት አንድ

ህይወት በተለያየ የእድገት ደረጃ ውስጥ ማለት ነው። ምሣሌ፡- 1 የሰው ህይወት ምዕራፍ።




ሥዕል 3/3 የሰው እድገት ደረጃ

ቢራቢሮዎች በራሪ ነፍሳት ናቸው። የሚራቡትም እንቁላል በመጣል ሲሆን እንቁላላቸውንም የሚጥሉት በቅጠላቅጠል ላይ ነው።

ምሣሌ፡- **2** የቢራቢሮ ህይወት ምዕራፍ


እንቁላል → እጭ → አባጨጓሬ → ቢራቢሮ




ሥዕል **3/4** የቢራቢሮ ዕድገት ደረጃ

ሥዕል 3.4 በማየት ቢራቢሮዎች ስንት የእድገት ደረጃ እንዳላቸው ግለፁ።

ምሣሌ፡- 3 የእፅዋቶች ህይወት ምዕራፍ፡- አብዛኞዎቹ እፅዋቶች የሚበቅሉት በዘር ፍሬያቸው ነው። የዘርፍሬው ለመብቀል የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ነገሮችን (ውሃ፣ አየርና ተስማሚ ሙቀት) ሲያገኝ የዘሩ ህይወት ክፍል በዘሩ ውስጥ ያለውን ምግብ በመመገብ ማደግ ይጀምራል። ከዚያም፡- ሥር፣ ቅጠልና ግንድ በማፍራት ያድጋል፤ ያፈራል፤ እንደ ተክሉ ዓይነት ጊዜው ሲደርስ አርጅቶ ይሞታል።



ሥዕል **3/5** የእፅዋት እድገት ደረጃ

**መልመጃ 3.2**

ሀ**.** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ ግለፁ።

1. የቢራቢሮ የመጀመሪያ እድገት ደረጃ ምንድነው?
2. የቢራቢሮ የህይወት ምዕራፎች ስንት ናቸው?
3. ለዘር መብቀል የሚያስፈልጉ መሠረታዎ ነገሮች ምንድንናቸው?
4. የህይወት ምዕራፎች ምን ዓይነት የተፈጥሮ ክስተት ናቸው?
5. በእፅዋት የህይወት ምዕራፍ ውስጥ ዘር የሚያፈራው የትኛው ደረጃ ነው?


### **3.1.3** መለኪያዎች

የርዝመት፣ የመጠንና የጊዜ መለኪያዎች

- የምንለካቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
- የወገብህ(ሽ) ቁጥር ስንት ነው?
- የአንድ ብር ርዝመትና ስፋት ስንት ነው?
- መለካት ለምን ይጠቅማል?

የርዝመት መለኪያ

ርዝመት (ርቀት) የሚለካው፡- በሴንቲ ሜትር፣ በሜትር፣ በኪሎ ሜትር ነው። ኪሎ ሜትር ትልቁ የርዝመት መለኪያ ሲሆን ትንሹ ደግሞ ሲንቲ ሜትር ነው።



ሥዕል 3/6 የተለያዩ የርዝመት መለኪያዎች

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/1**

አላማ፡- በክፍል ካሉት ተማሪዎች ውስጥ ከፍተኛ የቁመት ልኬት ያላቸውንና ዝቅተኛ የቁመት ልኬት ያላቸውን ለይቶ ማወቅ።

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡

- ማስመሪያ ወይም የቀመር መለኪያ ሜትር
- የተዘጋጀ የልኬት ማስፈሪያ ሠንጠረዥ

አሠራር

ሁለት ሁለት በመሆን በቁመት መለኪያ ሜትር ተራ በተራ መለካካትና የልኬት መጠኑን በልኬት ማስፈሪያ ሠንጠረዥ ውስጥ በስም ለይቶ ማስፈር (መመዝገብ)።

| ተ.ቁ | የተማሪው ስም | የቁመት ርዝመት | |
|---|---|---|---|
| | | ሜትር | ሴንቲ ሜትር |
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |
| 7 | | | |
| 8 | | | |
| 9 | | | |
| 10 | | | |
| 11 | | | |
| 12 | | | |


ሠንጠረዥ 3/1 የክፍል ተማሪን ቁመት መለየት

የተግባር ጥያቄ **3/1**

- በልኬት ሠንጠረዡ መሠረት የክፍላችሁ ረጅሙ (ሟ) ተማሪ ማነው (ናት)?
- በልኬት ሠንጠረዡ መሠረት የክፍላችሁ አጭሩ (ሯ) ተማሪ ማነው (ናት)?

የመጠን መለኪያ

| |
|---|
| - መጠን ማለት ምን ማለት ነው? |
| - መጠን በምን ይለካል? |
| - የራስህ (ሽ) ክብደት ስንት ነው? |




ሥዕል 3/7 የተለያዩ የክብደት መለኪያዎች

ተግባራ ክንዋኔዎች **3/2**

አላማ፡- በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ክብደት መለየት።

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

- የክብደት መለኪያ (ሚዛን)
- የተዘጋጀ የልኬት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ

አሠራር

- እያንዳንዱ ተማሪ ተራ በተራ ክብደቱን እንዲለካ ማድረግና ውጤቱንም በተዘጋጀው ሠንጠረዥ መመዝገብ፣
- በተገኘው ውጤት መሠረት በክፍል የሚገኘውን ከፍተኛ፣ ዝቅተኛና ተደጋጋሚ (እኩል) ክብደት ያለውን መለየት።

| ተ.ቁ | ስም | ክብደት በኪሎ ግራም | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ክፍተኛ | ተደጋጋሚ | ዝቅተኛ |
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |
| 7 | | | | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |
| 10 | | | | |
| 11 | | | | |
| 12 | | | | |
| 13 | | | | |

ሠንጠረዥ **3/2** ክብደትን መለየት


መጠን ወይም ክብደት አንድ ነገር በውስጡ ያካተታቸው መጠነቁስ ማሣያ ነው። ክብደት የሚለካው በክብደት መለኪያ መሣሪያ (ኪሎ ግራም) ነው። መጠን ወይም ክብደት የሚለካው በግራምና በኪሎ ግራም ነው። ግራም ትንሹ የክብደት መለኪያ ሲሆን ኪሎ ግራም ደግሞ ትልቁ የክብደት መለኪያ ነው።

አንድ ኪሎ ግራም አንድ ሺህ ግራም ነው።

?

- አንድ ኩንታል ስንት ኪሎ ግራም ነው?

የጊዜ መለኪያ



? የእጅ ሰዓት                    የግድግዳ ሰዓት


ሥዕል 3/8 የጊዜ መለኪያዎች

ጊዜ ማለት የቀን፣ ሳምንት፣ ወር ወይም የዓመት ርዝማኔ ማለት ነው። ይህ ርዝማኔ የሚለካው፡- በሰኮንድ፣ በደቂቃ፣ በሠዓት፣ በቀን፣ በሳምንታት፣ በወራት፣ ወዘተ ነው። ትንሹ የጊዜ መለኪያ ሰኮንድ ሲሆን ትልቁ ደግሞ ክፍለ ዘመን ነው።

? - አንድ ሰዓት ስንት ደቂቃ ነው?
- አንድ ደቂቃስ ስንት ሰኮንድ ነው?

ዘመናዊና ባህላዊ መለኪያ

- ባህላዊ መለኪያ ምን ዓይነት ነው?
- ለባህላዊ መለኪያ ዘዴ የምንጠቀምባቸው ነገሮች ምንድንናቸው?



ባህላዊ መለኪያ

ሥዕል 3.9 ባህላዊ መለኪያዎች

ዘመናዊ መለኪያ

ዘመናዊ መለኪያ የተለያየ ዓይነትና መጠን ያለው ሆኖ የልኬት መጠንን ለመግለፅ (ለመለካት) የሚያገለግል መሣሪያ ነው። ለምሣሌ፡- የተለያዩ ሜትሮች፣ ማስመሪያዎች፣ ወዘተ።

ባህላዊ (የተለምዶ) መለኪያ

የተለምዶ መለኪያ ዘመናዊ መለኪያ ከመሠራቱ በፊት ሰዎች የተለያዩ የሰውነታቸውን ክፍሎች ሌሎች ነገሮችን በመጠቀም የአንድን ነገር ርዝመትና ስፋት፣ ወዘተ የሚገልፁበትና አሁንም አልፎ አልፎ በአገልግሎት ላይ ያለ የመለኪያ ዘዴ ነው። እነዚህም የመለኪያ ዘዴዎች፡- ስንዝር፣ ክንድ፣ ጫማ፣ እርምጃ፣ ቁና፣ ፈረሱላ፣ ጋሻ፣ ወዘተ ናቸው።

መልመጃ **3.3**

መመሪያ ሀ**)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወላጆቻችሁን ወይም ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አሣዩ።

1. አንድ ፈረሱላ ስንት ኪሎ ግራም ነው?

2. አንድ ጋሻ ስንት ስኬር ካሬ ሜትር ይሆናል?

3. አንድ ክንድ ስንት ሜትር ወይም ስንት ሴንቲ ሜትር ይሆናል?

4. በአንድ ቀን ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?

መመሪያ **ለ)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ርዝመትን በክብደት መለኪያ መለካት ይቻላል።

2. ዓመት ከጊዜ መለኪያ ዘዴ አንዱ ነው።

3. ፈሣሽ ነገርን በክብደት መለኪያ (ሚዛን) መለካት ይቻላል።

4. የህይወት ደረጃዎች የተፈጥሮ ክስተት ናቸው።

### 3.1.4 ቁሣቁሶችን መመደብ

- መመደብ ማለት ምን ማለት ነው?
- በአከባቢችሁ የሚገኙ ነገሮችን በዝርዝር ጥቀሱ።
- ከጠቀሣችሁኋቸው ነገሮች ውስጥ ተፈጥሮአዊ የሆኑትን በአንድ ላይ በመመደብ በዝርዝር ግለፁ።
- በአከባቢያችሁ ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ ሰው ሰራሽ የሆኑትን በአንድ ላይ በመመደብ ለይታችሁ ግለፁ።
- በተፈጥሮአዊና በሰው ሰራሽ ነገር መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው?

በተፈጥሮአዊ በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነሱም፡- ህይወት ያላቸውን ነገሮችና ህይወት የሌላቸው ነገሮች ናቸው። ህይወት የሌላቸው ነገሮችም በሁለት ይመደባሉ። እነሱም፡- በተፈጥሮ የሚገኙና ሰው ሰራሽ ናቸው። በተፈጥሮ የሚገኙ ህይወት የሌላቸው

የምንላቸው እንደ ድንጋይ፣ አፈር፣ ውሃ፣ አየር፣ ማዕድናት፣ ወዘተ ናቸው። ሰው ሰራሽ ህይወት የሌላቸው የምንላቸው ደግሞ፡- መስታወት፣ ፊዶዮ፣ መኪና፣ አውሮፕላን፣ ጎማ፣ ላስቲክ፣ ወዘተ ናቸው።

ሌሎች የተለያዩ ነገሮችን ደግሞ የስሜት ህዋሳቶቻችንን በመጠቀም ተፈጥሮአዊ ባህሪያቸውን ለምሣሌ፡- ጠንካራ፣ ልል፣ ሸካራ፣ ለስላሳ፣ ከባድ፣ ቀላል፣ ወዘተ በማለት ለይተን እንመድባለን። ነገሮችን ለመለየት የምንጠቀምባቸው ስሜቶቻችንም በማየት ለምሣሌ፡- ቀለማትን፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ወዘተ በማለት ቅርፆችን፡- ክብ፣ ጠፍጣፋ፣ ሞላላ፣ ወዘተ በማለት ርቀትን ደግሞ ቅርብ፣ ሩቅ፣ ረጅም፣ አጭር በማለት እንለያለን። እንዲሁም በመዳሰስ፣ በማሽተትና በመቅመስ ነገሮችን እንለያለን። ነገር ግን በመቅመስ ነገሮችን ለመለየት መሞከር ለአደጋ ሊያጋልጥ ስለሚችል ካልተነገረን በስተቀር የማናውቅን ነገር በመቅመስ ለማለየት መሞከር በፍፁም አይመከርም።

## መልመጃ **3.4**

*መመሪያ ሀ*. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ተስማሚውን ቃል በባዶ ቦታ በመሙላት የተሟላ ዓረፍተ ነገር አድርጓቸው።

1. በአከባቢያችን የሚገኙ ነገሮች በ __________________ ይመደባሉ።
2. በአከባቢያችን የሚገኙ ህይወት የሌላቸው ነገሮች በ ________________ የሚመደቡ ሲሆን እነሱም፡ ___________ እና ______________ ናቸው።
3. ሸካራንና ልስላሴነት ያላቸውን ነገሮች መለየት የምንችለው በ _____ ነው።
4. የተለያየ ጣዕም ያላቸው ነገሮችን መለየት የምንችለው በ_________ ነው።
5. ቀለማትንና የተለያየ ቅርፅ ያላቸውን ነገሮች የምንለያቸው በ ______ነው።

*መመሪያ ለ*. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ ግለፁ።

1. በተፈጥሮ ከሚገኙ ህይወት የሌላቸው ነገሮች ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ።

   ሀ. ____________________________

   ለ. ____________________________

   ሐ. ____________________________

2. ከሰው ሰራሽ ህይወት የሌላቸው ነገሮች ውስጥ አራቱን ጥቀሱ።

   ሀ. ____________________________

   ለ. ____________________________

   ሐ. ____________________________

   መ. ____________________________

3. በመዳሰስ ከምንለያቸው ነገሮች ተፈጥሮአዊ ባህሪይ ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ።

   ሀ. ____________________________

   ለ. ____________________________

   ሐ. ____________________________

## 3.2 የተፈጥሮ ሀብት

- የተፈጥሮ ሀብት ማለት ምን ማለት ነው?
- የተፈጥሮ ሀብት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
- በአከባቢያችሁ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ምን ምን ናቸው?


የተፈጥሮ ሀብት ማለት በአከባቢያችን በተፈጥሮ የሚገኙና ለሰው ልጅ ጥቅም መዋል የሚችሉ ነገሮች ሁሉ የተፈጥሮ ሀብት ተብለው ይጠራሉ።


### 3.2.1 የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

ዋና ዋናዎቹ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ እፅዋት፣ እንስሳት፣ ውሃ፣ አየር፣ ደን፣ ማዕድናት (ብረታ ብረት)ና ጨው ናቸው።

## እፅዋት

እፅዋት የተለያየ ዓይነትና ተፈጥሮ ያላቸው ሆነው ሰው የሚተክላቸውንና በተፈጥሮ የሚበቅሉትን ሁሉ ያጠቃልላል። እፅዋት ለሁሉም እፅዋት በል እንስሳት በምግብ ምንጭነት የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው። ለሰው ልጅ ምግብነት የሚውሉ እፅዋት ለምሳሌ፡- ጎመን፣ ሙዝ፣ ድንች፣ እንሰት፣ ብርቱኳን፣ አቮካዶ፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ወዘተ ናቸው።







ሥዕል **3/10** ለሰው ልጅ ምግብነት የሚውሉ የእፅዋት ውጤቶች

## እንስሳት

እንስሳት የዱርና የቤት (ለማዳ) በመባል ይመደባሉ። የዱር እንስሳት የሚባሉት በጫካ የሚኖሩ ሲሆን ለማዳ የሚባሉት ደግሞ ከሰው ጋር ተላምደው በቤትና በቤት አካባቢ የሚኖሩ ናቸው። የቤት እንስሳት ለሰው ልጅ ከፍተኛ አገልግሎት


ያበረክታሉ። ከነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ ለምግብ ምንጭነትና ለጉልበት አገልግሎት የሚውሉት ተጠቃሾች ናቸው።



ሥዕል **3/11** ለሰው ልጅ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ የቤት እንስሳት

የዱር እንስሳት የምንላቸው ለምሣሌ፡- አንበሳ፣ ጅብ፣ ነብር፣ አቦሸማኔ፣ ተኩላ፣ ቀበሮ፣ ዝንጀሮ፣ ጉሬዛ፣ ግሥላ፣ ወዘተ ናቸው። ከእነዚህ እንስሳት ውስጥ ብርቅዬና በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የተለያዩ አጥቢና አእዋፋት አሉ። እነዚህን እንስሳት ለመመልከትና ለማጥናት ብዙ ሀገር ጎብኝዎች ወደ ሀገራችን ይመጣሉ። እነዚህ ጎብኝዎች ሲመጡ ገንዘብ ስለሚከፍሉ የሀገር ኢኮኖሚ ያድጋል። ስለዚህ እነዚህን እንስሳት መንከባከብና መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

የዱር እንስሳትን ደህንነት የምንጠብቀው የደንን ሀብት በመጠበቅና በማስፋፋት እንዲሁም ህገ ወጥ አደንን በመከላከል ነው።




ሥዕል **3/12** የዱር እንስሳት በከፊል

ውሃ

| |
|---|
| - ውሃ ምንድነው? |
| - ከየትስ ይገኛል? |

ውሃ ከሃይድሮጂንና ኦክስጂን ጋስ ውህደት የተሰራ ፈሳሽ የተፈጥሮ ሀብት ነው። ቀለም፣ ጣዕምና ሽታ የሌለው ለሰው ልጅና ለሌሎችም ህይወት ላላቸው ነገሮች ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጥ ፈሳሽ ነው።

ውሃ ከየት ይገኛል**?**



ሥዕል **3/13** ውሃ የሚገኝባቸው ቦታዎች

?

- ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ?
- ሥዕሉን በመመልከት ውሃ ከየት እንደሚገኝ ጥቀሱ።
- ከውሃ ጥቅሞች ውስጥ ቢያንስ አራቱን ጥቀሱ።


ሀ. ________________________________

ለ. ________________________________

ሐ. ________________________________

መ. ________________________________

ውሃ ከሚሰጣቸው በርካታ አገልግሎቶች ውስጥ፡- ለሁሉም ሕይወት ላላቸው ነገሮች በምግብ ክፍልነት የሚያገለግል ሲሆን በተለይ ለሰው፡- ምግብን ለማዘጋጀት፣ ገላን ለመታጠብ፣ ልብስ ለማጠብ ያገለግላል። በተጨማሪም ለማጓጓዣነት፣ የኤሌክትሪክ ጉልበት ለማመንጨት እንዲሁም ለተለያዩ እንስሳትና እፅዋት በመኖሪያነትና መራቢያነት ወዘተ ያገለግላል።




ሥዕል **3/14** የውሃ አገልግሎት

አየር

አየር የተለያዩ ጋሶች ድብልቅ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ነው። ንፁህ አየር ለሰውም ሆነ ለሌሎች ህይወት ላላቸው ነገሮች እጅግ አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ስጦታ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ጥቅሞችም አሉት።

ለምሣሌ፡- የመኪና ጎማ፣ የሞተር ሣይክል፣ የብስክሌት ጎማ ለመሙላት፣ ኳስ ለመሙላት፣ እሳት ለማንደድና ለማጥፋት፣ ምርትን ከገለባ ለመለየት፣ ለማጓጓዣ (አውሮፕላን)፣ ወዘተ ያገለግላል።



ሥዕል **3/15** የአየር ጥቅም በከፊል

አፈር

- አፈር ምንድነው?
- አፈር እንዴት ይፈጠራል?
- አፈር ለምን ይጠቅማል?


-

አፈር ከድንጋይ ስብርባሪ፣ ከእንስሳትና እፅዋት ቅሪተ አካል (ብስባሽ) የተሰራ ነው። ትላልቅ አለቶች (ድንጋይ) በረጅም ጊዜ የፀሀይ ሙቀት፣ ዝናብና ቅዝቃዜ ሲፈራረቅባቸው ተፈረካክሰው ወደ አፈርነት ይለወጣሉ። እንስሳትና እፅዋት ሲሞቱ አካላቸው ይበሰብስና ከእነዚህ የአለት ፍርክስካሾችሽ ጋር በመደባለቅ አፈር ይሆናል። በዚህ አይነት መንገድ የተሰራ አፈር ለም አፈር ይባላል። አፈር ለተክሎች እድገት አስፈላጊ ሲሆን ለሰው ልጅም ብዙ አገልግሎት ይሰጣል።

አፈር በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባል። እነሱም፡- ሸክላማ አፈር፣ አሸዋማ አፈር፣ ደቃቅ ወይም ለም አፈር ናቸው።

ደን

ደን በተፈጥሮ የሚገኝ (የበቀለ) ወይም ሰው የተከለው ሊሆን ይችላል። ለአንድ ሀገር ከሚያስፈልጉትን የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች ውስጥም አንዱ ነው። ደን ለብዙ አገልግሎቶች የሚውሉ ትላልቅ ዛፎችና ብዛት ያላቸው የተለያዩ የእፅዋት ዓይነቶች በቅለው የሚገኙበት ቦታ ነው። ከደን ሀብት ጥቅም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡- የብዙ የተለያዩ የዱር እንስሳት መኖሪያ (መጠለያ) በመሆኑ ለቱሪስት መስህብነት ያገለግላል። የተፈጥሮ አየር ሚዛንና የአካባቢ እርጥበትን ይጠብቃል። ለሙጫ፣ ለወረቀት ሥራ፣ ወዘተ... የሚያገለግሉ ዛፎች መገኛ በመሆኑ ይጠቅማል። የተለያዩ የቤትና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችን ለመስራት የሚያገለግሉ ዛፎች መገኛ በመሆን ወዘተ ይጠቅማል።




ሥዕል **3/16** ከደን ውጤት የሚገኙ የመገልገያ ቁሳቁሶች

ማዕድናት

ማዕድናት በመሬት ውስጥ ወይም በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ሲሆኑ እነሱም፡- መዳብ፣ ብረት፣ ወርቅ፣ ብር፣ አልሙኒየም፣ ኮፐር፣ ወዘተ ብረትነት ያላቸውና ብረትነት የሌላቸው እንደ ተፈጥሮ ጋስ፣ ነዳጅና ዘይት የመሳሰሉት ናቸው።

የተፈጥሮ ጋስ ለመኖሪያ ቤትና ለእንዱስትሪ በሀይል ምንጭነት ያገለግላል ወይም የሚያገለግል የተፈጥሮ ሀብት ነው። ማዕድናት በአብዛኛው ብረትነት ያላቸው በመሆናቸው እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የመገልገያ ቁሣቁሶችና ንብረቶችን ለመሥራት ያገለግላሉ። ለምሣሌ፡- የአንገትና የእጅ ጌጣጌጥ ለመሥራት፣ የመገልገያ ቁሳቁስ ማንኪያ፣ ብረት ድስት፣ ጭልፋ፣ ካውያ፣ ወዘተ የመጓጓዣ መኪና፣ አውሮፕላን፣ መርከብ፣ ወዘተ የግንባታ መዶሻ፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ ሚስማር፣ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።



ሥዕል **3/17** በመሬት ውስጥ ከሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች የሚሰሩ

- ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ?
- ማዕድናት የአንድ ሀገር የኢኮኖሚ መሠረት ናቸው።

### **3.2.2** የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም

- የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ማለት ምን ማለት ነው?
- የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ምን ምን ድነው?

የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ማለት፡- የተፈጥሮ ሀብቱን ደህንነት ሳንጎዳው አገልግሎቱ ዘላቂና አስተማማኝነት ባለው መንገድ ለቀጣዩም ትውልድ ሊተላለፍ በሚያስችል ዘዴ ሣይባክን መጠቀም ማለት ነው። የተፈጥሮ ሀብቶች ለሰው ልጅ ከሚያበረክቱት ጠቀሜታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። እኑሱም፡-

- ለምግብ ምንጭነት፣
- ለልብስ፣
- ለመጠለያ (ለተለያዩ ግንባታዎች)፣
- ለገቢ ምንጭነት (የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል)፣
- ለመጓጓዣ፣
- ለመዝናኛ፣
- ለቱሪስት መስህብነት (የሀገር ገጽታን ለማሳደግ)፣
- የተለያዩ የመገልገያ ቁሳቁሶችንና ጌጣጌጦችን ለመስራት፣ ወዘተ።

ለልብስ የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ሀብቶች

የሰው ልጅ ልብሶቹንና የተለያዩ መገልገያዎችን ከእንስሳትና እ    ፅዋት ውጤቶች ያዘጋጃል።

ለምሣሌ ከእንስሳት

ከቆዳቸው ከፀጉራቸው


- ቦርሳ - ሹራብ
- ጫማ - ብርድ ልብስ
- ኮት
- ጃኬት

ከቀንድና ሸሆናቸው የተለያዩ ጌጣጌጦችና መገልገያዎች፡-

| <u>መገልገያ</u> | <u>ጌጣጌጥ</u> |
|---|---|
| - ማንኪያ | - በተለያየ ቅርጽ የተሰሩ |
| - ጭልፋ | የግድግዳና የጠረጴዛ ጌጦች |
| - መጠጪያ (ዋንጫ) | (በወፎችና ሌሎች እንስሳት ቅርጽ |
| - የተለያዩ የልብስ ቁልፎችን | የተሰሩ) |

ከእፅዋት


- ከጥጥ፡- ጋቢ፣ ነጠላ፣ ቡልኮ፣ ቀሚስ፣ ሸሚዝ፣ ወዘተ።
- ከቃጫ፡- ጆንያ፣ ምንጣፍ፣ ቦርሣ፣ ዘምቢል፣ ወዘተ።




ሥዕል 3/18 ከዕፅዋት የተሰሩ ልብሶችና መገልገያዎች

የተፈጥሮ ሀብት መጠለያን ለመስራት ያገለግላል።

መጠለያ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ሲሆን ይህንን መሠረታዊ ነገር ለመሥራት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች የሚገኙት በአከባቢው ካሉት የተፈጥሮ ሀብት ነው። እነዚህም ጥሬ እቃዎች፡- ሣር፣ እንጨት፣ አፈር፣ ድንጋይና አሸዋ ናቸው።



ሥዕል **3/19** ከተፈጥሮ ሀብት የተሰሩ መጠለያዎች

## መልመጃ **3.5**

መመሪያ ሀ**)** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ለሁሉም ህይወት ላለው ነገር በምግብ ምንጭነት የሚያገለግል የተፈጥሮ ሀብት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. እንስሳት

   ለ. ማዕድን

   ሐ. አየር

   መ. እፅዋት

2. ብረትነት ያላቸው የመገልገያ ቁሳቁሶች የሚሰሩት ከ__________ ነው።

ሀ. ከእንስሳት ለ. ከማዕድናት

ሐ. ከእፅዋት መ. ከደን

3. ለቱሪስት መስህብነት የሚያገለግል የተፈጥሮ ሀብት የቱ ነው?

ሀ. ውሃ ለ. እፅዋት

ሐ. የዱር እንሰሳ መ. ማዕድን

4. የደን ሀብትን በመንከባከብ ደህንነቱ ሊጠበቅ የሚችል የተፈጥሮ ሀብት የቱ ነው?

ሀ. አየር ለ. አፈር

ሐ. የዱር እንስሳት መ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ውስን የሆነ የተፈጥሮ ሀብት የቱ ነው?

ሀ. ማዕድናት ለ. እንስሳት

ሐ. ውሃ መ. አየር

መመሪያ ለ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ ግለፁ።

1. ከውሃ መገኛዎች ውስጥ ሶስቱን ጥቀስ(ሺ)።

ሀ . ________________________________________

ለ. ________________________________________

ሐ. ________________________________________

2. ሶስቱ የአፈር አይነቶች እነማን ናቸው?

ሀ . ________________________________________

ለ. ________________________________________

ሐ. ________________________________________

3. መጠለያን ለመሥራት የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ሀብቶች የትኞቹ ናቸው? ቢያንስ ሶስቱን ጥቀስ/ሺ/።

ሀ . ________________________________

ለ. ________________________________

ሐ. ________________________________

4. በሀገራችን ብቻ ከሚገኙ የዱር እንስሳት ሁለቱን ጻፍ/ፊ/።

ሀ . ________________________________

ለ. ________________________________

5. ውሃ ለሰው ልጅ ከሚሰጠው ጥቅም ውስጥ ሶስቱን ጻፍ/ፊ/።

ሀ . ________________________________

ለ. ________________________________

ሐ. ________________________________

መመሪያ ሐ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. እንስሳት የቤትና የዱር በመባል ይመደባሉ።
2. አየር የተለያዩ ጋሶች ውሁድ ነው።
3. አፈር ከአለት ፍርክስካሽና(ስብርባሪ) ከቅሪተ አካል ብስባሽ የተሰራ ነው።
4. እንስሳትና እፅዋት አንዱ ለሌላው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ናቸው።
5. ደንና የዱር እንስሳት የማይነጣጠሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው።

**3.2.3** የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ

- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት ምን ማለት ነው?
- የተፈጥሮ ሀብት እንዴት ይጠበቃል?
- የተፈጥሮ ሀብትን የሚጎዱ ነገሮች (ሁኔታዎች) ምንድናቸው?

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት፡- የተፈጥሮ ሀብትን ለብክነትና ለጉዳት ከሚዳርጉ ሁኔታዎች መጠበቅ፣ መከላከልና መንከባከብ ማለት ነው። የተፈጥሮ ሀብታችንን ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ሳናደርግለት በግዴለሽነት ከተጠቀምንባቸው ለጉዳት ይዳረጉና እስከናካቴው ሊጠፉ ይችላሉ። ነገር ግን በጥንቃቄና በእንክብካቤ ይዘን ከተጠቀምንባቸው ዘላቂና አስተማማኝ አግልግሎት ይሰጡናል።

### 3.2.3.1 የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት ዓይነቶች

ከተፈጥሮ ሀብት ጉዳት ዓይነቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

ሀ. የአየር ብክለት፣ ለ. የውሃ ብክለት

ሐ. የደን መጨፍጨፍ፣ መ. የአፈር መሸርሸር ናቸው።

**ሀ.** የአየር ብክለት

የአየር ብክለት ማለት፡- የከባቢ አየር ይዘት መዛባት እንዲሁም በከባቢ አየር ውስጥ መኖር የማይገባቸው ለሰው ልጅ ጤንነት ተስማሚ ያልሆኑ ጋሶች ወደ ከባቢ አየር ውስጥ መቀላቀል ማለት ነው።

የአየር ብክለት መንስኤዎች፡-

- ከፋብሪካዎች የሚለቀቁ መርዛማነት ያላቸው የጭስ ጋሶች ምሣሌ፡- ሳልፈርዳይ ኦክሳይድ።

- ከተሽከርካሪ ሞተር የሚለቀቅ በከፊል የተቃጠለ ጋስ ለምሳሌ፡- ካርቦንሞኖክሳይድ።
- ከመፀዳጃ ቤቶች የሚለቀቅ ጋስ ለምሳሌ፡- ሜቴንጋስ
- በቤት ውስጥ ከሚነድ እንጨትና ከሰል የሚለቀቅ ጭስ ምሳሌ፡- ካርቦንዳይኦክሳይድ።
- የደን ቃጠሎ
- የደን መጨፍጨፍ ናቸው።

የአየር ብክለት መከላከያ ዘዴዎች፡-

- የደን ቃጠሎንና የደን መቆረጥን መከላከል፣
- ከፋብሪካዎችና ከተሽከርካሪዎች የሚወጣውን በካይ ጢስ በተተኪ ጉልበት በመቀየር መቀነስ፣
- ማንኛውንም አግባብ ያልሆነን ቃጠሎ መቀነስ፣
- ቆሻሻን ከማቃጠል ይልቅ መቅበር ናቸው።




ሥዕል 3/20 የከባቢ አየር የሚበከልባቸው መንገዶች።


**ለ)** የውሃ ብክለት

ውሃ በአግባቡ ካልተያዘ በቀላሉ ይበከላል። ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተህዋሲያንም መራቢያ ይሆናል። የተበከለ ውሃ ደግሞ ለሰውም ሆነ በውስጡ ለሚኖሩ እንስሳትን እፅዋት አደገኛ ነው።

የውሃ ብክለት መንስኤዎች

ዋና ዋናዎቹ የውሃ ብክለት መንስኤዎች፡-

- ከፋብሪካዎችና ሆስፒታሎች ወደ ወንዞችና ሀይቆች የሚለቀቅ እጣቢ፣ ዝቃጭና ኬሚካል፣
- በተለያዩ ምክንያት ወደ ወንዝ፣ ሀይቅና ውቅያኖስ የሚለቀቅ ጋዝ (ዘይት)፣
- ከሽንት ቤት ውጪ መፀዳዳት፣
- ከመኖሪያ ቤቶችና ሆቴሎች የሚለቀቅ ጥራጊ ቆሻሻ፣
- ከእርሻ መሬት በጎርፍ አማካኝነት እየታጠበ ወደ ወንዞችና ሀይቆች የሚገባ የማዳበሪያ ኬሚካል፣ ወዘተ ናቸው።



ሥዕል 3/21 የውሃ ብክለት መንስኤዎች

የውሃ ብክለት መከላከያ መንገዶች

ዋና ዋናዎቹ የውሃ ብክለት መከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡-

- ማንኛውንም ዓይነት ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዞች፣ ሐይቆችና ውቅያኖስ እንዳይገባ መከላከል፣
- መፀዳጃ ቤቶችን በመጠቀም ሽንትና ዓይነምድር ወደ ውሃ አካል እንዳይገባ መጠንቀቅ፣
- እፅዋቶችን መትከል፣
- ውሃን ለመጠጥነት ከመጠቀም በፊት የውሃ ማከሚያ መጨመር ወይም ማፍላትና በንፁህ ነጠላ ማጣራት።

ሐ. የደን መጨፍጨፍ

ለደን ሀብት መመናመን መንስኤዎች ሁለት ናቸው። እነሱም፡- የሰደድ እሳትና የደን መጨፍጨፍ ናቸው።

ለደን ሀብት ደህንነት የሚረዱ ዘዴዎችም፡- ከሰደድ እሳት መጠበቅ፣ በክፍት ቦታዎች ሁሉ ተክሎችን መትከል፣ ደንን አለመቁረጥና በተቆረጠው ምትክ ሌላ መትከል ተጠቃሾች ናቸው።

መ. የአፈር መሸርሸር

የአፈር መሸርሸር ማለት የአፈር ላይኛው ክፍል በጎርፍና በነፋስ እየታጠበና እየተጠረገ መወሰድ ማለት ነው። የአፈር መሸርሸር የአፈሩን ማዕድን ይዘት በመቀነስ ለምነቱን ያሳጣዋል።

የአፈር መሸርሸር መከላከያ መንገዶች


ዋና ዋናዎቹ የአፈር መሸርሸር መከላከያ መንገዶች ሁለት ናቸው። እነሱም፡-

1ኛ. እፅዋትን መትከልና

2ኛ. እርከን መስራት ናቸው።

እፅዋት መትከል

እፅዋት አፈሩን በሥሮቻቸው አቅፈው ስለሚይዙት በቀላሉ በጎርፍ በነፋስ ታጥቦ (ተጠርጎ) አይወሰድም።



ሥዕል 3/22 ገላጣ ቦታ ላይ ተክሎች ሲተከሉ።

እርከን መሥራት

ሁለተኛው የአፈር መሸርሸር መከላከያ ዘዴ እርከን በመስራት ነው። እርከን በቁልቁለታማና ተዳፋት አካባቢ የአፈርን መሸርሸር ለመከላከል አልፎ አልፎ በድንጋይ ወይም በአፈር የሚሰራ ደረጃ ነው። ይህ ዘዴ በቁልቁለት ወደታች የሚወረወረውን (የሚወርደውን) የውሃ ጉልበት በመቀነስ እየተጠረገ የሚሄደውን አፈር ያስቀረዋል።



ሥዕል **3/23** የእርከን ሥራ **(**ሰዎች ከድንጋይ **(**አፈር**)** እርከን ሲሰሩ**)**

**3.2.3.2** የተፈጥሮ ጥበቃ በቤትና በትምህርት ቤት

የአየር ብክለትን፣ የውሃ ብክለትንና የአፈር መሸርሸርን በመከላከል የተፈጥሮ አካባቢችንን መጠበቅ እንችላለን።

ሀ. የተፈጥሮ ጥበቃ በቤት

በቤታችን ለተፈጥሮ ጥበቃ ከምናደርግባቸው መንገዶች ዋና ዋናዎቹ፡-

- ከቤት የሚወጣውን ደረቅም ሆነ ፈሳሽ ቆሻሻን በጥንቃቄ ማስወገድ ወይም እንዲወገድ ማድረግ፣
- የጓሮ አትክልቶችን መትከል፣
- ችግኞችን መትከልና ተንከባክቦ ማሳደግ፣
- በደጃፋችን የሚያልፈውን የጎርፍ መሄጃ ቦይ እርከን በመሥራት እንዳይቦረቦር ማድረግና ተጠርጎ (ታጥቦ) የሚሄደውንአፈር ማስቀረት ናቸው።

ለ. የተፈጥሮ ጥበቃ በትምህርት ቤት

በትምህርት ቤት ውስጥ ለተፈጥሮ ጥበቃ ከምናደርግባቸው ዘዴዎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡- ቆሻሻን የትም አለመጣል፣ የተጣለውን ቆሻሻ ሰብስቦ በጥንቃቄ ማስወገድ፣ በባዶ ቦታዎች ችግኞችን መትከልና አፈር እንዳይሸረሸር ማድረግ፣ አከባቢን ማስዋብ፣ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።

## መልመጃ **3.6**

መመሪያ ሀ**)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ ግለፁ።

1. ከተፈጥሮ ጉዳት ዓይነቶች ውስጥ ሶስቱን ጻፉ

   ሀ. ____________________________________

   ለ. ____________________________________

ሐ. ____________________________________________

2. ከደን ሀብት ጥበቃ ዘዴዎች ውስጥ ሁለቱን ጻፉ

   ሀ. ____________________________________________

   ለ. ____________________________________________

3. የአፈር መሸርሸር መከላከያ ዘዴዎች ጻፉ

   ሀ. ____________________________________________

   ለ. ____________________________________________

4. እፅዋቶችንመትከል እንዴት የአፈር መሸርሸርን እንደሚከላከል በአጭሩ ግለፁ ______________________________________________________________________________________________

5. የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ በአጭሩ ግለፁ ______________________________________________________________________________________________

መመሪያ ለ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. በደን መጨፍጨፍ ይበልጥ የሚጎዳው ከሚከተሉት የቱ ነው?

   ሀ. አፈር          ለ. ውሃ

   ሐ. አየር          መ. የዱር እንስሳት

2. ከሽንት ቤት ውጪ መጸዳዳት ለየትኛው የተፈጥሮ ሀብት ብክለት መንስኤ ይሆናል?

   ሀ. ውሃ          ለ. አየር

   ሐ. ደን          መ. አፈር

**3.** የተሸረሸረ አፈር፦

ሀ. ለእፅዋቶች እድገት ተስማሚ ነው       ለ. የማዕድን ይዘቱ ከፍተኛ ነው።

ሐ. የማዕድን ይዘቱ ዝቅተኛ ነው       መ. ለም አፈር ነው


4. ከተሽከርካሪ ሞተር የሚለቀቅ በከፊል የተቃጠ ጋስ __________ ይባላል።

ሀ. ካርቦንዳይኦክሳይድ       ለ. ካርቦንሞኖክሳይድ

ሐ. ሣልፈርዳይኦክሳይድ       መ. ዝቃጭኬሚካል

### 3.3 በአከባቢያችን የሚገኙ እፅዋት


#### 3.3.1 የእፅዋት ክፍልና ተግባራቸው (ግንድ፣ ቅጠል፣ አበባና ሥር)




ሥዕል **3/24** የእፅዋት ክፍሎች

የእፅዋት ክፍሎች ከመሬት በታችና ከመሬት በላይ ተብለው በሁለት ይመደባሉ።

ሀ. ከመሬት በታች ያለው የእፅዋት ክፍል ስር ይባላል። ሥር ሁልጊዜ የሚያድገው ወደ አፈረ ውስጥ ነው። ስሮች ተራዘሞና ድራድር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። እነዚህም ቀጥ ብሎ ወደ መሬት የሚያድግና ተንሠራፍተው ወደ ጎን የሚያድገውን ሥር የሚያካትቱ ናቸው።



ሥዕል **3/25** የሥር ዓይነቶች

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/3**

ዓላማ፡**-** የሥር ዓይነቶችን መለየት።

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡**-**

- በአከባቢ የሚገኝ እፅዋት ሥር (ሣር፣ በቆሎ፣ የአበባ ጎመን፣ ካሮት፣ስኳር ድንች፣ ሸንኮራ አገዳ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ወዘተ)
- እርሳስ ላጲስ፣ ማስመሪያና ወረቀት (ደብተር) ወይም አስቀድሞ የተዘጋጀ የሥር መመዝገቢያ ሠንጠረዥ።

አሠራር፡- የተሰበሰቡ ሥሮችን ተራዘም ሥርና የተንሰራፉ ሥር ብሎ ለይቶ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ ውስጥ መመዝገብ።

| ተ.ቁ | የተክሉ ስም | ተራዘም | ድራድር ሥር |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |
| 7 | | | |
| 8 | | | |
| 9 | | | |

ሠንጠረዥ **3/3** የሥር ዓይነቶችን መለየት

የሥር ተግባር

- የሥር ተግባር ምንድን ነው?

የተክል ሥር የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል። እነሱም። ተክሉን ከአፈር ጋር ጠበቅ አድርጎ በማያያዝ ተክሉ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ማድረግ፣ ውሃና የሚሙ ማዕድናትን ከአፈር ውስጥ በመውሰድ ለተክሉ ላይኛው ክፍል (ግንድ፣ ቅርንጫፍ፣ ቅጠል፣ አበባና ፍሬ) በማቀበል ተክሉ ምግቡን እንዲያዘጋጅ ማድረግ ናቸው።

ለ. ከመሬት በላይ ያለው የእፅዋት ክፍል


ከመሬት በላይ ያለው የእፅዋት ክፍል፡- ግንድ፣ ቅርንጫፍ፣ ቅጠልና አበባ ናቸው።

ግንድ

የግንድ ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነሱም፡- ተንፏቃቂና ቋሚ ግንድ ናቸው።

**ሀ) ተፏቃቂ ግንድ**

**ተንፏቃቂ ግንድ የተወላገዱ ወይም የተጣመሙ ብዙ ቅርንጫፍ ግንዶች ያለው ነው።**



ሥዕል **3/26** የግንድ ዓይነቶች

**ለ) ቋሚ ግንድ**

**ቋሚ ግንድ፡- ቀጥ ያለና ቅርንጫፎቹ ያልበዙ ናቸው።**

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/4**

ዓላማ፡**-** በአከባቢ የሚገኙ የተክል ግንዶችን መለየት።

የሚያስፈልጉ ነገሮች

- ከአከባቢ የተሰበሰቡ ተክሎች።

- የተዘጋጀ ሠንጠረዥ ናቸው።


አሠራር፡-የተሰበሰቡ ተክሎችን ግንድ ቋሚና ተንፏቃቂ ማለት ለይቶ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ ውስጥ መመዝገብ።

| ተ.ቁ | የተክሉ ስም | ቋሚ /ቀጥ ያለ ግንድ | ተንፏቃቂ ግንድ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

ሠንጠረዥ 3/4 የግንድ ዓይነቶችን መመደብ

እንጨትነትና ሣርነት ያላቸው ግንዶች

እንጨትነት ያላቸው ግንዶች ውስጣቸው ዝግና ጠንካራ ተክሎች ሲሆኑ ሣር ያላቸው ግንዶች ደግሞ ውስጣቸው ክፍትና ጥንካሬ የሌለው ግንድ ያላቸው ተክሎች ናቸው።



ሀ) እንጨት ያለው ግንድ ለ. ሣር ያለው ግንድ

ሥዕል 3/27 እንጨት ያለውና ሣር ያለው ግንድ

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/5**

ዓላማ፡- በአከባቢ የሚገኙ ተክሎች ግንድን እንጨት ያለውና ሣር ያለው ግንድ ብሎ መለየት።

የሚያስፈልጉ ነገሮች

- በአከባቢ የሚገኙ ተክልችን (ግንድ) መሰብሰብ
- የተዘጋጀ ሠንጠረዥ

አሠራር፡- የተሰበሰቡ ግንዶችን ውስጣቸው ዝግ መሆኑንና ክፍት መሆኑን እያረጋገጡ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ መመዝገብ።

- በተሰጠው ምሣሌ መሠረት "□" በመፃፍ ማመልከት።

| ተ.ቁ | የተክሉ ስም | ሣርነት ያለው ግንድ | እንጨትነት ያለው ግንድ |
|---|---|---|---|
| 1 | በቆሎ | ✓ | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | ግራር | | ✓ |
| 8 | | | |
| 9 | | | |
| 10 | | | |

ሠንጠረዥ **3/5** ሣር ያለው ግንድና እንጨት ያለው ግንድን በዓይነት መመደብ

የተክል ግንድ ተግባር

| የተክል ግንድ ተግባር ምንድነው□ |
|---|

ግንድ የሚከተሉት ተግባራት አሉት። እነሱም፡-

ሀ. ውሃንና የሟሙ ማዕድናትን ከሥር ተቀብሎ ከላይ ላሉት የተክል ክፍሎች (ቅርንጫፎች፣ ቅጠል፣ አበባና ፍሬ) መስጠት፣

ለ. ቅጠሎች ያዘጋጁትን ምግብ ለቅርንጫፎችና ሥር ማስተላለፍ፣

ሐ. ለተክሉ ጥንካሬ መስጠትና ቀጥ ብሎ እንዲቆም ማድረግ፣


መ. ከመሬት በላይ ያለውን የተክሉን ክፍሎች (ቅርንጫፎችን፣ ቅጠሎች፣ አበባዎችንና ፍሬዎችን መሸከም ናቸው)።

ቅጠል

የቅጠል ዓይነትና ተግባር

የቅጠል ዓይነት

| - ቅጠሎች በምን በምን ይለያያሉ□ |
|---|



ሥዕል 3/28 የቅጠል ዓይነቶች

ቅጠሎች የሚለያዩት፡- ግንድ ላይ በሚኖራቸው አቀማመጥ፣ በጠርዛቸው ቅርጽ፣ በሥርወታቸው (ውስጣቸው በሚገኝ መስመር አቀማመጥ)፣ በስፋታቸው (በመጠናቸው)፣ ወዘተ ነው።

ተግባራዊ ክንውን **3.6**

ዓላማ፡- ቅጠሎችን በዓይነታቸው መመደብ።

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

- ከአከባቢ የተለያዩ ቅጠሎችን መሰብሰብ።
- የተዘጋጀ ሠንጠረዥ።

አሠራር፡-

የተሰበሰቡ ቅጠሎችን በሥዕል 3.28 ውስጥ ከተጠቀሱት የቅጠል ዓይነቶች ጋር በማነፃፀር የትኛው ዓይነት እንደሆነ ፊደሉን በሠንጠረዥ ውስጥ በመፃፍ ማመልከት።

| ተ.ቁ | ቅጠሉ የተወሰደበት ተክል ስም | ከሥዕል 3.28 ጋር ሲነፃፀር የሚመስለው |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| | | |

ሠንጠረዥ **3/6** ቅጠሎችን በዓይነታቸው መመደብ

### የቅጠል ተግባር

የቅጠል ዋናው ተግባር ለተክሉ ምግብ ማዘጋጀት ነው። ስለዚህ ቅጠል የተክሉ ወሳኝ ክፍል ነው።

አበባ



ሥዕል 3/29 የአበባ ዓይነቶች

| |
|---|
| - አበባ የትኛው የተክል ክፍል ነው |
| - አበባዎች የሚለያዩት በምናቸው ነው |

አበባዎች የተክል መራቢያ ዘር የሚገኝበት ክፍል ናቸው። የተለያየ ቀለም ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደማቅ ቀለም ሌሎቹ ደግሞ ደብዘዝ ያለ ቀለም አላቸው። ደማቅ ቀለም ያላቸው አበባዎችን ሰዎች ለውበታቸው ሲሉ በግቢያቸው፣ በየአደባባዩና መዝናኛ ቦታዎች ይተክሉዋቸዋል።

የአበባ ጥቅም፡-

አበባ የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት። እነሱም፡-

- ለተክሉ ፍሬና ዘር ማፍራት፣
- ለቤትና አካባቢ ድምቀት መስጠት፣
- ለንቦች ምግብ የሚሆን ወለላ ማዘጋጀት ናቸው።

መልመጃ **3/7**

መመሪያ ሀ**)** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የሥር ተግባር ያልሆነው የቱ ነው

   ሀ. ተክሉን ከአፈር ጋር ማያያዝ

   ለ. ውሃና የሟሙ ማዕድናትን ለግንዱ ማቀበል

   ሐ. ለእፅዋቱ ምግብ ማዘጋጀት

   መ. መልሱ አልተሰጠም

2. ከሚከተሉት ውስጥ የግንድ ተግባር የቱ ነው

   ሀ. ለተክሉ ምግብ ማዘጋጀት

   ለ. ለተክሉ ፍሬ ማፍራት

   ሐ. ከመሬት በላይ ያለውን የተክሉን ክፍል መሸከም

   መ. ተክሉን ከአፈር ጋር ማያያዝ

3. ዘርና ፍሬን የሚያፈራ የተክል ክፍል የቱ ነው

   ሀ. ቅጠል ለ. ግንድ

   ሐ. አበባ መ. ሥር

መመሪያ ለ) የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃል በመሙላት

አረፍተ ነገሩን የተሟላ አድርጉ።

1. ሁለቱ የስር ዓይነቶች _________________ እና ______________ ናቸው፡
2. ሁለቱ የግንድ ዓይነቶች __________ እና ________ ናቸው፡
3. ከአበባ ጥቅሞች ውስጥ ሁለቱ ______ እና_______ናቸው።
4. ከግንድ ተግባሮች ውስጥ ሁለቱ _________ እና_________ ናቸው።

መመሪያ ሐ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ቅጠሎች ሁሉ አንድ ዓይነት ናቸው።
2. የተክሎች ግንድ እድገቱ ወደ አፈር ውስጥ ነው።
3. ሁሉም እፅዋት ምግባቸውን ማዘጋጀት ይችላሉ።
4. እንጨት ያለው የተክል ግንድ፣ ሣር ካለው የተክል ግንድ የበለጠ ጠንካራ ነው።
5. ሣር ያለው የተክል ግንድ ውስጥ ክፍት ነው።

### **3.3.2** የተለያዩ የእፅዋት ክፍሎችን መሰብሰብና ማስቀመጥ

የተለያዩ እፅዋት ወይም የእፅዋት ክፍልን ሣይበላሽ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ማድረግ ይቻላል። ይህም ዘዴ ምንበር ይባላል።

እፅዋትን ወይም የእፅዋት ክፍልን (ቅጠል፣ ግንድና ሥር) ማንበር

እፅዋትን ለማንበር፡- ተክሉን (እፅዋቱን) አስተካክሎ ማዘጋጀት፣ ንፁህ ጋዜጣ አዘጋጅቶ ከላይና ከታች ማድረግና በጋዜጣው ላይ ጠንካራ ካርቶን ማድረግ

ምቹ ቦታ አስቀምጦ ከባድ ነገር (ድንጋይ) በመጫን እንዲደርቅ ማድረግ። መድረቁ ሲረጋገጥ ብርሃን በሚያስተላልፍ ፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ አድርጎ ከማስታወሻ ጋር አሽጎ ማስቀመጥ ነው።

በማስታወሻው ላይም፡-

- የተክሉ ስም፣
- ከየት እንደተገኘ፣
- የተገኘበት ቀን፣
- ማን እንዳገኘው፣
- ቀንና ዓመተ ምህረት ይፃፍበታል።

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/7**

ዓላማ፡- እፅዋትን ማንበር

የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-


መቀስ፣ የፕላስቲክ ከረጢት፣ ምላጭ፣ ፕላስተር ወይም ሙጫ፣ ዶሲ( ክላሰር)።

አሠራር

- የሚፈለገውን እፅዋት ወይም የእፅዋት ክፍልን መሰብሰብ፣
- በማንበር ማድረቅ፣
- የደረቀውን እፅዋት በወፍራም ወረቀት (ዶሲ) ላይ በሙጫ ወይም በፕላስተር ማጣበቅ፣
- በተክሉ ግርጌ የእፅዋቱ ስም፣ የተሰበሰበበት ቀን፣ እፅዋቱ የተገኘበት ቦታ (ሥፍራ)፣ የሰብሳቢውን ስምና ዓመተ ምህረቱን ማፃፍ።

- በመጨረሻም ብርሃን በሚያስተላልፍ ፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ አሽጎ በአስፈላጊው ቦታ ማኖር።

የዚህ ዘዴ ጠቀሜታው አንዳንድ በቀላሉ የማይገኙ እፅዋቶችን ወይም በክፍል ውስጥ አምጥቶ ለአስረጂነት ወይም ለማስተማሪያነት ለመጠቀም የማይቻል እፅዋትን፣ የአካል ክፍሉን በማስቀመጥ በሌላ ጊዜ ሲፈለግ በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል።



ሥዕል **3/30** እፅዋትን ወይም የእፅዋት ክፍልን ማንበር **(**ማድረቅ**)**

### **3.3.3** እፅዋቶችን ማሣደግ

| |
|---|
| - ተክሎች ለማደግ ምን ምን ያስፈልጋቸዋል |

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/8**

ዓላማ፡- ችግኝን በእቃ ላይ እንዲበቅል በማድረግ ቀላል የሆነ የተግባር ሙከራ መሥራት።

ለክንዋኔ የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

- አራት በለም አፈር የተሞሉ ጣሳዎች፣
- አንድ ዓይነት የሆኑ ቅጠላማ ችግኞች፣
- በአራቱም ጣሳ ላይ ከ 1-4 ቁጥሮችን ጽፎ መለጠፍ።

የአሠራር ቅደም ተከተል

1. አራቱንም ችግኞች በጣሳዎቹ ውስጥ መትከል።
2. አንድ ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ አየርና የፀሐይ ብርሃን እንዲያገኝ ማድረግ።
3. ሁለት ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ ውሃ እንዳያገኝ ማድረግ።
4. ሶስት ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ በፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ በማድረግ አሸን አየር እንዳያገኝ ማድረግ።
5. አራት ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ የፀሐይ ብርሃን እንዳያገኝ ጨለማ ቦታ (ቁምሣጥን ውስጥ) ማድረግ።
6. ሁለት ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ ካለው ችግኝ በስተቀር ሌሎቹን በመጠኑ ውሃ ማጠጣት።
7. ከአንድ ሣምንት በኋላ የአራቱንም ችግኞች እድገት በማየት ውጤቱን መመዝገብና ሪፖርት ለክፍሉ ማቅረብ።

ተግባራዊ ጥያቄዎች

- ከሙከራው ምን ተገነዘባችሁ□
- ጥሩ ዕድገት እያሣየ ያለው ችግኝ በየትኛው ቁጥር ጣሳ ውስጥ ያለው ነው□
- የጠወለገው (የደረቀው) ችግኝ በየትኛው ቁጥር ጣሳ ውስጥ ያለው ነው□

- ቅጠሎቹ ከአረንጓዴነት ወደ ብጫነት የተቀየሩ ችግኝ በየትኛው ቁጥር ጣሳ ውስጥ የተተከለው ነው?

**3.3.4** እፅዋት ለማደግ ምን ያስፈልጋቸዋል?

ለተክሎች እድገት የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡- አፈር፣ ውሃ፣ አየርና የፀሐይ ብርሃን ናቸው። ተክሎች ለዕድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ ማዕድናትን የሚገኙት ከአፈር ሲሆን በተጨማሪም አፈር የተክሎችን ሥር ጠበቅ አድርጎ በመያዝ ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ይረዳቸዋል።


ውሃ ለተክሎች እድገት በጣም አስፈላጊ ነው። ተክሎች ምግባቸውን ሲያዘጋጁ ከሚያስፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ ውሃ አንዱ ነው። ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀትም ሆነ ያዘጋጁትን ምግብ ለመጠቀም አየር ያስፈልጋቸዋል። ምግባቸውን ሲያዘጋጁ ወደ ውስጥ የሚተነፍሱት አየር ካርቦንዳይኦክሳይድ የተባለ ጋስ ሲሆን ምግባቸውን ካዘጋጁ በኋላ ወደ ውጪ የሚተነፍሱት አየር ደግሞ ኦክሲጂን የተባለ ጋስ ነው።

በተጨማሪም ተክሎች ምግባቸውን ለማዘገጃት የፀሐይ ብርሃን ያስፈልጋቸዋል።

**3.3.5** እፅዋትን ለማሣደግ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮች


ማንኛውንም ተክል (ሰብል) ለማልማት ሲፈለግ የተክሉ ዘር (ፍሬ) የሚዘራበት ወይም ችግኝ የሚተከልበት ቦታ (መሬት) በሚገባ መታረስና መለስለስ አለበት። በተለይ የተክል ችግኝ የሚዘጋጅበትና የጓሮ አትክልቶች ለምሣሌ፡- ጥቅል ጎመን፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ወዘተ ያሉት መደብ ተዘጋጅቶ አፈሩ በሚገባ መለስለስና በመስመር መተከል አለባቸው። በተጨማሪም የአፈሩን ለምነት ለመጠበቅ ማዳበሪያ ወይም ኮምፓስት (ብስባሽና ፍግ) መጨመር አስፈላጊ ነው።

የችግኝ መትከያ ቦታን ቆፍሮ ለማለስለስና መደቦችን ለማዘጋጀት የተለያዩ አነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ፡- መቆፈሪያ፣ መኮትኮቻ፣ ማለስለሻ፣ መስመር ማውጫና ውሃ ማጠጫ ናቸው።



ሀ) ሹል ቅርፅ ያለው ዶማ　　　　ለ) ጠፍጣፋ ዶማ

ሥዕል **3/31** መሬት ለመቆፈርና ለመኮትኮት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች



ሥዕል **3/32** ለመቆፈር፣ በይ ለማውጣትና የችግኝ መደብ ለማዘጋጀት የሚያገለግል መሣሪያ

ከላይ በስዕሉ የምታዩት መሣሪያ ለምን ለምን የሚጠቅም ይመስላችኋል

ይህ መሣሪያ፡-

- ዘር ከመዘራቱ በፊት አፈር ለማለስለስ፣
- እንደ ፍግ ወይም ብስባሽ ያሉ የአፈር ለምነት መጠበቂያ ግብአቶችን ለማዳረስ (ለመበተን) ይረዳል።
- ከተዘራ በኋላ ደግሞ ዘሩን ለመበተንና ዘርዘር ያለ ችግኝ (ቡቃያ) እንዲበቅል ይረዳል።



ሥዕል **3/34** የችግኝ ውሃ ማጠጫ

ውሃ ማጠጫ ውሃውን የሚረጨው በትናንሽ የወንፊት ቀዳዳዎች በኩል ስለሆነ አፈሩ ባለበት ይርሣል አይሸረሸርም።

አትክልትን መንከባከብ

ተክል ተገቢው እንደክብካቤ ከተደረገለት ጥሩ የተክል ውበት ይኖረዋል፣

- ለተክል ሊደረግለት የሚገባው እንክብካቤ ጥዋት ወይም ማታ ውሃ ማጠጣት ምክንያቱም በፀሐይ ሰዓት ካጠጣን ውሃው በፀሐይ ሙቀት ስለሚተን ተክሉ የሚስፈልገውን ያህል ውሃ አያገኝም።
- መኮትኮትና ማረም፡- መኮትኮት ሥር በቂ አየር እንዲኖረው ሲያደርግ ማረም ደግሞ ምግቡን አረም እንዳይሻማው ይረዳል።
- ከበሽታ መጠበቅ የበሽታ ምልክት ከታየ መድሃት መርጨት።

ተግባራዊ ክንዋኔ **3/9**

ዓላማ፡- በትምህርት ቤት ውስጥ ለእፅዋት ማብቂያ የሚሆን ቦታን ሰርቶ ማሣየት

አሠራር፡- በቡድን (5-10) አባላት ያሉበት

ቅደም ተከተል

1. ምቹ ቦታን ከትምህርት ቤቱ አስፈቅዶ መውሰድ፣
2. ቦታውን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣
3. ቦታውን በሚገባ መቆፈርና ማለስለስ፣
4. መደብ ማዘጋጀትና በመደቡ ላይ መስመር ማዘጋጀት
5. የታሰበውን ዘር በመስመሩ መዝራት፣
6. በየጊዜው ውሃ ማጠጣትና ዘሩ ሲበቅል መኮትኮትና ማረም።

መደብ ሲዘጋጅ ሁለት ዓይነት መደብ ማዘጋጀት እንደሚቻል ለተማሪዎች ማወቅ ይገባቸዋል። አንደኛው የመደብ ዓይነት በክረምት ወቅት የሚሰራ ሲሆን የመደቡ ወለል ከፍ ብሎ ዙሪያው መሬት ዝቅ ይላል። ምክንያቱም ውሃ መደቡ ላይ እንዳይተኛ ይረዳል።

ሁለተኛው የመደብ ዓይነት የበጋ መደብ ሲሆን መደቡ ዝቅ ብሎ ዙሪያው መሬት ከፍ ይላል ይሕም ውሃ እንዳይባክን ይረዳል። ማለትም ውሃው ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድ ያደርጋል።

መልመጃ **3.8**

ሀ**.** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ ግለፁ።

1. አፈር ለተክሎች የሚሠጠው ጥቅም ምንድነው
2. ተክሎች ምግባቸውን ካዘጋጁ በኋላ ወደ ውጪ የሚተነፍሱት አየር ምንድነው
3. ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጋቸው አየር ምን ይባላል
4. ለተክሎች ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮች ምንድናቸው
5. አንድ ተክል ከመተከሉ በፊት መደረግ ያለበት ቅድመ ዝግጅት ምንድነው
6. የዘር መዝሪያ ወይም የችግኝ መትከያ ቦታን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን በዝርዝር ግለፁ።
7. አትክልት ውሃ መጠጣት ያለበትን ጊዜና ምክንያቱን ግለፁ።
8. ለአትክልት ዕድገት አስፈላጊ ከሆኑት እንክብካቤዎች ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ።

   1. ________________________________
   2. ________________________________
   3. ________________________________

## **3.4** በአከባቢያችን የሚገኙ እንስሳት

### **3.4.1** እንስሳትን መመደብ

እንስሳት፡- በመራቢያቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገባቸው ሁኔታ፣ በአኗኗራቸውና የሰውነት ሽፋናቸው ይለያያሉ። መመደብ ማለት የነገሮችን አንድነትና ልዩነት መሠረት በማድረግ በጣም የሚመሳሰሉትን በአንድ ላይ (በአንድ ክፍል) የማድረግ ዘዴ ነው።

ሀ**)** የእንስሳት አረባብ

እንስሳት በአረባብ ዘዴያቸው በሁለት ይመደባሉ። እነሱም፡- እንቁላል የሚጥሉና መሰላቸውን የሚወልዱ ናቸው።

እንቁላል የሚጥሉ እንስሳት

እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳት እንቁላል ከሰውነታቸው ውጪ ይጥሉና በእንቁላሉ ውስጥ ያለው “ህዋስ” ወደ አካል ይለወጣል። ከዚያም የእንቁላል ውስጥ ዕድገቱን ሲጨርስ ከእንቁላሉ ይወጣሉ።



ሥዕል **3/34** እንቁላል የሚጥሉ እንስሳት

- በዚህ ሥዕል ውስጥ የሚታዩዋቸው እንስሳት እንቁላላቸውን የት እንደሚጥሉ በእንሰሳቱ ፊት ለፊት በመፃፍ ግለፁ።
- ከነዚህ እንስሳት ውስጥ እንቁላሉ ለሰው ልጅ ምግብነት የሚያገለግለው የየትኛው ነው
- እንቁላሉ ትልቅ የሆነ እንቁላል ጣይ የትኛው ነው

ልጅ የሚወልዱ እንስሳት

ልጅ (መሰላቸውን) የሚወልዱ እንስሳት ህይወት ያለው በአካል ዕድገት አነስተኛ የሆነ መሰላቸውን በመውለድ ጡት በማጥባት ያሳድጓቸዋል። ስለዚህም አጥቢዎች ይባላሉ።




ሥዕል **3/35** መሰላቸውን የሚወልዱ እንስሳት


- ከላይ በተገለፀው ሥዕል ውስጥ
    - ሀ. በራሪ አጥቢ እንስሳ የትኛው ነው?
    - ለ. በውሃ ውስጥ የሚኖሩ አጥቢ እንስሳ የትኞቹ ናቸው?

እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸው መመደብ


እንስሳት ከእፅዋት የሚለዩበት አንዱ ባህሪያቸው ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ መቻላቸው ነው። ይህ እንቅስቃሴ ግን እንደየመንቀሳቀሻ አካላቸው ዓይነትና ቁጥር ይለያያሉ።

ለምሣሌ


- በአራት እግራቸው የሚራመዱ፣
- በሁለት እግራቸው የሚራመዱ፣
- በመዋኘት የሚንቀሳቀሱ፣
- በክንፋቸው የሚበሩ፣
- በደረታቸው መሬት ለመሬት በመሳብ የሚንቀሳቀሱ።



ሥዕል **3/36** በደረታቸው የሚሳቡ እንስሳት



ሥዕል 3/37 የሚበሩ እንስሳት (አእዋፍ)




ሥዕል **3/38** በአራት እግራቸው የሚራመዱ እንስሳት


እንስሳትን በአመጋገብ ባህሪያቸው መመደብ

እንስሳት በአመጋገብ ባህሪያቸው በሶስት ይመደባሉ። እነሱም፡-

1. እፅዋት በል
2. ሥጋ በል
3. እፅዋትና ሥጋ በል ናቸው።



ሥዕል **3/39** እፅዋት በል እንስሳት




**ሥዕል 3/40 ሥጋ በል እንስሳት**




**ሥዕል 3/41 እፅዋትና ሥጋ በል እንስሳት**

? ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንስሳት ከታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ የአመጋገብ ባህሪያቸውን “□” ምልክት በማስቀመጥ ለይታችሁ አሣዩ።

| ተ.ቁ | የእንሰሳው ስም | እፅዋት በል | ሥጋ በል | እፅዋትና ሥጋ በል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ላም | | | |
| 2 | አይጥ | | | |
| 3 | እባብ | | | |
| 4 | ጅብ | | | |
| 5 | ሰው | | | |
| 6 | ቀበሮ | | | |
| 7 | አንበሳ | | | |
| 8 | አሣማ | | | |
| 9 | ግመል | | | |
| 10 | ጥንብ አንሳ | | | |

ሠንጠረዥ 3/7 እንስሳትን በአመጋገብ ባህሪያቸው መለየት

እንስሳትን በአኗኗራቸው መመደብ


እንስሳት ከሚለያዩባቸው መንገዶች አንዱ በመኖሪያ (አካባቢ) ቦታቸው ነው።

ለምሣሌ፡-


- በውሃ ውስጥ የሚኖሩ፡- አሣ፣ አሣነባሪ፣ የውሃ እናት።
- በመሬት ላይ የሚኖሩ፡- ሰው፣ የዱርና የቤት እንስሳት።
- በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ፡- እንቁራሪት፣ አዞ፣ ጉማሬ።

በቤት የሚኖሩ - ለማዳ እንስሳት


በጫካ የሚኖሩ - የዱር እንስሳት



ሥዕል 3/42 በመሬትና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት



ሥዕል 3/43 በውሃ ውስጥ ብቻ የሚኖሩ እንስሳት



ሥዕል 3/44 በመሬት ላይ የሚኖሩ እንስሳት

### መልመጃ 3.9

**መመሪያ ሀ)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. አዞ ከውሃ ውጪ መኖር አይችልም።
2. ዳክዬ የሚትኖረው በውሃ ውስጥ ነው።
3. እንቁራሪት በውሃ ውስጥና በመሬት ላይ መኖር የሚችል እንሰሳ ነው።
4. እባብ በውሃ ውስጥ መኖር ይችላል።

**መመሪያ ለ)** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ አብራሩ።

1. አሣዎች ከውሃ ውጪ መኖር የማይችሉት ለምንድነው
2. በመሬትና በውሃ ውስጥ መኖር የተለየ ጥቅም አለውን
3. የጥያቄ "2" መልሳችሁ አለው ከሆነ እንዴት የለውም ከሆነ ደግሞ ለምን


4. በውሃ ውስጥ የሚኖሩ አሣዎች የሚተነፍሱትን አየር የሚያገኙት ከየት ነው□ አየሩስ ምን ዓይነት ነው (ጋስ ነው ወይስ ፈሳሽ)?
5. እንቁራሪቶች ከመሬት ወደ ውሃ ሲገቡ የሚተነፍሱት እንዴት ነው□

እንስሳትን በቆዳ ሽፋናቸው መመደብ


እንስሳት በቆዳ ሽፋናቸው ይለያያሉ።

እነዚህም፡-


- ቆዳቸው፣ በፀጉር የተሸፈነ፣ በላባ የተሸፈነና በቅርፊት የተሸፈነ ተብለው ይመደባሉ።



ሥዕል **3/45** ቆዳቸው በፀጉር የተሸፈነ እንስሳት



ሥዕል **3/46** ቆዳቸው በቅርፊት የተሸፈነ እንስሳት



ሥዕል **3/47** ቆዳቸው በላባ የተሸፈነ እንስሳት


**3.4.2** የእንስሳት ተዋጽዖ

- ቀደም ሲል እንዳየነው ከሰው ልጅ የምግብ ምንጮች ውስጥ አንዱ እንሰሳ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሰው ከእንስሳት ውጤት ብዙ ነገር ይጠቀማል ወይም ያገኛል።


ከነዚህ የእንስሳት ተዋፅኦዎችም፡-

ለምሣሌ፡-

- ከወተት ተዋፅኦ፣ ቅቤ፣ አይብና እርጎ
- ከቆዳ ሌጦ ጫማ፣ ጃኬት፣ ኮት፣ ቀበቶ፣ ሻንጣ፣ ገንዘብ መያዣ የኪስ ቦርሳ ለመስራት፣
- ከቀንድና ሸሆናቸው የተለያዩ ጌጣጌጦችን፣ የመገልገያ ዕቃዎች (ማንኪያ፣ ጭልፋ፣ መጠጫ ዋናጫ፣ የልብስ ቁልፎችን ለመሥራት፣)
- ከፀጉራቸው፡- የሱፍ ልብሶችን (ሹራቦች፣ ብርድልብስ) ለመሥራት ይጠቀምባቸዋል።
- አጥንታቸውን፡- በመፍጨት - ለአፈር ማዳበሪያ፣ ከሌሎች ምግቦች ጋር በመቀላቀል ለዶሮዎችና ለዓሣ መኖ (ምግብ) ለመሥራት ይጠቀምባቸዋል።



ሥዕል **3/48** ለቆዳና ሌጦ የሚያገለግሉ እንስሳት




ሥዕል **3/49** ለፀጉራቸው የሚፈለጉ እንስሳት

### **3.4.3** ለእንስሳት እርባታ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች

ሁሉም የቤት እንስሳት ለሰው መሰጠት የሚገባቸውን ግልጋሎት መስጠት የሚችሉት በጥንቃቄ ሲያዙና እንክብካቤ ሲደረግላቸው ብቻ ነው። ከእንስሳት መንከባከቢያ ዘዴዎች ውስጥ ጥቂቱ፡-

- በአግባቡ መመገብ፣
- የተስተካከለ፣ ከዝናብና ብርድ የሚከላከል ማደሪያ፣
- በአግባቡ ጤናቸውን ጠብቆ መያዝ ገላቸው ሲቆሽሽ ማጠብ፣ በተለይ የቤት እንስሳት (ውሻ፣ ድመት፣ ላም፣ ፈረስ...) ከሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ስላላቸው በድንገት ቢታመሙ ወደ ሰው ማስተላለፍ ስለሚችሉ ለጤንነታቸው ቅርብ ክትትል ማድረግ በየጊዜው ማሳከም (ማስከተብ)፣

- እንስሳትን አለመተናኮልና አክብሮት መስጠት ናቸው።



ሥዕል **3/50** የቤት እንስሳትን መንከባከብ

ሥዕል **3/51** ለእንስሳት እርባታ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

ማጠቃለያ

ቀስተዳመና፣ ድርቅና የጎርፍ መጥለቅለቅ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ክስተቶች ናቸው።

መወለድ፣ ማደግና መሞት በሁሉም ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚታይ የተፈጥሮ ክስተት ነው።

የተፈጥሮ ሀብት በተፈጥሮ የሚገኝና ለሰው ልጅ ጠቃሜታ መዋል የሚችል ነገር ነው። የሰው ልጅ መገልገያ የሆኑት ዋና ዋናዎቹ የተፈጥሮ ሀብቶች፡- እፅዋት፣ እንስሳት፣ ውሃ፣ አፈር፣ አየር፣ ደንና ማዕድናት ናቸው።

የተፈጥሮ ሀብት ለሰው ልጅ ከሚሰጡት ጥቅም ውስጥ ግምባር ቀደም የሆኑት፡- ለምግብነት፣ ለልብስ፣ ለመጠለያ፣ ለገቢ ምንጭነት፣ ለመጓጓዣ፣ ለመዝናኛ፣ ለቱሪስት መስህብነት፣ የተለያዩ የመገልገያ ቁሳቁሶችንና ጌጣጌጦችን ለመስራት የሚባሉት ተጠቃሾች ናቸው።

ግድ የለሽ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ያስከትላል። ስለዚህ ይህንን ችግር ለመቀነስ፡- በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት፣ ስለተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ህብረተሰቡን ማስተማርና ህብረተሰብ አቀፍ የሆነ የአከባቢ ጥበቃ ሥራን መሥራት አስፈላጊ ነው።

የተፈጥሮ ክስተት በአጋጣሚ (ድንገት) ወይም በዑደት ሰዓትና ጊዜን ጠብቆ በመቀያየር የሚከሰት ነገር ነው።

በአጋጣሚ (ድንገት) የሚከሰቱ የተፈጥሮ ክስተቶች እንደጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ድርቅ፣ ቀስተደመና፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የመሳሰሉ ናቸው። በዑደት ጊዜን

ሰዓት ጠብቀው የሚከሰቱ ደግሞ፡- ቀንና ሌሊት፣ ወቅቶችና የህይወት ምዕራፍ ናቸው።

መለኪያዎች (የልኬት መስፈሪያ) ዘመናዊና ባህላዊ (የተለምዶ) ተብለው በሁለት ይመደባሉ። ዘመናዊ መለኪያ ሜትር፣ ሣንቲሜትር፣ ኪሎ ሜትር፣ ግራም፣ ኪሎ ግራም፣ ሰዓት፣ ደቂቃና ሴኮንድ ናቸው። ባህላዊ መለኪያ እንደሥንዝር፣ እርምጃ፣ ጋሻ፣ ፈረሱላ፣ ቁና የመሣሰሉ ናቸው።

በአከባቢያችን የሚገኙ ነገሮች ህይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸው ተብለው በሁለት ይመደባሉ። ህይወት ያላቸው ደግም እፅዋትና እንስሳት ተብለው በሁለት ይመደባሉ። ህይወት የሌላቸውም እንዲሁ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ተብለው በሁለት ይመደባሉ።

- የተፈጥሮ ሀብት በአከባቢ የሚገኝና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚውል ነገር ነው። የተፈጥሮ ሀብት ለሰው ልጆች ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ውስጥ
    - ለምግብ ምንጭነት፣
    - ለልብስ
    - ለመጠለያ ግንባታ፣
    - ለገቢ ምንጭነት፣
    - ለመጓጓዣ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ካልተደረገለት ለጉዳት ይዳረጋል። ከተፈጥሮ ሀብት የጉዳት ዓይነቶች ውስጥ፡-

- የአየር ብክለት፣
- የውሃ ብክለት፣
- የደን መጨፍጨርና፣
- የአፈር መሸርሸር ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የተፈጥሮ ሀብትን በቤትና በትምህርት ቤት ውስጥ ሣይቀር ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የተክል ክፍል ከመሬት በታችና ከመሬት በላጥ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ከመሬት በታች ያለው ክፍል ሥር ይባላል። ሥር ተራዘምና ድራድር ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

ግንድ ከመሬት በታች ያለውንና ከመሬት በላይ ያለውን የተክል ክፍል የሚያገናኝ ነው። ግንድ እንጨት ያለውና ሣር ያለው ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

ቅጠል የተክሉን ምግብ የሚያዘጋጅ የተክል ክፍል ነው። አበባ ደግሞ የተክሉን ዘርፍ ፍሬ የሚያፈራ የተክል ክፍል ነው።

ተክልን ወይም የተክል ክፍልን (ቅጠል፣ ግንድና ሥር) ለረጅም ጊዜ ሣይበላሽ እንዲቆይ የማድረግ ዘዴ ማንበር ይበላል።

ለተክል ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ውሃ፣ አየር፣ የፀሐይ ብርሃንና አፈር ናቸው።

የችግኝ መትከያ ወይም የዘር መዝሪያ ቦታን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የእጅ መሣሪያዎች መቆፈሪያ፣ መኮትኮቻ፣ ማለስለሺያና ውሃ ማጠጫ ናቸው።

እንስሳት በመዋለጃቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በአኗኗራቸውና በሰውነት ሽፋናቸው ተለይተው ይመደባሉ።

የእንስሳት እርባታ በአግባቡ መመገብንና ጤንነታቸውን ጠብቆ መያዝን ይፈልጋል።

# ክፍለ ትምህርት አራት

## 4. ወረዳችን /ክፍለ ከተማችን/

- ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ ምንድን ነው?
- በወረዳና በቀበሌ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ቁልፍ ቃላት

- ቀበሌ
- ወረዳ/ክፍለ ከተማ

በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሰዎች መንደሮችን ይመሰርታሉ። መንደሮችም በአንድነት ሆነው ቀበሌ ይመሰርታሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ አጎራባች የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች በአንድነት ሆነው ወረዳን ይመሰርታሉ። በትልልቅ ከተሞች ቀበሌዎች በአንድነት ሆነው ክፍለ ከተማን ይመሰርታሉ። ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ ከቀበሌ ቀጥሎ የሚገኝ መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ነው።

? ትምህርት ቤታችሁ የሚገኝበት ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ ስም ምን ይባላል?

### 4.1. የወረዳችን አቅጣጫዎች

ቁልፍ ቃላት

- አቅጣጫ
- አቀማመጥ
- ታሪካዊ ቦታዎች

#### 4.1.1. አራቱ አቅጣጫዎች

- ስንት ዋና ዋና አቅጣጫዎች አሉ? ስማቸውን ጥቀሱ።
- ፀሀይ በየትኛው አቅጣጫ ትወጣለች?


አበይት ወይም ዋና ዋና አቅጣጫዎች የምንላቸው አራት ናቸው። እነሱም፡-

1. ምስራቅ
2. ምዕራብ

3. ሰሜንና

4. ደቡብ በመባል ይታወቃሉ።

- ምስራቅ ፀሀይ ጠዋት የምትወጣበት አቅጣጫ ነው።
- ሰሜን ፊታችንን ወደ ምስራቅ ስናዞር በስተግራ የሚገኘው አቅጣጫ ነው።
- ደቡብ ፊታችንን ወደ ፀሀይ መውጫ ስናዞር በስተቀኝ የምናገኘው አቅጣጫ ነው።
- ምዕራብ ማታ ፀሀይ የምትጠልቅበት አቅጣጫ ነው።
- ወደ ማታ ፊታችንን ወደ ፀሀይ መግቢያ ወይም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ስናዞር ሰሜን በስተቀኝ፣ ደቡብ በስተግራ፣ ምስራቅ በስተኋላችን ይገኛል።




ሥዕል 4/1 አራቱ አበይት አቅጣጫዎች

በክፍል ውስጥ ተራ በተራ በመነሳት አቅጣጫዎችን ሰሜን፣ደቡብ፣ምዕራብና ምስራቅ በማለት ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ።

### 4.1.2. የወረዳችን አቀመቀመጥ ከሌሎች አዋሳኝ ወረዳዎች ጋር ሲታይ


- ከወረዳችሁ በስተሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ ያሉትን ተፈጥሮአዊ አዋሳኞች ስም ተናገሩ።
- ወረዳችሁን የሚያዋስኑ ወረዳዎችን ስም ተናገሩ።
- ወረዳችሁን የሚያዋስን የውሃ አካል አለ? ካለ ተናገሩ።

በአቅራቢያችሁ የሚገኙ ቦታዎችን መገኛ ለመግለፅ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ትችላላችሁ። በዚህም መሰረት በአንድ ቦታ ቆመን ወይም ተቀምጠን የተለያዩ ነገሮችን ከፊቴ፣ ከኋላዬ፣ ከግራዬ፣ ወይም ከቀኜ በማለት መገኛቸውን መግለፅ ወይም ማመልከት ይቻላል።

? በመቀመጫችሁ ላይ እንደተቀመጣችሁ ከግራችሁ፣ ከፊታችሁ፣ ከቀኛችሁና ከኋላችሁ እነማን እንደተቀመጡ ስም እየጠራችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ከላይ በተገለፀው ሁኔታ አንድ ነገር ከሌሎች ነገሮች ሲነፃፀር የሚገኝበት ቦታ ወይም አቅጣጫ አንፃራዊ መገኛ ይባላል። በዚህ ዓይነት በወረዳችሁ ዙሪያ የሚገኙ ታዋቂ ነገሮችን መነሻ በማድረግ አንፃራዊ መገኛውን ለማመልከት ሞክሩ።

አንፃራዊ መገኛ የሚገለፀው በአካባቢያችን በሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች ነው። ተፈጥሮአዊ የምንላቸው እንደ ተራራ፣የውሀ አካላት/ወንዝና ሀይቅ/ በመሳሰሉት ሲሆን ሰው ሰራሽ ደግሞ እንደ ትልልቅ መስሪያ ቤቶች፣አጎራባች ወረዳዎችና የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህ በታች የሚገኘው ሥዕል /ካርታ/ በደቡብ ክልል የሚገኙ ወረዳዎችን ያሳያል።




ሥዕል 4/2 የወረዳዎች አንፃራዊ መገኛ

- ከላይ በሥዕሉ የተገለፁትን ወረደዎች አንፃራዊ መገኛ ተናገሩ።
- የወረዳችሁ ወይም የክፍል ከተማችሁን አንፃራዊ መገኛ ተናገሩ።

### **4.1.3.** በወረዳችን የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች

ከብዙ ዓመታት በፊት አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተከናወኑባቸው ቦታዎች ሁሉ ታሪካዊ ስፍራዎች ይባላሉ። የቀደምት ሰዎች መኖሪያ የነበሩ ዋሻዎች፣መሰብሰቢያ አደባባዮች፣ የጦር ሜዳዎች፣ የአምልኮ ስፍራዎች፣ ቤተ መንግስታትና የመሳሰሉት ታሪካዊ ስፍራዎች የህዝቦችን ታሪክ ያንፀባርቃሉ።

በወረዳችሁ ውስጥ ታሪካዊ ስፍራዎች አሉ? ካሉ ስማቸውንና የሚገኙበትን ቀበሌ ስም በመጥቀስ ለመምህራችሁ ግለፁ።

መልመጃ **4/1**

መመሪያ ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን ዓረፍተ ነገር እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. ፀሀይ የምትወጣው በስተደቡብ አቅጣጫ ነው።
2. ፀሀይ የምትጠልቀው በስተሰሜን አቅጣጫ ነው።
3. ምዕራብ ፀሀይ የምትጠልቅበት አቢይ አቅጣጫ ነው።
4. በአንድ አካባቢ የሚገኙ መንደሮች በአንድነት ሆነው ቀበሌ ይመሰርታሉ።
5. ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ ከቀበሌ ቀጥሎ የሚገኝ መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ነው።

መመሪያ ለ. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ።

1. ________ፊታችንን ወደ ምስራቅ ስናዞር በስተግራ የምናገኘው አቅጣጫ ይባላል።
2. ________ፊታችንን ወደ ፀሀይ መውጫ ስናዞር በስተቀኝ የምናገኘው አቅጣጫ ይባላል።
3. ________ማታ ፀሀይ የምትጠልቅበት አቅጣጫ ይባላል።
4. በአንድ አካባቢ የሚገኙ ቀበሌዎች በአንድነት ሆነው______ይመሰርታሉ።

መመሪያ ሐ. በአጭሩ መልስ ስጡ።

1. አበይት አቅጣጫዎችን ዘርዝሩ።

   ሀ.________________________

   ለ.________________________

   ሐ.________________________

   መ.________________________

2. የወረዳችንን አንፃራዊ መገኛ እንዴት መግለፅ እንችላለን?______________
   ______________________________________________________________
   _______


3. ታሪካዊ ቦታዎች የሚባሉት ምን ዓይነት ቦታዎች ናቸው?______________
   ______________________________________________________________
   _______

## 4.2. የወረዳችን መሬት አቀማመጥ


| |
|---|
| ▪ የወረዳችሁ የመሬት አቀማመጥ ምን ዓይነት ነው? |

**ቁልፍ ቃላት**

**- አቀማመጥ - ገፅታ - ሜዳ - ተራራ - ፕሎቶአማ - ሸለቆ**



ሥዕል **4/3** ተራራማ መሬት



ሥዕል **4/4** ሸለቆማ ቦታዎች



ሥዕል **4/5** ሜዳማ ቦታዎች

(?) ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በመመልከት የተለያዩ የመሬት አቀማመጦችን ስም ተናገሩ።

በምድር ላይ የተለያዩ ተፈጥሮአዊ አቀማመጦች አሉ። እነሱም ተራራ፣ ሸለቆ፣ ኮረብታ፣ ሜዳና የመሳሰሉት ሲሆኑ ተራራ ከኮረብታ የበለጠ ከፍታ ያለው የመሬት አካል ነው።


ከተራራ ላይ ዝናብ ሲዘንብ አፈሩ እየተሸረሸረ ወደ ሜዳ ወይም ሸለቆ ውስጥ ይወርዳል። ሜዳ ልጆች ኳስ የሚጫወቱበትና አዋቂዎች ፈረስ የሚጋልቡበት ለጥ ያለ የመሬት አቀማመጥ ነው። ሸለቆ በሁለት ከፍታ ቦታዎች መካከል የሚገኝ ዝቅተኛ ስፍራ ነው።

የወረዳችንን መሬት ስንመለከት ለጥ ያለ ሰፊ መሬት፣ ከአካባቢው በጣም ከፍ ብሎ የሚታይ መሬት ወይም ከፍተኛና ጠፍጣፋ ቅርፅ ያለውን መሬት እናገኛለን። የአንድ ወረዳ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ እነዚህን የመሬት ቅርፅ ሁኔታዎች ያመለክታል። የተለያዩ የመሬት አቀማመጥ ሁኔታዎችን ለመግለፅ የምንጠቀምባቸው የተለመዱ ስያሜዎች አሉ። እነሱም፡-

- ለጥ ያለና ሰፊ መሬት ያለበትን አካባቢ- ሜዳ
- ከአካባቢው በጣም ከፍ ብሎ የሚታይ መሬት- ተራራ
- ከፍተኛና ጠፍጣፋ ሆኖ ደልዳላ የሆነ መሬት- ፐሎቶአማ
- በውሃ የተቦረቦረና ረዥም ጉድጓድ ዓይነት ቅርፅ ያለው መሬት- ሸለቆ ብለን እንጠራለን።

በዚህም መሰረት የአንድ ወረዳ ተፈጥሮአዊ የመሬት አቀማመጥ በውስጡ የሚገኙትን ተራሮች፣ ሜዳዎች፣ ፐሎቶአማ መሬቶችንና ሸለቆችን ሁኔታ ያመላክታል።

(?) ከላይ ከተጠቀሱት የመሬት ቅርፆች መካከል የወረዳችሁን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ በይበልጥ የሚገልጹት የትኞቹ ናቸው?



ሥዕል 4/6 የመሬት ተፈጥሮአዊ ገፅታዎች

## **4.2.2.** የመሬት አቀማመጥ ገጽታዎች

በወረዳችን የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እንደሚገኙ ተመልክተናል። እነዚህን የተለያዩ መልክዓ ምድሮችን ስንመለከት የተለያዩ የመሬት ገጽታዎችን እናገኛለን።

የወረዳችን የመሬት ገጽታ በደን የተሸፈነ፣በውሃ የተያዙ መሬቶችና በውሃ የተሸረሸሩ እንዲሁም የተራቆቱ መሬቶች ብለን መግለጽ እንችላለን።

መሬቱ በብዛት በበቀሉ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ካሉት በደን የተሸፈነ ይባላል። ደን በተፈጥሮ የሚገኝ ወይም ሰው የተከለው ሊሆን ይችላል። በደን የተሸፈነ መሬት ውበት አለው። ነፋሻማ አየር ይኖረዋል። አብዛኛውን ጊዜ የዱር አራዊት ስለሚገኙበት ለመዝናኛነት ያገለግላል።

ዕፅዋት አልባ መሬት የተራቆተ መሬት ይባላል። እንደዚህ ዓይነት መሬት ለጎርፍ ስለሚጋለጥ አፈሩ ይሸረሸራል። ከዚያም ዕፅዋትን ማብቀል አይችልም። በተጨማሪም በዕፅዋት ያልተሸፈነ መሬት ውበት የለውም።

ሌሎች በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ የመሬት ገፅታዎች ደግሞ የውሃ አካላት ናቸው። የውሃ አካላት የምንላቸው ወንዝ፣ሀይቅ፣ ባህር፣ ውቅያኖስና የመሳሰሉት ናቸው። ወንዝ ከከፍተኛ ቦታ ተነስቶ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚፈስ የውሃ አካል ነው። ሀይቅ በሰፊ ቦታ ላይ የተኛ የውሃ አካል ነው። ባህርና ውቅያኖስ በሃገራችን አይገኙም። ባህርና ውቅያኖስ የሚባሉት ከሀይቅ የሚሰፉ ብዙ የምድርን ክፍል የሸፈኑ የውሃ አካላት ናቸው። በውሃ አካላት ውስጥ በርካታ የሆኑ ህይወት ያላቸው እንስሳት ይገኛሉ። እነሱም አሳ፣ ጉማሬ፣ አዞ፣ አሳ ነባሪና የመሳሰሉት ናቸው። በውሃ አካል ከሚገኙ እንስሳቶች ውስጥ አሣን የሰው ልጆች ለምግብነት ይጠቀሙበታል።

- ከላይ ከተጠቀሱት የመሬት ገጽታ መካከል የወረዳችሁን ተፈትሮአዊ ገፅታ የሚገልፀው የትኛው እንደሆነ ለመምህራችሁ ንገሩ።
- በፕላስቲክ ጭቃ ወይም በሸክላ ጭቃ በቡድን በመሆን የወረዳችሁን ካርታ እንዴት መስራት እንደምትችሉ መምህራችሁን በመጠየቅ ለመስራት ሞክሩ። በካርታውም የመሬት አቀማመጡንም አሳዩ።

## መልመጃ 4/2

መመሪያ ሀ፡- የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን ዓረፍተ ነገር እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. ተራራ ከኮረብታ አነስ ያለ ከፍታ ያለው የመሬት አካል ነው።
2. ሸለቆ በሁለት ከፍታዎች መካከል የሚገኝ ዝቅተኛ ስፍራ ነው።
3. መሬቱ በብዛት በበቀሉ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ካሉት በደን የተሸፈነ ይባላል።

መመሪያ ለ፡- በሚከተሉት ክፍት ቦታዎች ላይ ትክክለኛውን ቃል ሙሉ።

1. ለጥ ያለና ሰፊ መሬት ያለበት አካባቢ ______________________ ይባላል።
2. ከፍተኛና ጠፍጣፋ ሆኖ ደልዳላ መሬት _____________________________ይባላል።
3. በአከባቢያችሁ በጣም ከፍ ብሎ የሚታይ መሬት ______________ይባላል።
4. በውሃ የተቦረቦረ ረዥም ጉድጓድ ዓይነት ቅርጽ ያለውን መሬት ______________ ብለን እንጠራለን።

መመሪያ ሐ፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

1. እፅዋት አልባ መሬት ምን ተብሎ ይጠራል
2. የውሃ አካላት የምንላቸውን የመሬት ገጽታዎች ዘርዝሩ።

## 4.3 በወረዳችን የሚገኙ መስሪያ ቤቶች

| በወረዳችሁ ወይም ክፍለ ከተማችሁ የሚገኙት መስሪያ ቤቶች ስማቸውን ዘርዝሩ። |
|---|

ቁልፍ ቃላት

- ማዕድን
- ሰብአዊ
- ግብረሰናይ
- ኢንዱስትሪ

### 4.3.1 መሥሪያ ቤቶች

ህዝቦች በአንድ ላይ በመሆን ቀበሌና ወረዳ እንደሚመሰርቱ በክፍለ ትምህርቱ መግቢያ ላይ ተምረናል። ወረዳ ከቀበሌ ቀጥሎ የሚገኝ መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን እንደሆነም ተወያይተናል።

መስሪያ ቤቶች የምላቸው ለወረዳው ህዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሥራዎችን ለመሥራት የተመሰረቱ ናቸው።

በወረዳው ውስጥ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የግል ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የእምነት ተቋማት ይገኛሉ።

- በወረዳችሁ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የትኞቹ ናቸው
- በወረዳችሁ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የምንላቸው የትኞቹ ናቸው
- በወረዳችሁ ውስጥ የግል ድርጅቶች የምንላቸው የትኞቹ ናቸው
- በወረዳችሁ ውስጥ የሀይማኖት ተቋማት የትኞቹ ናቸው

የመንግስት መስሪያ ቤቶች

ለወረዳው ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ልዩ ልዩ ስራዎች ለመስራት የተመሰረቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አሉ።

ምሣሌ፡-

- የወረዳው የትምህርት ጽ/ቤት - የወረዳው የትምህርት ስራዎችን በኃላፊነት ይመራል።

- የግብርናና ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ዋና ጽ/ቤት - የወረዳውን የግብርና፣ የገጠር መንገድ፣ የውሃና ማዕድን ዘርፍ ሥራዎችን በኃላፊነት የሚመራ መስሪያ ቤት ነው።

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚባሉት ለህብረተሰቡ ሰብዓዊ እርዳታ ለመስጠትና የልማት ሥራዎችን ለመሥራት የተቋቋሙ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችና ሌሎች በማህበረሰብ አካላት የሚቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው።

ምሣሌ፡-

- አክሽንኤይድ፣ ኢየሩሳሌም የህፃናትና የማህበረሰብ ልማት፣ ሚሪጆይ ድርጅት፣ ወዘተ

የግል ድርጅቶች

የግል ድርጅቶች የሚባሉት ግለሰቦች በግል ወይም በቡድን ያቋቋሟቸው እንደ ሆቴል፣ ፋብሪካ፣ ኢንዱስትሪ፣ የሸቀጣሸቀጥ መደብሮችና የመሳሰሉት ናቸው።

የእምነት ተቋማት

የእምነት ተቋማት የምንላቸው ለህብረተሰቡ አምልኮታዊ ተግባራትን የሚያከናውኑባቸው ተቋማት ናቸው። እነሱም ቤተክርስቲያን፣ መስጊድና የመሳሰሉትን የአምልኮ ስፍራዎችን ያመለክታሉ።



ሥዕል 4/7 የእምነት ተቋማት

### 4.3.2 የመሥሪያ ቤቶች ተግባር

| |
|---|
| በወረዳችሁ ውስጥ ማን ምን ይሰራል□ ለመምህራችሁ ንገሩ። |

የወረዳ አስተዳደር

የወረዳ አስተዳደር ለወረዳ ህዝብ ልማት፣ ሠላም፣ ደህንነትና ፍትህ የሚሰራ የመንግስት መዋቅር ነው። የወረዳ አስተዳደር የተለያዩ የአስተዳደር አካላትና በምርጫ የሚወከሉ የህዝብ ተወካዮችና መሪዎች ይኖሩታል።

(?) - የህዝብ ተወካዮችና መሪዎች የሚመረጡት በማን ነው? የምርጫው ሂደትስ እንዴት እንደሆነ ታውቃላሁች? መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።



ሥዕል 4/8 ህዝቡ ተወካዮቹን ለመምረጥ ድምፅ ሲሰጥ

የወረዳ የአስተዳደር አካላት ፖሊስ፣ ፍርድ ቤትና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ናቸው። እነዚህ የአስተዳደር አካላት በህግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት አላቸው። ከሚያከናውኗቸው ተግባራትም ዋና ዋናዎቹን እንመልከት።

ፖሊስ

| የፖሊስ ሥራ ምንድ ነው? ለመምህራችሁ ንገሩ። |
|---|

የአንድ ወረዳ ፖሊስ እጅግ በርካታ ተግባራት አሉት። ከእነሱም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- በህብረተሰቡ ውስጥ ወንጀል እንዳይፈፀም ይከላከላል።
- ወንጀል ፈፅሞ የተደበቀ ወንጀለኛን አድኖ በመያዝ፣ በህግ ቁጥጥር ስር እንዲውል ያደርጋል።
- ወንጀልን መርምሮና አጣርቶ ለፍርድ ቤት ያስተላልፋል።

- በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ሰላም፣ ደህንነትና ፀጥታ እንዲከበር ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ በመሆን ይሰራል።

? እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ወንጀል ሲሰራ ብትመለከቱ ለማን መጠቆም እንዳለባችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።

ፍርድ ቤት

| የፍርድ ቤቶች የስራ ድርሻቸው ምንድነው? ለመምህራችሁ ንገሩ። |
|---|

ፍርድ ቤቶች በርካታ ተግባሮችን ያከናውናሉ። ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቱ፡-

- ለወንጀል ድርጊቶች የቅጣት ውሳኔ ይሰጣሉ።
- ለተለያዩ የክርክር ጉዳዮች የዳኝነት ብይን ይሰጣሉ።

## መልመጃ 4/3

መመሪያ ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ፖሊስ ወንጀልን አጣርቶ ለፍርድ ቤት የማስተላለፍ ስልጣን አለው።
2. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚባሉት ለህብረተሰቡ ሰብአዊ እርዳታ ለመስጠት የተቋቋሙ ግብረሰናይ ድርጅቶች ናቸው።
3. የወረዳ አስዳደር የተለያዩ የአስተዳደር አካላት በምርጫ የሚወከሉ የህዝብ ተወካዮችና መሪዎች ይኖሩበታል።
4. መስጊድ የእምነት ተቋም ነው።
5. ኢየሩሳሌም የህፃናትና የማህበረሰብ ልማት ድርጅት የመንግስት መስሪያ ቤት ነው።

መመሪያ፡- ለ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የመንግስት መስሪያ ቤት የትኛው ነው፧
   ሀ. አክሽን ኤይድ ለ. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት
   ሐ. ሆቴል መ. ቤተክርስቲያን
2. ከሚከተሉት ውስጥ የግል ድርጅት የምንለው የትኛው ነው፧
   ሀ. ሆቴል ለ. ሚሪጆይ
   ሐ. ቤተክርስቲያን መ. የወረዳ ገጠር ልማት ማስተባበሪያ
3. ከሚከተሉት ውስጥ የፖሊስ የስራ ድርሻ ያልሆነው የቱ ነው፧
   ሀ. በህብረተሰቡ ውስጥ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል
   ለ. ወንጀል ፈፅሞ የተደበቀ ግለሰብን አድኖ መያዝ
   ሐ. ለወንጀል ድርጊቶች የቅጣት ውሳኔ መስጠት
   መ. የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ መጠበቅ፣
4. በወረዳ አስተዳደር ውስጥ የማይካታተው የትኛው ነው፧
   ሀ. ፖሊስ ለ. የእምነት ተቋማት
   ሐ. ፍርድ ቤት መ. የመንግስት መስሪያ ቤት
5. _________ የወረዳው የትምህርት ስራዎችን በኃላፊነት ይሰራል።
   ሀ. ትምህርት ጽ/ቤት ለ. ጤና ጽ/ቤት
   ሐ. የገጠር ልማት ማስተባበሪያ መ. መልሱ አልተሰጠም

6. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለተለያዩ የክርክር ጉዳዮች የዳኝነት ብይን ይሰጣል።

ሀ. ጤና ጽ/ቤት ለ. ፍርድ ቤት

ሐ. ፖሊስ ጽ/ቤት መ. የወረዳ አስተዳደር

መመሪያ ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ ስጡ።

1. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስራ ድርሻ ምንድነው

2. የግል ድርጅቶች የምንላቸውን ዘርዝሩ።


3. የሀይማኖት ተቋማት የምንላቸውን ዘርዝሩ።

## 4.4 የወረዳው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

ቁልፍ ቃላት

- ስራ
- እድገት
- ኢኮኖሚ
- ቴክኖሎጂ

- በቤታችሁ የእናንተ ተግባር ምንድነው ለመምህራችሁ ንገሩ።
- ቤተሰቦቻችሁ በምን ዓይነት ሥራ ላይ እንደተሰማሩ ለመምህራችሁ ግለፁ።
- በወረዳችሁ የሚገኙ ሰዎች ምን ዓይነት ስራዎችን እንደሚሰሩ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።
- ስራ መስራት ለምን እንደሚጠቅም ወላጆቻችሁን በመጠየቅ የሚነግሩአችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው።




ሥዕል 4/9 የተለያዩ የስራ መስኮች

## 4.4.1 የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

ግብርና

| |
|---|
| በወረዳችሁ ሰዎች እርሻ ሲያርሱ አስተውላችኋል□ ከብትና ፍየል የሚያረቡ ሰዎችን ዓይታችሁ ታውቃላችሁ□ |

በእርሻ ወይም በከብት እርባታ ሙያ የተሰማራ ሰው ገበሬ ይባላል። ገበሬው እርሻውን በማረስ የተለያዩ ምርቶችን ያመርታሉ። ገበሬው መሬት ከማረስ በተጨማሪ ከብቶችን ያረባል።



ሥዕል 4/10 የግብርና ሙያ

? በአከባቢያችሁ ከሚኖረው ህዝብ አብዛኛው የሚኖረው በከተማ ነው ወይስ በገጠር□

አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ የሚኖረው በገጠር ነው። አብዛኛው የገጠር ህዝብ ኑሮው የተመሰረተው በግብርና ላይ ነው።
ገበሬው መሬት በማረስና በማምረት ለራሱና በከተማ ለሚኖሩ ህብረተሰብ ለምግብ የሚሆኑ ምርቶችን ያቀርባል።

? በአከባቢችሁ ምን አይነት የምግብ ሰብሎች እንደሚመረቱ ዘርዝሩ።
እነዚህ የምግብ ሰብሎች ከየት እንደሚገኙ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

በተለያዩ አከባቢዎች የሚኖሩ ገበሬዎች የተለያየ ሰብሎችን ያመርታሉ። በአንዳንድ አካባቢ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ የመሳሰሉትን ሲያመርቱ በሌላ አካባቢ ስንዴ፣ ገብስ፣ ዘንጋዳና የመሳሰሉትን ሰብሎች በማምረት ገቢ ያገኛሉ።

ገበሬው መሬቱን አርሶ ከሚያገኘው ምርት ለራሱ የሚበቃውን ከተጠቀመ በኋላ ሌላውን ገበያ ያወጣና ይሸጣል። በሚያገኘው ገንዘብ ልብስና ለኑሮ የሚያስፈልጉትን እንደ ጨው፣ ስኳር፣ ዘይትና የመሳሰሉትን ይገዛል።


- በአከባቢያችሁ ገበሬው ለምግብነት ከሚውሉት ሌላ ምርቶችን ያመርታል□
- በቤት ውስጥ ለምግብነት የምንጠቀምባቸው ዘይትና ስኳር ከምን ይሰራሉ□
- ዘመናዊ የቆዳ ጃኬቶችና ጫማዎች ከምን የሚሰሩ ይመስሏችኋል□ እስኪ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።
- የለበሳችሁት ልብስ ከምን የተሰራ ይመስላችኋል□

በፋብሪካ የሚሰሩና ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ ምርቶች አብዛኞቹ ከግብርና በሚገኙ ጥሬ ነገሮች የተሰሩ ናቸው።

ጥጥ የግብርና ውጤት ነው። ገበሬው እርሻ በማረስ ጥጥ ያመርታል። ሰብስቦ ለፋብሪካ ይሸጣል። ነጋዴው ከገበሬው በመግዛት ሰብስቦ ለፋብሪካ ይሸጣል። ፋብሪካ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ጥጡ ወደ ጨርቅነት ይ ቀየራል።

የሸንኮራ አገዳ የግብርና ውጤት ነው። ፋብሪካ ውስጥ ገብቶ ተቆርጦ ከተጨመቀ በኋላ የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ ወደ ስኳርነት ይቀየራል።

ከብት ማርባት የግብርና ዘርፍ ነው። ገበሬው ከብቱን ገበያ አቅርቦ እንደሚሸጥ ተምረናል። የተሸጠው ከብት ታርዶ ሥጋው ለምግብነት ይውላል። ቆዳው ደግሞ ፋብሪካ ውስይ ይገባና ዘመናዊ ቆዳ ጫማ፣ ጃኬትና ቦርሳ ይሰራበታል።




ሥዕል 4/11 የቆዳ ውጤቶች

ገበሬው ከምግብ ሰብሎች በተጨማሪ አተር፣ ባቄላ፣ ሽንኮራ፣ በሎቄ፣ የመሳሰሉ ጥራጥሬዎችን ጎመን፣ ሽንኩርት፣ ድንች፣ ቆስጣ፣ ካሮት፣ ቲማቲም፣ የመሳሰሉ አትክልቶችንና ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ማንጎ፣ አቮካዶና የመሳሰሉ ፍራፍሬዎችን በመትከል ለምግብነት ተጠቅሞ ቀሪውን ለገበያ ያቀርባል።

በገበያ ቀን ገበሬው ከእህል በተጨማሪ በሬ ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ የመሳሰሉትን ወደ ገበያ ሲያመጣ አስተውላችኋል

ከብት ማርባት የግብርና ሙያ አካል ነው። እርሻ ከማረስ ጎን ለጎን ከብት እያረቡ የሚኖሩ ሰዎች አሉ። ሰፊ የግጦሽ መሬቶች ባሉባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች በአብዛኛው ከብት እያረቡ ብቻ ይኖራሉ። ከብት ብቻ እያረቡ የሚኖሩ ሰዎች አርብቶ-አደር በመባል ይታወቃሉ።

? ከብት ብቻ እያረቡ የሚኖሩ ሰዎች በአከባቢያችሁ አሉ  እስኪ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ተወያዩ።




ሥዕል 4/12 ለምግብነት የሚሆን የግብርና ውጤቶች



ሥዕል 4/13 አርብቶ አደር

የግብርና ውጤቶች ለምግብነት ከሚሰጡት ጠቀሜታ በተጨማሪ ለኢንዱስትሪው ምርት በጥሬ ዕቃነት ያገለግላል።

በግብርናው ዘርፍ የሚመረቱ ምርቶች በኢንዱስትሪው ክፍል ስለሚፈለጉ ገበሬዎች ሸጦ ከፍተኛ ገንዘብ ያገኛሉ። የኢንዱስትሪው ውጤት የሆኑትን ገዝቶ በመጠቀም የተሻለ ኑሮ መኖር ይችላሉ።

? ብዙ ፋብሪካዎች ቢከፈቱ ለገበሬው ምን ጥቅም እንደሚሰጡ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ የነገሩአችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

ንግድ

| |
|---|
| ደብተርና እስክሪብቶ የሸጠላችሁ ማን ነው□ |
| የወረዳችሁ የገበያ ቀን መቼ እንደሆነ ታውቃላችሁ□ |

በገበያ ቀን ገበሬ ያመረተውን እህል ለነጋዴ ይሸጣል። ነጋዴውም ከገበሬው የገዛውን እህል መልሶ ለበላተኛ ይሸጣል። ከፋብሪካ የተመረቱ ዕቃዎችን ባለሱቅ ይገዛና መልሶ ለሚጠቀሙ ሰዎች ይሸጣል።

በርካታ የንግድ ሥራ መስኮች አሉ። ሰዎች በተለያዩ መስኮች በመሰማራት ራሳቸው ያስተዳድራሉ። ለአከባቢው ህብረተሰብም ግልጋሎት ያበረክታሉ።




## ሥዕል **4/14** የንግድ ሥራ መስኮች

- በአከባቢያችሁ የምታውቋቸውን የንግድ ዘርፎች ተናገሩ።
- በአከባቢያችሁ አብዛኛው ሰው ተሰማርቶ የሚኖረው በየትኛው የንግድ ሥራ ነው?
- የንግድ መስኩ ለአከባቢው ነዋሪ ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ?
- በንግድ ሥራ የተሰማሩ ሰዎች ለራሳቸው ምን ጥቅም እንደሚያገኙና ለአከባቢውም ነዋሪ ምን አይነት አገልግሎት እንደሚያበረክቱ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

*መጓጓዣ*


- የምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በምን ይጓጓዛሉ?
- በገበያ ቀን ሰዎች እህል ከገጠር ወደ ከተማ በምን እንደሚያመጡ አስተውላችኋል?
- ወላጆቻችሁ ከባድ እቃ ከአንድ ቦታ ወደ ቤት በምን ያመጣሉ።



ሥዕል 4/15 የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶች

- ከላይ በሥዕሉ የምትመለከቷቸው ምን አገልግሎት ይሰጣሉ
- በገጠር የሚኖሩ ሰዎች ከገጠር ወደ ከተማ በምን ይመጣሉ

በገጠር የሚኖሩ ሰዎች ከሩቅ ቦታ ያለ ዘመድ ለመጠየቅ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ። የሚሄዱበት ቦታ የመኪና መጓጓዣ የሌለበት ከሆነ በቤት እንስሳት ላይ ተቀምጠው ይሄዳሉ። ፈረስ፣ አህያና በቅሎን ለመጓጓዣነት ይጠቀማሉ።




ሥዕል **4/16** የመኪና ትራንስፖርት

- በአከባቢያችሁ ሰዎች በሰፊው የሚጠቀሙበት የመጓጓዣ አይነት የትኛው ነው
- በአከባቢያችሁ የገጠሩ ነዋሪ የሚጠቀመው የትኛውን የመጓጓዣ አይነት ነው

ኢንዱስትሪ

- በአከባቢያችሁ የሚገኝ ኢንዱስትሪ (ፋብሪካ) አለ□ ካለ ለመምህራችሁ ንገሩ።




ሥዕል **4/17** የኢንዱስትሪ ውጤቶች

አብዛኛው ኢንዱስትሪዎች ጥሬ እቃዎችን ከግብርና ውጤቶች ያገኛሉ። ይህንን ከግብርና ያገኙትን ጥሬ ዕቃ ለአጠቃቀም እንዲመች በማድረግ አሻሽለው ለገበያ ያቀርባሉ።


ለምሣሌ፡- የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ጥጥን እንደ ጥሬ እቃ ይጠቀማል። ይህም ሲባል ጥጥን ተጠቅሞ ወደ ልብስነት ይቀይራል ማለት ነው።

ኢንዱስትሪ በአንድ አገር ውስጥ በብዛት መገኘታቸው የእድገት ምልክት ነው። አንድ አገር አደጋ የሚባለው በርካታ ኢንዱስትሪዎች ሲኖሩት ነው። ኢንዱስትሪዎች በርካታ የሆኑ ሰዎችን በውስጣቸው ቀጥረው ያሰራሉ። ስለዚህ ኢንዱስትሪዎች ለበርካታ ሰዎች የስራ እድል ይፈጥራሉ።

ዘመናዊ ልብስ በፋብሪካ ውስጥ ይሰራል። ልብስን የሚሰራ ፋብሪካ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በመባል ይታወቃል።

(?) በአከባቢያችሁ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ አለ□ ካለ ለመምህራችሁ ንገሩ።

በደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ ሀዋሳ ጨርቃ ጨርቅና አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች አሉ። ፋብሪካዎቹ ምን አይነት ጨርቃ ጨርቅ እንደሚያመርቱ መምህራችሁን በመጠየቅ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።



ሥዕል 4/18 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ


የእጅ ሥራ

| |
|---|
| በአከባቢያችሁ ጋቢ ወይም የጥበብ ልብስ የሚሰሩ ሰዎች አሉ |

የሸማ ሥራ የሚሰራ ሰው ሸማኔ ተብሎ ይጠራል። ሸማ ሰሪ ባህላዊ የሆኑ ልብሶችን ይሰራሉ። የጥቡብ ልብሶችን፣ ቀሚሶችን፣ ነጠላዎችን፣ ቡሉኮዎችንና ጋቢዎችን በመስራት ለሰው ልጅ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣሉ።

በቤታችን ውስጥ የምንጠቀምባቸውን ባለሶስት እግር በርጩማ /ኩርሲ፣ ወንበር/፣ ሳጥን፣ እንዲሁም ማረሻ፣ ቢላዋና መሬት ለመቆፈር የምንጠቀምበት ዛሬ ያና ቆቶ ባህላዊ የእጅ ሥራ (እደ ጥበብ) ውጤቶች ናቸው።

እነዚህ የሰው ልጅ የሚጠቀምባቸው የእጅ ጥበብ ውጤት ናቸው።




ሥዕል 4/19 የእጅ ጥበብ /የእጅ ሥራ/ ውጤቶች

- በሥዕሉ የሚታዩ የእጅ ስራ /እደ ጥበብ/ ውጤቶች ከምን እንደተሰሩ ተናገሩ።
- በአከባቢያችሁ እነዚህ የእጅ ሥራ /እደጥበብ/ ውጤቶች የሚሰሩበትን ቦታ በመጎብኘት እንዴት እንደሚሰሩ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

ክር በመጣላለፍ ሹራብ መስራት ይቻላል። ከትምህርት ቤታችሁ የእጅ ስራ ክበብ ካለ ሹራብ እንዴት እንደሚሰራ የክበቡን አባላት ጠይቁ። የሹራብን አሰራር ካያችሁ በኋላ

ወላጆቻችሁን ክርና ኪሮሽ እንዲሰጧችሁ ጠይቃችሁ በተመለከታችሁት መሠረት ሹራብ ለመስራት ሞክሩ።



ሥዕል 4/20 የሹራብ አሠራር

## **4.4.2** የቴክኖሎጂ ውጤቶችና ጠቃሚ ተግባራት

| በወረዳችሁ የሚገኙትን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመምህራችሁ ንገሩ። |
|---|

በወረዳችሁ ውስጥ በርካታ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ይገኛሉ። የቴክኖሎጂ ውጤቶች የምንላቸው ሬድዮ፣ ቴሊቪዥን፣ ምድጃ፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ (ጀኔሬተር)፣ ካውያ (የኤሌክትሪክ)፣ ስልክና ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል)ና የመሳሰሉት ናቸው።

ሬድዮ　　　　　　　　　የኤሌክትሪክ ምድጃ　　　　　　የኤሌክትሪክ ካውያ

ቴሌቪዥን　　　　　　የኤሌክትሪክ ማመንጫ　　　　　　ተንቀሳቃሽ ስልክ

ሥዕል 4/21 የቴክኖሎጂ ውጤቶች

- ከላይ በሥዕሉ የምትመለከቱት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለምን ለምን እንደሚጠቅሙን ለመምህራችሁ ንገሩ።

እያንዳንዱ የቴክኖሎጂ ውጤት የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። በጥንት ዘመን ሰዎች ለሩቅ ዘመዶቻቸው መልዕክት የሚልኩት በሰው አማካኝነት ነው። መልዕክተኛ በእግሩ ወይም በጋማ ከብት ላይ ተቀምጦ ረጅም መንገድ በመጓዝ መልዕክቱን ለተላከለት ሰው ያደርሳል። እንደዚሁም በአንድ አከባቢ ለሚኖሩ ሰዎች መልዕክት ለመንገር ከተፈለገ ጥሩንባ ይነፋል። በአከባቢ የሚኖሩ ሰዎች የጥሩንባ ድምፅ ሲሰሙ በአንድ አከባቢ በዛፍ ጥላ ሥር ይሰባሰባሉ። ከዚያም ለምን እንደሚፈለጉ ይነገራቸዋል።

ሥልጣን እየጨመረ ሲመጣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከባህላዊ መንገዶች የተሻሉና ፈጣን በሆነ መንገድ መልዕክት የሚያስተላለፉ መሣሪያዎችን ሰርተው መጠቀም ጀመሩ። ሬድዮ፣ ቴልቪዥን፣ ስልክና የመሳሰሉት ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ናቸው።

- በዘመናዊና ባህላዊ መገናኛ ዘዴዎች መካከል ምን ልዩነት አለ□
- እናንተ ከምታውቁአቸው መገናኛ ዘዴዎች መካከል በፍጥነት መልዕክት ማስተላለፍ የሚችለው የትኛው ነው□

### 4.4.3 ለወረዳ ዕድገት መሥራት

ስራ መስራት ለምን እንደሚጠቅም ለመምህራችሁ ንገሩ።

የአንድ ቤተሰብ መሪዎች እናትና አባት በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ለቤተሰቡ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ ያገኛሉ። ነገር ግን እነሱ ካልሰሩ ቤተሰቡ ከፍተኛ ችግር ላይ ይወድቃል። ስለዚህ የቤተሰቡ አባላት በተለይም እናትና አባት ቤተሰቡን የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው። እንዲሁም ልጆች አቅማቸው የሚፈቅደውን ስራ ሰርተው ቤተሰቡን መርዳትና ጥናታቸውን በፕሮግራም ማጥናት አለባቸው።

በአንድ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በተለያዩ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ናቸው። ለምሳሌ፡- አብዛኛው የወረዳ ህዝብ በግብርና፣ በንግድ፣ በኢንዱስትሪ እንዲሁም በመንግስት ስራና በመሳሰሉት ይተዳደራል። ህዝብ በተለያየ የስራ መስክ ላይ ከተሰማራ የወረዳውም ሆነ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እያደገ ይሄዳል። በተሻለ የስራ መስክ ለመሰማራት ጠንክሮ መስራትና መማር በጣም አስፈላጊ ነው።

ማንኛውም የወረዳው ነዋሪ ለእድገት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ወይም ስራ ጠቃሚና ሊበረታታ ይገባዋል። አንድ ሰው ከታመመ ስራ መስራት አይችልም። ስራ ለመስራት ሆነ ትምህርት ለመማር ጤናማ መሆን ያስፈልጋል።

እናንተ ህመም ሲሰማችሁ ወደየት ትሄዳላችሁ□

ማንኛውም ሰው ህመም ሲሰማው ለህክምና ወደ ህክምና ተቋማት ይሄዳል፡፡ ከዚያም ለሀኪሙ በሽታውን ነግሮ ይታከምና ከበሽታው ይድናል፡፡ ሐኪሙ ባይኖር ኖሮ ግን መታከም አይቻልም ነበር፡፡

አከባቢያችንን ለማጽዳት ጠዋት ተነስተው አከባቢ የሚጠርጉ ሰዎችን ተምልክታችኋል? እነዚህ ሰዎች አከባቢያችንን ፅዱና ንፁህ በማድረግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ የፅዳት ሠራተኞች በሽታ አምጭ የሆኑ ህዋሳት እንዳይኖሩ በማድረግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ የፅዳት ሠራተኞች ልክ እንደ ሐኪሙ ለወረዳቸው እድገት እኩል ተግባራትን አከናውነዋል ማለት ነው፡፡

? ስራ ክቡር ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

### 4.4.4 ለሁሉም ሥራ አድናቆት መስጠትና አስፈላጊነቱን ማወቅ

የወረዳችሁ ሠራተኞች ሁሉ ሥራ ቢያቆሙ ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ምን ይመስሏችኋል? ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

እያንዳንዱ የወረዳው ሠራተኛ ስራውን በአግባቡ ካልተወጣ የወረዳው እድገት ወደ ኋላ ይቀራል፡፡ ፖሊሶች ስራቸውን ቢያቋርጡ ከፖሊስ ልናገኛው የሚገቡን አገልግሎቶች በሙሉ ይቋረጣሉ፡፡ ይህም ሲባል በህብረተሰቡ ውስጥ ወንጀል ይስፋፋል፤ ወንጀለኞችን ለህግ የሚያቀርብ ይጠፋል፤ ሰላምና ፀጥታ ይታወካል፡፡

? የወረዳው ጤና ሠራተኞች ስራቸው ምንድነው? ለህብረተሰቡ ምን አገልግሎት ይሰጣሉ? የወረዳው ጤና ሠራተኞች ስራቸውን ቢያቆሙ ምን ይከሰታል?

ሰዎች ጤናቸው ሲታወክ ወደ ሀኪም ቤት በመሄድ በጤና ሠራተኞች ህክምና ያገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ የጤና ሠራተኞች ስራቸውን ካቆሙ የህብረተሰቡ ጤና ችግር ላይ ይወድቃል፡፡

? በትምህርት ቤት ውስጥ የመምህር ጠቀሜታ ምንድነው?
የትምህርት ቤቱ መምህራን ስራ ቢያቆሙ ምን ይከሰታል?

በትምህርት ቤት ውስጥ ትልቁ ሰው መምህሩ ነው። ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በአግባቡ የሚከታተሉት በመምህሩ እርዳታ ነው። መምህሩ ከሌለ ትምህርት ቤቶች አይኖሩም። ተማሪዎችም ትምህርታቸውን ለማግኘት አይችሉም ማለት ነው።

በአጠቃላይ ማንኛውም ሠራተኛ ወይም የወረዳ ነዋሪ ለወረዳው እድገት እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ወረዳ የሚኖረው ህዝብ ሲኖር ብቻ ነው። ሰዎች ደግሞ በስራ ሲሰማሩ ለወረዳው እንዲሁም ለሀገር እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ማንኛውም ሠራተኛ በሚያደርገው የስራ እንቅስቃሴ አድናቆትን መስጠት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ስራን መናቅ አስፈላጊ አይደለም ስራዎች ሁሉ እኩል ክብር አላቸው።

## መልመጃ **4.4**

መመሪያ ሀ፦ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን ዓረፍተ ነገር እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. አብዛኛው የሀገራችን ህዝቦች የሚኖሩት በገጠር ነው።
2. አብዛኛው የገጠሩ ህዝብ የገቢ ምንጭ የተመሰረተው በግብርና ላይ ነው።
3. ጥጥና የሸንኮራ አገዳ ለፋብሪካዎች እንደ ጥሬ እቃ ሆነው ያገለግላሉ።
4. የግብርና ምርቶች በፋብሪካ ውስጥ እንደ ጥሬ ዕቃ ያገለግላሉ።
5. ኢንዱስትሪዎች በአንድ አገር ላይ በብዛት መገኘታቸው የእድገት ምልክት ነው።

መመሪያ ለ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአግባቡ ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ሸማ ስራ የሚሰራ ሰው ___________ ይባላል።

ሀ. ገበሬ ለ. ነጋዴ

ሐ. ሸማኔ መ. አርብቶ አደር

2. ከሚከተሉት ውስጥ የቴክኒዮሎጂ ውጤት ያልሆነው የቱ ነው□

ሀ. ሬድዮ ለ. ቴሌቪዥን

ሐ. ጀኔሬተር መ. መልሱ አልተሰጠም

3. ከሚከተሉት ውስጥ ፈጣን መልዕክት ማስተላለፊያ መሣሪያ የቱ ነው□

ሀ. ሬድዮ ለ. ቴሌቪዥን

ሐ. ስልክ መ. ሁሉም መልስ ነው

4. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛው ዓረፍተ ነገር የቱ ነው□

ሀ. በአንድ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በተለያዩ ስራ የተሰማሩ ናቸው።

ለ. ሁሉም የወረዳው ሰራተኞች ለወረዳው እድገት እኩል መስራት አለባቸው።

ሐ. ማንኛውም ስራ ለሀገር እኩል ጠቀሜታ አለው።

መ. ሁሉም ትክክል ነው።

5. ከሚከተሉት ውስጥ በክልላችን የሚገኝ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የቱ ነው□

ሀ. አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ለ. ሀዋሳ ጨርቃጨርቅ

ሐ. ባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ መ. ሀናለ መልስ ናቸው

መመሪያ ሐ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

1. ለመጓጓዣ የምንገለግልባቸውን እንስሳት ጥቀሱ□
2. ከብት ብቻ እያረቡ የሚኖሩ ሰዎች ምን በመባል ይታወቃሉ□
3. በእርሻና በከብት እርባታ ሙያ የተሰማሩ ሰዎች ምን ይባላሉ□
4. ልብስን የሚሰራ ፋብሪካ ምን በመባል ይታወቃል□
5. የእጅ ሥራ ውጤቶች የሚባሉትን ዘርዝሩ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ

## እኛነታችን

የተመደበው ጊዜ **51** ክ/ጊዜ

መግቢያ

ይህ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉት ንዑስ ርዕሶች አሉት። እነሱም ምግብ፣ የምግብ ጥቅም፣ በተለምዶ የምንመገባቸው ምግቦች የምግብ ምንጮች፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ ጤና፣ የጤናማነት ጥቅም፣ ጤናማና፣ ህመምተኞችን ማወዳደር፣ የህመም ምልክቶች፣ የህመም ስሜት ሲሰማን ምን ማድረግ እንደሚገባን፣ የግል ንፅህና፣ የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶች፣ የግል ንፅህናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት ችግር እንደሚፈጠርባቸው፣ የግል ንፅህናን ባለመጠበቅ የሚከሰቱ በሽታዎች፣ ኤድስ በደም የሚተላለፍ በሽታ መሆኑ፣ አንድ ሰው በአደጋ ላይ የሚገኝ ከሆነ በአስቸኳይ ለትልቅ ሰዎች መንገር፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ ልምዶች፣ ለሌሎች ጤንነት ሀላፊነት እንዳለበን ማሣየት የሚሉ በዝርዝር የሚተኮርባቸው ትምህርቶች ናቸው።

በዚህም መሠረት መምህራን በክፍለ ትምህርቱ የተጠቀሱትን በመከታተል የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ተማሪዎቹ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባችኋል።

<u>አጠቃላይ ዓላማ፡-</u> ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

1. የምግብን ጥቅም ይዘረዝራሉ፣ በአከባቢያቸው በተደጋጋሚ ለምግብነት የሚውሉ ምግቦችን ይዘረዝራሉ፣ ከእንስሳትና እፅዋት የሚገኙ የተለያዩ ምግቦችን ይለያሉ፣ ትክክለኛ የሆነ የአመጋገብ ሥርዓትን ያሣያሉ።
2. የጤናን ምንነት ይገልፃሉ፣ ጤናማ መሆንና ህመመተኛነትን በማወዳደር ይገልፃሉ።
3. የህመም ምልክቶችን ይናገራሉ፣ የህመም ስሜቶች ሲሰሚቸው ለሌሎች እንዴት መናገር እንደሚችሉ ይገልፃሉ፣ ጥሩ የግል ጤና አጠባበቅንም ያሣያሉ፣
4. ሣይንሳዊ የሆነ የምርምር አሰራሮችና ክህሎቶችን በዚህ ክፍለ ትምህርት ተግባራዊ ያደርጋሉ። አከባቢን በመመልከት፣ በመጠየቅ፣ በመመደብ፣ ግንኙነትንና አብሮ መሥራትን በተግባር ያሣያሉ።

**1.1** ምግብ

የተመደበው ጊዜ- 17 ክ/ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የምግብን ምንነት ይገልፃሉ።
- የምግብን ጥቅም ያስረዳሉ።
- በአከባቢያቸው የተለመዱ ምግቦችን ይዘረዝራሉ።
- የእንስሳትና የእፅዋትን ተዋፅኦ ለይተው ይመድባሉ።
- ከእንስሳትና ከእፅዋት የሚገኙ ምግቦችን ምሣሌ ይሰጣሉ።
- ትክክለኛውን የአመጋገብ ሥርዓትን ያሣያሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች፡-

- ምግብ
- የምግብ ጥቅም
- በተለምዶ የምንመገባቸው ምግቦች
- የምግብ ምንጮች
- የአመጋገብ ሥርዓት

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

በቅድሚያ ዋናውን ርዕስ ያስተዋውቁና በክፍለ ትምህርቱ ርዕስ ሥር ያገኙዋቸውን ቁልፍ ቃላት በማንበብ እንዲያውቁዋቸው ያድርጉ።
ከዚያም የመጀመሪያውን ንዑስ ርዕስ ያቅርቡና ለማነቃቂያነት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲነጋገሩና ለመመለስ እንዲሞክሩ ጊዜ ይስጧቸው። ይህንን ሲያደርጉ ጥያቄዎቹን በጥቁር ሠሌዳው ላይ በመፃፍ ወይም በማንበብ ሊሆን ይችላል።

ከዚያም የተማሪዎቹን ምላሽ ከሰበሰቡ በኋላ ልክ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንደተጠቀሰው ሰው ከሌሎች እንሰሳት ጋር በብዙ መንገድ እንደሚመሳሰል ያስረዱዋቸው። እንደ ምሳሌም መዋለዱ፣ መመገቡ፣ መተንፈሱ፣ መንቀሳቀሱ ተጠቃሽ መሆኑን ይንገሯቸው።

ይሁን እንጂ ሰው ከሌሎች እንሰሳት የሚለዩት ባህሪያት ያሉትና ከነዚህም ውስጥ የራሱን መጠለያ ሰርቶ መኖሩ፣ ቋንቋ መናገሩ፣ ማሰብና ማቀዱ፣ ያሰበውንና ያቀደውን በሥራ

መግለፅ መቻሉ ልዩነቶቹ መሆኑን ማብራራትና ሦስቱ የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ምግብ፣ ልብስና መጠለያ መሆናቸውን ይግለፁላቸው።

1.1.1 ስለ ምግብ ምንነትና የምግብ ጥቅም ተማሪዎች ሀሳቦችን ከወላጆቻቸውና ከሌሎች ሰዎች እንዲያሰባስቡ በማድረግና ካሰባሰቡ በኋላ በመልክ በመልኩ አድርገው ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉዋቸው። የምግብ ምንነትን በተመለከተ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ እንደተጠቀሰው ሊበላና ሊጠጣ የሚችል ነገር መሆኑን ምሳሌዎችን በመጥቀስ ይግለጹላቸው። የምግብ ጥቅም እንደዚሁ ለእድገትና ጥንካሬ፣ ኃይልና ሙቀት ለመስጠትና በሽታን ለመከላከል የሚጠቅም መሆኑን ያስረዱዋቸው። የምግቦችን የምግብነት ይዘት በተመለከተ ተማሪዎች በክፍል ወይም በቤት ሥራ መልክ እንዲወያዩበት በማድረግ፣ ምላሻቸውን በመቀበል ምግቦች ሁሉ እኩል የሆነ ጠቃሚ ንጥረ ምግብ እንዳልያዙና እንዲያውም አንዳንድ የምግብ ክፍሎች በምግብ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ቢኖራቸውም የምግብነት ይዘት እንደሌላቸው "ውሃ"ን በምሣሌነት በመጥቀስ ማስረዳት ይገባል።

የምግብ ዓይነቶችን ምድብ በተመለከተ የምግብ ዓይነቶች በስንት እንደሚከፈሉ፣ ስማቸውንና የእያንዳንዱን ክፍል ጥቅም ተማሪዎቹ እንዲገልፁ በመጠየቅ ምላሻቸውን መቀበልና ምግቦች ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚመደቡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመፃፍ ያስረዱዋቸው።

የእያንዳንዱን ምግብ ክፍል ዝርዝር ዓይነትና ጥቅም ለማነቃቂያነት በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የእያንዳንዱን ምግብ ክፍል ሥዕል መሠረት በማድረግ እንዲመልሱ ያድርጉ። ይህንን ሲያከናውኑ በተለይ በእያንዳንዱ የምግብ ክፍል ውስጥ በስዕል የቀረቡ ምግቦችን ወደ ክፍል ማምጣት የሚችሉትን በክፍል አቅርቦ እያሳዩ ማስረዳት ይበልጥ ተመራጭነት ይኖረዋል።

ሦስቱም የምግብ ክፍል የእንስሳትና እፅዋት ተዋጽኦ ያካተቱ መሆኑን ማስረዳት። ገንቢና ጠጋኝ ምግብችን ይበልጥ መመገብ ያለባቸው ህፃናትና አዛውንቶች መሆናቸውንም ማብራራት። ምክንያቱም ለህፃናት ከዕድሜያቸው ጋር የሚጣጣም የተስተካከለ ዕድገት እንዲኖራቸው ሲሆን፣ ለአዛውንቶች ደግሞ የተጎዱና የደከሙ ህዋሶቻቸውን ለመጠገን

እንደሚያስፈልጋቸው ማብራራት እንዲሁም የገንቢና ጠጋኝ ምግቦች እጥረት የህፃናትን እድገት ፍጥነት እንደሚቀንስ፣ ኳሺኳር ለሚባል በሽታ እንደሚያጋልጣቸው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሥዕል አንድ አምስትን እንዲመለከቱ በማድረግ ማስረዳት ይጠበቃል።

ሃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦችን ይበልጥ መመገብ ያለበት የህብረተሰብ ክፍል ከባድ የጉልበት ሥራ የሚሰሩ መሆናቸውንና በቅዝቃዜና ብርድ ሰዓት ለሁሉም ሰው እንደሚያስፈልጉ መግለፅ ተገቢ ነው።

በበሽታ ተከላካይ ምግቦች እጥረት የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን ተማሪዎች ያውቁ እንደሆነ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሞክሩ መጠየቅና መልሶቻቸውን መሰብሰብ፣ ሙከራቸውንም ማድነቅ ከዚያም በበሽታ ተከላካይ ምግቦች እጥረት የሚከሰቱ በሽታዎች እንደ ድድ መድማት፣ እንቅርት፣ ኳሺኳር፣ ወርሃነት፣ የደም ማነስ፣ ወዘተ መሆናቸወን መግለፅና እነዚህም በሽታዎች በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚከሰቱ መሆናቸውን፣ እንደ ኳሺኳርና ወርሃነት ያሉት ግን በህፃናት ላይ ብቻ ሊታዩ እንደሚችሉ በሚገባ ማብራራት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ህፃናት የተሟላ ጤንነትና የተስተካከለ ዕድገት እንዲኖራቸው የተሟላ ምግብ ማግኘት ያለባቸው መሆኑን ያስረዱዋቸው። ህፃናት በመጠንና ዓይነት የተሟላ ምግብ ካላገኙ ግን፦

- ከዕድሜ በታች የሆነ ዕድገት እንደሚኖራቸው፣
- ለበሽታ በቀላሉ እንደሚጋለጡ ፣
- ከአቻቸው ጋር እኩል ተራሩጠው መጫወት እንደሚሳናቸው በሚገባ ማብራራት አስፈላጊ ነው።

## 1.1.2 በተለምዶ የምንመገባቸው ምግቦች

ተማሪዎች በአከባቢቸው በተደጋጋሚ ለምግብነት የሚውሉ የምግብ ዓይነቶችን ሥም እንዲዘረዝሩ መጠየቅና ዝርዝር አዘጋጅተው እንዲያሠፍሩ ማድረግ፣ ከዝርዝሩም ውስጥ ይበልጥ ለመመገብ የሚመርጡትንና የሚስማማቸው የትኛው እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉና በተሰጠው ምርጫም ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ከመጀመሪያ በማድረግ እንደገና በቅደም ተከተል በመፃፍ በአከባቢው ተወዳጅ የሆነው ምግብ የትኛው እንደሆነ ያሣዩዋቸው። በዚህም በአንድ አካባቢ ተዘወትሮ ለምግብነት የሚቀርብ ምግብ የተለምዶ ምግብ እንደሚባል ያስረዱዋቸው።

### 1.1.3 የምግብ ምንጮች

የምግብ ምንጭን በተመለከተ ተማሪዎቹን ለማነቃቂያነት የቀረበውን ጥያቄ በመጠየቅ በአካባቢያቸው የሚመገቡት ምግብ ከምን ከምን እንደሚገኝ እንዲናገሩ ማድረግና የልጆቹን መልሶች በማቀናጀት ምግቡ ምንም ይሁን ምን የመጣው ከሁለቱ ምንጮች ማለትም ከእንስሳትና እፅዋት መሆኑን ተማሪዎቹ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ። ከዚያም ተማሪዎቹ በአከባቢያቸው ከእፅዋት የሚዘጋጁ የምግብ ዓይነቶችንና ከእንሰሳት የሚዘጋጁ ምግቦችን ምን ምን እንደሆኑ እንዲገልፁ በማድረግ፤ ለምሣሌ፡- ከእፅዋት ለሚገኙ ምግቦች በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ሥዕል አንድ ስድስት ከእንስሳት ለሚገኙ ምግቦች ደግሞ ሥዕል አንድ ሰባትን መሠረት አድርገው ሌሎችንም እንዲናገሩ መጋበዝና እነዚህ ምግቦች በምን ዓይነት መልኩ ተዘጋጅተው ለምግብነት እንደሚውሉ እንዲገልፁ ማድረግ አስፈላጊ ነው። መልሶቻቸውንም ማሰባሰብና ከሁለቱም ምንጮች የሚገኙ ምግቦች እንደየአካባቢ ሁኔታና የምግቡ ዓይነት በጥሬነታቸው፣ ተጠብሶ ወይም በስሎ (ተቀቅለው) ለምግብነት እንደሚውሉ ማብራራትና ከእፅዋት የሚገኙ ምግቦች የእፅዋት ተዋጽኦ እንደሚባሉ ሥዕል አንድ ስድስትን እንዲመለከቱ ማድረግ። ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች ደግሞ የእንስሳት ተዋጽኦ እንደሚባሉ መግለፅና ለዚህም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሥዕል አንድ ሰባትን መጥቀስና ሌሎችንም እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

### 1.1.4 የአመጋብ ሥርዓት

የአመጋገብ ሥርዓትን በሚመለከት ለማነቃቂያነት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሞክሩ እድል መፍጠር። ከዚያም ጊዜ ሰጥተው ምላሻቸውን ማሰባሰብ ያስፈልጋል።

በቀጣይነትም የሰው የአመጋገብ ሥርዓት እንደ ምግቡ ዓይነት፣ ባህል፣ የስልጣኔ ደረጃ የሚለያይ መሆኑንና በሦስት ደረጃዎች (ክፍሎች) መከፈሉን ጊዜ ሰጥተው ያስረዱዋቸው። እነዚህ ሥርዓቶችም፡-

- ከምግብ በፊት
- በምግብ ወቅት
- ከምግብ በኋላ

መሆናቸውን ማብራራትዎን መርሳት የለብዎትም። አያይዘውም ስለእያንዳንዱ የአመጋብ ሥርዓት በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ በስፋት መገለፁን በመጠቆም አንብበው ይበልጥ እንዲረዱ ማድረግ ተገቢነት ይኖረዋል።

### 1.4.1 ምግብን ተካፍሎ መመገብ

ምግብን ተካፍሎ ስለመመገብ ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲሞክሩ በማድረግ የአብዛኛዎቹን ምላሽ ማመዛዘንና ዋጋ መስጠት (ጥሩ ምላሽ መሆኑን መግለፅ) እና አብሮ መመገብ ጥሩ ልምድና የመልካም ማህበራዊ ግንኙነት መሠረት መሆኑን ማስረዳት አስፈላጊ ነው። ሥዕል አንድ ዘጠኝን እንዲመለከቱና ምን እንደተገዘቡ የተጠየቀውንም ጥያቄ መሠረት አድርገው እንዲመልሱ ማድረግ የተማሪዎቹን ግንዛቤ የበለጠ እንደሚያሰፋ መታወቅ አለበት።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የእያንዳንዱን የምግብ ክፍል ዝርዝር የያዘ ሥዕል፣
- የምግብ እጥረት ያለባቸው ህፃናት እንዲሁም አዋቂዎች ሥዕል፣

## 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

- የምግብን ምንነትና ጥቅም ለይተው ማወቃቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም፣
- የምግብ ክፍሎችንና አገልግሎታቸውን በሚገባ መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም፣
- የእፅዋትንና የእንስሳት ተዋጽኦ የሆኑ ምግቦችን እንዲመድቡና ምሳሌ እንዲሰጡ በመጠየቅ መገምገም፣
- በአካባቢያቸው በተለምዶ ለምግብነት የሚውሉ ምግቦችን እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ መገምገም፣
- የአመጋገብ ሥርዓቶችና ጥቅማቸውን እንዲገልፁ በመጠየቅ መገምገም፣
- አብሮ መመገብ ምን ጥቅም እንዳለው እንዲገልፁ በመጠየቅ መገምገም፣

መልመጃ **1.1** መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. ውሸት

4. እውነት
5. ውሸት
6. እውነት
7. እውነት
8. እውነት

ለ/

1. የተለምዶ
2. በሽታ ተከላካይ
3. የመልካም ማህበራዊ ግንኙነት
4. የመብነን/ቅባት

ሐ/

| | |
|---|---|
| 1. ለ | 6. ለ |
| 2. ለ | 7. ሐ |
| 3. መ | 8. ሀ |
| 4. ለ | 9. መ |
| 5. ለ | 10 . ሐ |

መ/ 1. ሀ. ሰውነት መገንባትና መጠገን
ለ. ኃይልና ሙቀት መስጠት
ሐ. በሽታን መከላከል

2. ሀ እንስሣት ለ. እፅዋት
3. ሀ. ከምግብ በፊት ሥነ ሥርዓት
ለ. በምግብ ጊዜ ሥነ ሥርዓት
ሐ. ከምግብ በኋላ ሥነ ሥርዓት

4. ለዚህ ጥያቄ መልስ አግባብ የሆኑ መልሶችን መቀበል ይቻላል።
ለምሣሌ፡-

- የዓይን በሽታ
- የጥርስ በሽታ
- የእከክ በሽታ
- የወስፋት በሽታ
- የተቅማጥ በሽታ
- የአሜባ በሽታ
- የተስቦ በሽታ ወዘተ.

## 1.2 እኛ ጤናማ ነን!

የተመደበው ጊዜ 17 ክ/ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፦ ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- ጤና የአካልና የማህበረሰብ ደህንነት መሆኑን ይገልፃሉ።
- ጤናማ የመሆን ጥቅምን ያስረዳሉ፣
- በታመመ ሰውና በጤናማ ሰው መካከል ያሉትን ባህሪያት ያወዳድራሉ።
- የታመመ ሰውን መርዳት ጠቀሜታ እንዳለው ያስረዳሉ።
- የህመም ምልክቶችን ይዘረዝራሉ፣
- የሕመም ስሜቶችን ይገልፃሉ፣
- የህመም ስሜት ሲሰማቸው ለሌሎች ሰዎች መናገር ጥቅም እንዳለው ያስረዳሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘት

- ጤና ምንድነው ?
- ጤናማ የመሆን ጥቅም፣
- ጤናማ የሆኑና የታመሙ ሰዎችን ማወዳደር፣
- ለታመሙ ሰዎች የሚደረግ እንክብካቤ፣
- የጤና መጓደል ምልክቶች፣
- የህመም ስሜት ሲሰማን ምን ማድረግ አለብን?

## 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች፦

## 1.2.1 ጤና ምንድነው?

ይህንን ትምህርት መጀመሪያ በክፍለ ትምህርቱ ርዕስ ስር የሚያገኙዋቸውን ቁልፍ ቃላት እንዲያውቋቸው ያድርጉ። ከዚያም ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ያበረታቱአቸው። ጤና ማለት ምን ማለት እንደሆነም እንዲያብራሩ ያድርጉ። "ሁል ጊዜ ደስተኞች ናችሁ ወይ?" ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ፣ "አዎ" ወይም አይደለሁም ሊሉ ይችላሉ። "አይደለም" ወይም "አይደለሁም" የሚል ምላሽ ከተሰጠ ግን ምክንያቱ ምን እንደሆነ እንዲያብራሩ ማድረግ ይጠበቃል።

"የምትከፉና የምትደሰቱ ምን ስትሆኑ ነው□" ለተባለው ጥያቄ የተለያየ መልስ ሊመልሱ ይችላሉ። ለምሣሌ ሲርበን፣ ወላጆቻችን ሲቆጡን፣ ወዘተ ሊሉ ይችላሉ። ነገር ግን ከጤንነት ሁኔታ ጋር በማያያዝ ሲያማችሁስ በማለት ጤና ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልፁ ማድረግና በመጨረሻም የጤናን ትርጉም የውስጣዊና ውጫዊ አካል ደህንነት ማለት መሆኑንና በጥቅሉ የአካልና የማህበረሰብ ደህንነት ማለት መሆኑን አብራርተው ያስረዱዋቸው።

ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን በአንደኛ ክፍል ውስጥ ተምረውት የመጡ ስለሆነ የተወሰኑትን በማስታወስ እንዲጠቅሱ ማድረግ ነው።

## 1.2.2 የጤናማነት ጥቅም

ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀመርና ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ማበረታታት ምላሾቻቸውን መቀበል ከዚያም ጤናማ ሰው በእውቀቱና በጉልበቱ ጠቃሚ የሆነ ሥራ መሥራት እንደሚችል፣ ጤናማ ያልሆነ ሰው ግን ይህንን ማድረግ እንደሚሣነው ማብራራት ተገቢ ነው።

ጤናማ ሰዎች በጥቅሉ፡-

- ደስተኞች እንደሆኑ፣
- ውስጣዊ ደህንነት እንደሚሰማቸው፣
- ንቁና ጠንካሮች እንደሆኑና፣
- የዕለት ተዕለት ሥራቸውን በሙሉ ሀይላቸው ማከናወን የሚችሉ መሆናቸውን ማስረዳት ይጠበቃል።

### 1.2.2.1 ደስተኛ መሆንና አለመሆን

በጤናማና ጤናማ ባልሆነ ሰው መካከል ያሉትን ልዩነቶች ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ በማድረግ ሀሳባቸውን መቀበልና ጤናማ ሰው ከላይ ከፍ ብሎ የተገለፁትን ባህሪያት እንደሚያሳዩ ያስረዱዋቸው።

በተቃራኒው የታመመ ሰው ግን፡-

- ደስተኛ እንዳልሆነ፣
- ውስጣዊ ደህንነት እንደማይሰማው፣
- መተኛት እንደሚያበዛ፣

- የዕለት ሥራውን በአግባቡ ማከናወን እንደሚሣነው በመዘርዘር ጤናማ የሆነ ሰውና ታማሚ ሰው የሚያሳየውን ባህሪይ ለይቶ ማስረዳት ይገባል። በተጨማሪም ሥዕል አንድ አስርን እንዲመለከቱና ከዚያም እንዲያብራሩ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

### 1.2.2.2. ህመምተኞችንና አካል ጉዳተኞችን ማክበርና መተባበር

ለማነቃቂያነት የቀረበውን ጥያቄ በመጠየቅ መጀመር። ጥያቄውን ተማሪዎቹ እንዲመለሱ በማድረግ መልሳቸውን መሰብሰብና ህመምተኛነትና አካል ጉዳተኛነት የሚለያዩ መሆኑን ማስረዳት። እንዲሁም እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ሲያጋጥሙን ርህራሄ ማሳየት፣ ማክበርና መተባበር የህሊና እርካታ እንደሚሰጥ ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

### 1.2.3 ጤናማና ህመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር

ይህንን ትምህርት ቀደም ሲል በጤናማነትና ጤናማ ባለመሆን መካከል ብዙ የባህሪ ልዩነቶች እንዳሉ የተማሩ መሆኑን በመግለፅ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ በሠንጠረዥ አንድ አንድ እንዲመለከቱ ማድረግና በተጨማሪም በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በቀረበው ተግባራዊ ክንዋኔ መሠረት ጤናማ ባልሆነ ሰው ላይ የሚታዩት ባህሪያትን ከወላጆቻቸውና ከጤና ባለሙያዎች ጠይቀው ልዩነቶቹን በሠንጠረዥ ሰርተው እንዲያመጡ የቤት ሥራ መስጠትና በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ከተዘረዘሩት ባህሪያት ጋር እንዲያነፃፅሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### 1.2.3.1 ህመምተኛን መርዳትና መንከባከብ

የታመሙ ሰዎችን መርዳትና መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን ማስረዳት። ከምንከባከብባቸው መንገዶች ውስጥ ለምሣሌ፡- በማጫወት፣ ልብሣቸውን በማጠብና ወደ ህክምና ተቋም በመውሰድ እንዲታከሙ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይንገሯቸው።

### 1.2.4 የህመም ምልክቶች

አንድ ሰው መታመሙን እንዴት ማወቅ እንደሚቻል እንዲገልፁ በማድረግ ትምህርቱን መጀመርና የታመመ ሰው የተለያዩ የጤና መጓደል ምልክቶች እንደሚታዩበትና ከነዚህም የጤና መጓደል ምልክቶች መካከል እንደትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ … ተጠቃሾች መሆናቸውን ማስረዳት አስፈላጊ ነው። ከተማሪዎቹ መካከልም ታሞ የሚያውቅ ካለ በወቅቱ ተሰምቶት(ቷት) የነበረው የህመም ምልክት ምን እንደነበር መጠየቅና ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲናገር (ትናገር) በማድረግ ከላይ ከተገለፁት ምልክቶች ጋር ማነፃፀር ተገቢነት አለው። ሥዕል አንድ

አስራ ሁለትን እንዲመለከቱ ማድረግ ትምህርቱ ይበልጥ ህያው እንዲሆን የሚያግዝ መሆኑን አይዘንጉ።

**1.2.5** የህመም ስሜቶች ሲሰሙን ምን ማድረግ ይገባናል

ይህንን ትምህርት ሲያቀርቡ ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ያድርጉ። የተማሪዎቹን ምላሽ ከተቀበሉም በኋላ የህመም ስሜቶች እንደ በሽታው ዓይነት እንደሚለያዩ በመግለፅ፣ የህመም ስሜት በሽታው የተከሰተበት የአካል ክፍል ላይ ተፈጥሮአዊ ሥራው መተጓጎል መሆኑን ያስረዱዋቸው።

ተማሪዎቹም የህመም ስሜት ሲሰማቸው ወዲያውኑ ለወላጆቻቸው ወይም ለመምህራቸው መንገር እንዳለባቸውና በፍጥነትም ወደ ህኪም ቤት በመሄድ ህክምና ማግኘት እንደሚገባቸው በአፅንኦት ያስገንዝቧቸው።

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረበውን ተግባራዊ ክንዋኔ የሚሰሩ ተማሪዎች እንዲመረጡና አንዱ ሐኪም ሌሎቹ እንደ ታማሚና ሌሎቹ ደግሞ እንደ አስታማሚ ሆነው አስመስለው እንዲሰሩ በማድረግ የተማሪውን ግንዛቤ ማሳደግ እንደሚቻል መታወቅ አለበት።

**4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-

- ሥዕሎች
- ቻርቶች
- ፖስተሮች

5. የመከታተያና መገምገሚያ ስልቶች፡-

- የጤናን ምንነት በመጠየቅ መረዳታቸውን መገምገም፣
- በጤነኛና በታማሚ ሰዎች የሚታዩ ባህሪያትን ማወቃቸውን ለመገምገም የተወሰኑትን እንዲጠቅሱ ማድረግ፣
- የህመም ስሜት ሲሰማን ምን ማድረግ እንዳለብን መጠየቅ፣
- የታመሙ ሰዎችን ምን በማድረግ መርዳት እንደሚችሉ መጠየቅ፣

- የጤና መጓደል ምልክቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

**የመልመጃ 1/2 መልሶች**

ሀ/ 1. እውነት

2. ሀሰት

3. ሀሰት

4. እውነት

5. እውነት

ለ/ 1. ሀ    2. ሀ    3. ሐ

**የመልመጃ 1/3 መልሶች**

2. ከፍተኛ ትኩሳት፣ራስ ምታት፣ማንቀጥቀጥ፣ከፍተኛ ላብ

3. ራስ ምታት፣ሳል፣ማስነጠስ

4. ትኩሳት፣ራስ ምታት፣ከፍተኛ ላብ

5. ራስ ምታት፣ማዞር፣አቅም ማነስ

7. ሆድ ቁርጠት፣ተቅማጥ እና ማስማጥ

8. ማቃጠልና ቃር

9. ሆድ ቁርጠት፣ ንጣት፣ ጎሮሮ አካባቢ መቆርቆር፣ ምራቅ አፍ ውስጥ መብዛት

10. ማፈን /መተንፈስ አለመቻል/፣ ሳልና ጉልበት ማነስ

**የመልመጃ 1/4 መልሶች**

ሀ/ 1. መ

2. ሐ

3. ሀ

4. ሠ

5. ሐ

ለ/ 1. ለ

2. ሐ

3. ሀ

4. ሠ

5. መ

ሐ/ 1. እውነት

2. ሀሰት

3. ሀሰት

4. እውነት

## 1.3. የግል ንጽህናችንን እንጠብቃለን

የተመደበው ጊዜ **17** ክፍለ ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፦
   - ጥሩ የሆነ የጤና አጠባበቅን በተገቢው መልኩ ይገልፃሉ።
   - በንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን ይጠራሉ።
   - ኤድስ በሽታ በደም ንክኪ የሚተላለፍ መሆኑን ይገነዘባሉ።
   - ትክክለኛ የሆነ የግል ንጽህና አጠባበቅን ተግባራዊ ያደርጋሉ።

2. ዝርዝር ይዘቶች
   - የግል ንጽህናችንን ለምን እንጠብቃለን?
   - እኛ የግል ንጽህናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት ችግር ይፈጠርባቸዋል?
   - የግል ንጽህናን ባለመጠበቅ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች፣
   - ኤድስ በደም የሚተላለፍ በሽታ፣
   - አንድ ሰው በአደጋ ላይ የሚገኝ ከሆነ ለትልቅ ሰዎች በአስቸኳይ መንገር አለባችሁ፣
   - የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች።

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

### **1.3.1.** የግል ንጽህናችንን ለምን እንጠብቃለን**?**

የዕለቱን ትምህርት፣"የግል ንጽህና ማለት ምን ማለት እንደሆነ? የግል ንጽህናን መጠበቅ ለምን እንደሚያስፈልግ? እንዲሁም የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ?" የሚሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን በመጠየቅ ይጀምሩ። በቀጣይነትም ተማሪዎቹ የሚሰጡትን መልስ መቀበል ያስፈልጋል። ከዚያም የግል ንጽህና ማለት ሰው ለአካል ክፍሉና ለሚለብሰው ልብሱ የሚያደርገው ጥንቃቄ መሆኑን ያስረዱዋቸው። የግል ንጽህናን መጠበቅ ለምን አስፈለገ ? ለሚለው የግል ንጽህና መጓደል ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ከማጋለጡም በላይ ውበትን የሚቀንስ መሆኑን ያስረዱዋቸው።

የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶችም

- እጅን፣ እግርንና ፀጉርን መታጠብ፣
- የእጅና እግር ጥፍርን መቁረጥ፣
- ገላን መታጠብ፣
- ጥርስን በሚገባ መፋቅና
- ልብስን አጥቦና ተኩሶ መልበስ መሆኑ ማስገንዘብ ይጠበቃል።

እጅን፣ ፊትን፣ እግርንና ፀጉርን መታጠብ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ተማሪዎቹ እንዲገልፁ በመጠየቅ መልሶቻቸውን ይቀበሉ። ተማሪዎቹ ለሚያደርጉት ተሳትፎም ያበረታቱዋቸው። ከዚያም፡-

- በእጃችን ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ስለምንነካ ንጹህ የሚመስለው እጃችን ንጹህ እንዳልሆነ ማሳወቅና ሁል ጊዜ ከምግብ በፊትና በኋላ በንጹህ ውሃና ሳሙና በደንብ መታጠብ አስፈላጊ እንደሆነ ማስረዳት፣
- ፊታችንን ካልታጠብን በዝንቦች አማካይነት ለሚተላለፉ በሽታዎች ከመጋለጣችንም በላይ ውበታችንም ስለሚቀንስ፣ ፊትን ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋትና አስፈላጊ በሆነ ሰዓት መታጠብ አስፈላጊ እንደሆነ ማስረዳት፣
- እግርን የሚያጠቁ የበሽታ መንስኤዎች ለምሳሌ እንደ ፈንገስ(ጮቅ) እና ባክቴሪያዎች እንዳሉ መግለፅና በተጨማሪም እግር በሙቀትና አቧራ ሽታ ሊያመጣ እንደሚችል በማስረዳት ዘወትር እግርንና ካልሲን ማጠብ እንደሚያስፈልግ መግለፅ፣
- ፀጉር አቧራን መሰብሰብ እንደሚችል በዚህም ምክንያት ቶሎ እንደሚቆሸሽ፣ ሲቆሸሽ ደግሞ የሚያሳክክ ከመሆኑም በላይ መልኩን እንደሚቀይርና ይህም ውበታችንን እንደሚቀንስ በመግለፅ ቢያንስ በየ ሶስት ቀኑ መታጠብና ሲያድግም ማሳጠር አስፈላጊ እንደሆነ ማስረዳት፣
- ጥፍሮቻችን ሲያድጉ ቆሻሻን መያዝ የሚችሉና ይህ ቆሻሻ ደግሞ ለበሽታ አምጪ ተህዋሲያን ምቹ መደበቂያ እንደሚሆን በመግለፅ፣ ጥፍሮቻችን በአዲስ ምላጭ ወይም ሌላ ሰው በማይጠቀምበት ጥፍር መቁረጫ መቁረጥ፣ እጅን በምግብ ወቅት መታጠብ ቆሻሻን ለማስለቀቅ እንደሚረዳ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

በቀጣይነትም ተማሪዎቹ ከጥርስ ጥቅሞች ውስጥ ጥቂቶቹን እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ መልሶቻቸውን ይቀበሉ። ከዚያም ጥርስ ብዙ አገልግሎቶች እንዳሉት የሚከተሉትን ነጥቦች በማስረዳት ያሣውቁዋቸው። ይኸውም፡-

- ምግብን መፍጨት፣
- የደቀቀውን ምግብ ከምራቅ ጋር ማዋሃድ፣
- ንግግርን አስተካክሎ ለመናገር፣
- ውበትም እንደሆነ የሚሉትን ማለት ነው።

የጥርስ ንጽህና መጠበቂያ መንገዶችም፡-

- ከምግብ በፊትና በኋላ በውሃ መጉመጥመጥና ከምግብ በኋላ ደግሞ በሚገባ መፋቅ፣
- አልፎ አልፎም በጥርስ ማፅጃ ሳሙና ማጠብ ለጥርስ ደህንነት አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ጥሩ ያልሆነ የአፍ ጠረንንም እንደሚቀንስ መግለፅ።

የገላን መታጠብ አስፈላጊነት በተመለከተ፣ ገላቸውን በሳምንት ስንት ጊዜ ንደሚታጠቡ፣ እንዲሁም ከመታጠባቸው በፊትና ከታጠቡ በኋላ ያለውን ልዩነት እንዲናገሩ በመጠየቅ መልሶቻቸውን መቀበልና ተሳትፎዋቸውን ማድነቅ። ከዚያም ገላ በተለያየ መንገድ ሊቆሽሽ እንደሚችልና ይህንን ቆሻሻ በየጊዜው ካልታጠብን፦

- የሰውነታችን ጠረን እንደሚቀየር፣
- እንደሚቀነቅነን (እንደሚያሳክከንና)
- ምቾት እንደሚነሳን ማስረዳትና ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ገላችንን መታጠብ ለጤንነታችን አስፈላጊ እንደሆነ ማስረዳት ይኖርብዎታል።

ልብስ ከምን ከምን እንደሚሰራ፣ ለምን እንደሚጠቅመንና ልብስን ማፅዳት ለምን እንደሚያስፈልግ ይጠይቋቸውና መልሶቻቸውን ይቀበሉ። ከዚያም ተቀራራቢ ወይም ትክክለኛ የሆኑ መልሶቻቸውን በማጠናከር ልብስ ከዕፅዋትና እንስሳት ወጤት እንደሚሰራ፣ ጠቀሜታውም እንደየወቅቱ ሁኔታ ከብርድ፣ ከፀሐይና ነፋስ እንደሚጠብቀን እንዲሁም ገላን ለመሸፈን እንደሚጠቅመን ይግለፁላቸው።

በሌላም በኩል ልብስ በላብና አቧራ ሊቆሽሽ እንደሚችልና የቆሸሸ ልብስ ደግሞ ለተለያዩ እንደቅማል ላሉ ደም መጣጭና በሽታ አስተላላፊዎች መኖሪያና መራቢያ ስለሚሆን ልብስን ቶሎ ቶሎ ማጠብ ለተለያዩ በሽታዎች ከመጋለጥ እንደሚያድንና እንዲሁም የታጠበ ልብስ ውበትንም እንደሚጨምር አብራርቶ ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

#### 1.3.1.1 እኛ የግል ንጽህናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት ችግር ይፈጠርባቸዋል?

በዚህ ርዕስ ስር ለማነቃቂያነት የተቀመጡ ጥያቄዎችን ማለትም፣ ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፉ የሚችሉ የበሽታ ዓይነቶችን፣ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ውስጥ በግል ንጽህና ጉድለት የሚተላለፉት የትኞቹ እንደሆኑ እንዲለዩ በመጠየቅ የተማሪዎቹን ምላሽ ያሰባስቡ፤ተሳትፎአቸውንም ያድንቁላቸው።ከዚያም በአብዛኛው በግል ንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፉ የሚችሉ በመሆኑ በበሽታው ከተያዝን ወደ ሌላ ሰው እንዳይተላለፍ ካልተጠነቀቅን በሽታውን ወደ ሌላ ሰው በማስተላለፍ ሌሎች ጤነኞችን ለበሽታ የምንዳርግ መሆኑን ማስረዳት። ስለዚህም፡-

አንደኛ- የግል ንጽህናችንን በሚገባ በመጠበቅ በሽታውን መከላከል፣

ሁለተኛ- ከተያዝን ደግሞ በሽታው ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባን ያስረዱዋቸው።

### 1.3.2 የግል ንጽህናን ባለመጠበቅ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች

በግል ንጽህና ጉድለት ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን ተማሪዎቹ እንዲጠቅሱ ይጠይቁዋቸው። መልሶቻቸውንም ያሰባስቡ። ከዚያም እነሱ(ተማሪዎቹ) ከመለሱት ውስጥ ትክክል የሆነውን በማስቀደም በግል ንጽህና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

- የዓይን ማዝ
- እከክ
- ጉንፋን
- የሳንባ በሽታ (TB)
- ወስፋት ወዘተ መሆናቸውን ያስረዱዋቸው።

የነዚህ በሽታዎች መንስኤና የህመም ምልክትም በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ መጠቀሱን ይጠቁሚቸው።

### 1.3.3 ኤድስ በደም የሚተላለፍ በሽታ

ይህንን ትምህርት ለማነቃቂያነት የተጠየቁ ጥያቄዎችን ማለትም፡-

- ኤድስ ምንድነው?

- መንሲውስ?

- መተላለፊያውስ?

- እንዴት መከላከል እንደሚቻል በመጠየቅ ይጀምሩ። የተማሪዎቹን መልስ ተራ በተራ በቅደም ተከተል በጥያቄዎቹ መሰረት ያሰባስቡ። ተሳትፎአቸውንም ያድንቁ። ከዚያም ኤድስ እስካሁን መድሃኒት ያልተገኘለትና የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅም የሚያዳክም በሽታ መሆኑን፣ መንስኤውም ኤች አይ ቪ (HIV) የተባለ ቫይረስ እንደሆነ ያስረዱዋቸው።

መተላለፊያ መንገዱም በደም ንክኪ እንደሆነና መከላከያ መንገዱም፡- ማንኛውንም የደም ንክኪ ማስወገድ፣ ሌሎች በተጠቀሙበት ስለታም ነገር(ምላጭ)፣ ሹል ነገር(መርፌ)፣ የጥርስ ቡርሽ (መፋቂያ) አለመጠቀም ጥቂቶቹ መሆናቸውን ያስረዱዋቸው።

በተጨማሪም ዋና ዋናዎቹ የኤድስ በሽታ ምልክቶች፡-

- ክብደት መቀነስ፣
- ተከታታይ ትኩሳት፣
- የማያቋርጥ ሳል፣
- ከፍተኛ የሆነ ተቅማጥ፣
- የአፍ መቁሰል፣
- የሳንባ በሽታ (TB) መሆናቸውን ያስረዱዋቸው።

#### **1.3.3.1** አንድ ሰው በአደጋ ላይ የሚገኝ ከሆነ ለትልቅ ሰዎች በአስቸኳይ መንገር አለባችሁ።

ይህንን ትምህርት ለማነቃቂያነት የተጠየቁ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀመርና ትክክለኛ የሆነውን ምላሽ መሰረት በማድረግ አደጋ እንደመንስኤው ዓይነት የሚለያይና ሰውን ለችግር የሚዳርግ መሆኑን ይግለፁላቸው። አያይዘውም አደጋ ላይ የሚገኝ ሰው ቢያጋጥማቸው በአስቸኳይ ለሌሎች ሰዎች መንገርና ችግሩ እንዲቃለል ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዱዋቸው።

## **1.4.** የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች

የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምድ ምን ምን እንደሆነ ተማሪዎቹ እንዲገልፁ ያድርጉ። መልሶቻቸውንም ይቀበሉ፤ተሳትፎአቸውንም ያድንቁ። ከዚያም የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች የሚባሉትን ማለትም፡-

- ገላን መታጠብ፣
- ጥርስን ሁል ጊዜ ከምግብ በኋላ መፋቅና ማፅዳት፣
- የታጠቡ ልብሶችን መልበስ፣
- የመኖሪያ ቤትን ጽዳት መጠበቅ፣
- የትምህርት ቤት ግቢንና የመማሪያ ክፍሎችን ንጽህና መጠበቅ፣
- መፀዳጃ ቤትን መጠቀም፣
- የሰውና የእንስሳትን መኖሪያ መለየት፣
- ቆሻሻን የትም አለመጣልና ለቆሻሻ መጣያ የተዘጋጀ ዕቃን መጠቀም መሆናቸውን ይግለፁላቸው። አያይዘውም እነዚህ ተግባራት ቋሚና ሁል ጊዜ ተፈፃሚ መሆን እንዳለባቸው ማወቅ እንደሚገባቸው ያስረዱዋቸው።

### **1.4.1** ለሌሎች ጤንነት ኃለፊነት እንዳለብን ማሳየት።

ለሌሎች ጤንነት ኃለፊነት እንዳለብን እንዴት ማሳየት እንደሚቻል ተማሪዎቹ እንዲናገሩ ይጠይቁዋቸውና መልሶቻቸውን ይቀበሉ። ከዚያም የግል ንጽህና በተገቢው መንገድ መጠበቅ ለራስም ሆነ ለሌሎች ጤንነት ጠቃሚ እንደሆነና ከግል ንጽህና ጉድለት የመጣ የጤና መጓደል ቢያጋጥመን እንኳ ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለብን እንዲያውቁ ማስረዳት ያስፈልጋል። ከዚያም መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተጠቀሱ ምሳሌዎችን እንዲመለከቱ ይምከሯቸው።

## **4.** የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-

- ሥዕሎች
- ፖስተሮች
- ገላጭና ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ነገሮችንም መጠቀም ይቻላል።

## **5.** የመከታተያና የመገምገሚያ ስልቶች

- የግል ንጽህናን መጠበቅ ለምን እንደሚያስፈልግ መጠየቅና መገምገም፣

- የግል ንጽህና መጠበቂያ ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ እንዲገልጹ በማድረግ መገምገም፣
- የግል ንጽህናን ባለመጠበቅ ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮች፣ መንስኤአቸውንና የህመም ምልክቶቻቸውን እንዲገልጹ በማድረግ መገምገም፣
- ኤድስ ምን እንደሆነ፣ መንስኤው፣ መተላለፊያውንና መከላከያውን እንዲገልጹ በማድረግ መገምገም፣
- የግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶችን እንዲገልጹ በማድረግ መገምገም፣
- የግል ንጽህናን በሚገባ በመጠበቅ ለራስም ሆነ ለሌሎች ጠቃሚ መሆኑን እንዴት እንደሚገልጹ እንዲናገሩ በማድረግ መገምገም ያስፈልጋል።

የመልመጃ **1.5** መልሶች

ሀ/

1. ሐ
2. ሀ
3. ሐ
4. ሀ

ለ/

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት

የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ሀ/ 1. ለ 2. ሀ 3. ሠ

4. መ 6. ለ 7. ሐ

ለ/

1. እውነት 4. ሀሰት

2. እውነት 5. ሀሰት

3. እውነት 6. እውነት

ሐ/

1. ሠ
2. ሀ
3. መ
4. ለ
5. ሐ

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

## 2. ህብረተሰባችን

የተመደበለት ክ/ጊዜ ብዛት **- 53**

*መግቢያ*

ይህ ክፍለ ትምህርት አራት ዋና ዋና ርዕሶችና በርካታ ንዑስ ርዕሶች አሉት። እነሱም የህብረተሰባችን አባላት ርዕስ ስር በሚል "እንዴት መመደብ እንደሚቻልና ስለህፃናት መብቶች፣ በህብረተሰቡ ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚቻል በዚህም ውስጥ ስለ እለት እንቅስቃሴ ማቀድ፣ እራስን የማስተዳደር ክህሎቶችና በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ተሳታፊ ስለመሆን ይተነትናል። በተጨማሪም የህብረተሰባችን የኃይል ፍላጎቶችና የነዚህ ኃይል ምንጮችን በተመለከተና ምስሎችን ከሸክላ አፈር ከፕላስቲክ ጭቃና ከወረቀት እንዴት መስራት እንደሚቻል፣ የንድፍ ሥራና ማስጌጥ እንዴት እንደሚቻል በዝርዝር ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

ስለዚህ መምህራን በትምህርቱ የተጠቀሱትን በመከታተል የትምርህርቱን ዓላማ ከግብ ማድረስና ተማሪዎቹ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

አጠቃላይ ዓላማ

ተማሪዎች ይህን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፦

1. የአካባቢያቸውን ነዋሪዎች ዕድሜን መሠረት በማድረግ ይመድባሉ።
2. የህፃናት መብትን ይናገራሉ፣ እነዚህን የህፃናት መብቶች እንዴት ሰዎች እንደሚጥሱዋቸው ምሣሌ በመስጠት ያስረዳሉ። እነዚህ መብቶች እንዴት ሊጠበቁ እንደሚችሉ የመፍትሔ ሀሳብ ያቀርባሉ።
3. የቀን ተቀን ውሎአቸውን ያቅዳሉ እራስን በራስ መምራት ችሎታን ያሳያሉ። በአንዳንድ የማህበረሰብ ስራ ለመሣተፍ በእድሜያቸው መጠን ፍላጎት ያሣያሉ።
4. ለኅብረተሰቡ ኃይል ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ይገልፃሉ። በተጨማሪ የኃይል ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ ይገልፃሉ።
5. ሥዕልና ቅርፃ ቅርጽ ስራ በመለማመድ የተለያዩ ጌጦችን ይሰራሉ። የተለያዩ ቅርጻ ቅርጽ በወረቀትና በሸክላ በመሥራት ያሳያሉ።

6. በክፍለ ትምህርቱ ሳይንሳዊ የሆኑ ክህሎቶችን ያገኛሉ። ይኸውም አከባቢን በመመልከት፣ በመመዝገብ፣ በመጠየቅ፣ በመመደብ፣ በመለካት፣ ግንኙነት በመፍጠር፣ ምሣሌዎችን በመጥራትና አብሮ ተባብሮ በጋራ መስራት ናቸው።

## 2.1 የህብረተሰባችን አባላት

የተመደበው ጊዜ **- 15** ክፍለ ጊዜ

### 1. ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የተለያዩ የመንደራቸውን ነዋሪዎች እድሜን መሰረት አድርገው ምደባ ያደርጋሉ።
- እራሳቸውንም በየትኛው ምድብ እንደሚያገኙ ያስረዳሉ።
- የህፃናት መብትን ለይተው ያውቃሉ፣ ይዘረዝራሉ።
- የህፃናት መብት እንዴት እንደሚደፈሩ ምሣሌ በመስጠት ያስረዳሉ።
- የህፃናት መብት በምን መንገድ ማስጠበቅ እንደሚቻል ሀሣብ ይሰጣሉ።

### 2. ዝርዝር ይዘቶች

### 2.1 የህብረተሰባችን አባላት

**2.1.1** የህብረተሰባችን አባላት መመደብ

**2.1.2** እናንተ በየትኛው የህብረተሰብ ምድብ ናችሁ□

**2.1.3** ምን ዓይነት መብቶች አሉን□

- የህፃናት መብት
- የህፃናት መብት አለማክበር
- የህፃናት መብት ማስከበር
- የህፃናት ችግር ሲገጥማቸው ማን መብታቸውን እንደሚያስከብርላቸው።

### 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በመጀመሪያ ዋናውን ርዕስ ያስተዋውቁና በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ በመማር ሂደት የሚያገኟቸውን መታወስ የሚገባቸው ነጥቦችና ዓላማውን ግንዛቤ እንዲይዙ ያድርጓቸው።
- ከዚያም የመጀመሪያውን ንዑስ ርዕስ ያቅርቡና ቁልፍ ቃላቶችን እንዲያውቁ በማድረግ ለማነቃቂያ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲነጋገሩና ለመመለስ እንዲሞክሩ ጊዜ ይስጧቸው። ጥያቄዎቹን በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመፃፍ ወይም በማንበብ ሊሆን ይችላል።
- የህብረተሰብ አባላት እድሜን መሰረት በማድረግ ህፃን፣ ወጣት፣ ጎልማሳና ሽማግሌ ብለን እንደምንመድባቸው ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ። መድበውም ከጨረሱ በኋላ ምን ያህል የቤተሰባቸው አባላት በየትኛው ምድብ ውስጥ እንደሚገኙ መጠየቅ።
- እራሳቸውን የህብረተሰብ በትኛው ምድብ ውስጥ እንደመደቡ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ።
- ህፃን መሆን ያለውን ጠቀሜታና ጉዳት እንዲናገሩ ተማሪዎችን መጠየቅና ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ። በተጨማሪም እርስዎ ማብራሪያ ይስጧቸው። ከዚህ ጋር በተገናኘ ነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች ህፃናት መሆናቸውን ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ።
- አንድ ሰው በእድሜው ከአንድ የእድሜ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ ወይም ምድብ እንደሚተላለፍ በተማሪዎች መጽሀፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው ዘርዝረው ያብራሩላቸው።
- ተማሪዎች ህፃናት ምን ምን እንደሚያስፈልጋቸው ወይም ሊሟሉላቸው ይገባል በሚል እንዲወያዩበት ማድረግና የሚወያዩበት ርዕስም ለመኖር እራሳቸውን ለመከላከልና ለእድገታቸው በማለት መሠረታዊ የሆኑ ሁኔታዎችን እንዲያውቁ ማድረግ።
- ተማሪዎች ስለ ህፃናት መብት በዝርዝር እንዲረዱ በግልፅ የተለያዩ መሠረታዊ ጉዳቶችንና ምሳሌዎችን እያጣቀሱ ማስረዳት። የሚከተሉት መብቶች የበለጠ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፦
    - የመማር መብት፣
    - በአደገኛ ሥራ ያለመሰማራት መብት፣

- ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የማግኘት መብት ናቸው።

- ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑና የተለያዩ የህፃናት መብቶች ረገጣ የሚያሳዩ ጽሁፎችን በማንበብ ተማሪዎች እንዲወያዩበት ማድረግ፣
- የህፃናትን መብት ለማስከበር በትምህርት ቤትና በአከባቢው የሚደረጉ ጥረቶችን ማስተዋወቅ መወያየት።
- እናንተ ችግር ቢገጥማችሁ የት ትሄዱና መብታችሁን ታስከብራላችሁ የሚል የመወያያ ጥያቄ በመጠየቅ እንዲመልሱና እንዲወያዩበት ማድረግ።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ህፃን፣ ወጣት፣ ጎልማሳንና ሽማግሌን የሚገልፅ ስዕል ወይም ፎቶግራፍ ወይም በተማሪዎች መፅሐፍት ላይ የተቀመጠውን ሥዕል 2/1 መጠቀም።
- ስለ ህፃናት መብት መከበር ወይም አለመከበር የሚያሳዩ ፖስተሮች፣ ጽሁፎችና የመሳሰሉትን መጠቀም።
- መብታቸው የተጠበቀላቸው ህፃናት ሥዕል 2/2።
- ህፃናት በጥናት ላይ ሳሉ የሚያሳይ ሥዕል 2/3።

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- የአከባቢውን ህብረተሰብ ዕድሜን መሠረት በማድረግ በተለያዩ ክፍሎች መመደብ እንደቻሉ መጠየቅና መገምገም እራሳቸውን በየትኛው ምድብ እንዳካተቱ መጠየቅና መገምገም፣
- የህፃናትን መብት እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የህፃናት መብት እንዴት እንደሚጣሱ ምሳሌ በመስጠት በየትኛው ምድብ እንዳካተቱ መጠየቅና መገምገም።
- የህፃናትን መብት እንዴት እንደሚጣሱ ምሳሌ በመስጠት እንዲያስረዱ ማድረግና እንዴት መጠበቅና ማስከበር እንደሚቻል እንዲናገሩ ማድረግ።

## ሀ) የመልመጃ 2.1 መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት

4. እውነት

5. እውነት

6. ሐሰት

7. ሐሰት

ለ)

1. ህፃን፣ወጣት፣ ጎልማሳና ሽማግሌ፣

2/ ሀ. ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ለ. ፍቅርና እንክብካቤ ማግኘት፣

ሐ. የመማር መብት፣

መ. በአደገኛ ስራ ያለመሰማራት መብት፣

ሠ. ምግብ፣ልብስና መጠለያ የማግኘት፣

ረ. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ የመኖር መብት ናቸው።

## 2.2. በህብረተሰቡ ውስጥ መኖር

የተመደበለት ክ/ጊዜ ብዛት **- 14**

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የቀን ተቀን ውሎዋቸውን ዕቅድ የመንደፍና የመጠቀም ችሎታ ይኖራቸዋል።
- በእራሳቸው የእድሜ መጠን እራሳቸውን የማስተዳደር ክህሎትን ያሳያሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

- የዕለት እንቅስቃሴን ማቀድ
    - የቀን ወይም የሣምንት እንቅስቀሴን ማቀድና መፃፍ
- እራስን የማስተዳደር ክህሎት
- በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ተሳታፊ መሆን
    - በክበባት መሳተፍ /ኤድስ ክበብ፣ የአከባ እንክብካቤ ክበብ፣ የልጃገረዶች ክበብ ወዘተ./

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በመጀመሪያ በርዕሱ ስር የተቀመጡትን ቁልፍ ቃላት በማንበብ እንዲያውቁ ያድርጓቸው።
- በመቀጠልም በህብረተሰቡ ውስጥ መኖር ሲባል ምን ማለት እንደሆነና መልካም ማህበራዊ ግንኙነት እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ግንዛቤ እንዲይዙ በማነቃቂያ ጥያቄ ትምህርቱን መጀመር። ተማሪዎቹ የሚያውቁትን እጅ እያወጡ ተራ በተራ እንዲመልሱ ማድረግና የሰው ልጅ አብሮ ሲኖር በተለያዩ መንገዶች እንደሚገናኝና ከሰዎች ጋር መግባባት፣መከባበር፣መፋቀር፣ወዘተ ሲኖረን በህብረተሰቡ ውስጥ መልካም ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር እንደምንችል ያስረዷቸው።
- ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ሰው መልካም ዜጋ እንደሆነ በማብራራት ከጓደኞቻቸው ጋር የሚኖራቸውን መልካም ግንኙነት ለምን እንደሚጠቅማቸው እንዲወያዩ ማድረግ።
- በየዕለቱ ለሚያከናውኗቸው ጉዳዮች ዕቅድ እንዳላቸው መጠየቅና ተራ በተራ እጅ እያወጡ እንዲመልሱ ማድረግ። ዕቅድ ማለት አንድን ነገር በፕሮግራም መስራት ማለት እንደሆነ የተለያዩ ምሣሌዎችን በመስጠት ግንዛቤ ማስያዝ።

- ጊዜን በዕቅድ መጠቀም በሚል ርዕስ በተማሪዎች መማሪያ መፅሐፉ ላይ የቀረበውን ውይይት ለክፍሉ ተማሪዎች በማቅረብ ከውይይቱ ምን ትምህርት እንዳገኙና ጊዜያቸውን እንዴት ለመጠቀም እንዳቀዱ መጠየቅ።
- በቀን ውስጥ የሚያደርጓቸውን የተለያዩ ተግባራት ለይተው እንዲያወጡ በማድረግ እነዚህም የመኝታ ጊዜ፣የምግብ ጊዜ፣የጥናት ጊዜ፣የጨዋታ ጊዜ፣የቤት ስራ ጊዜ፣የስራ ጊዜ በማለት እንዲከፋፍሉ ማድረግ።
- ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ለማከናወን በቀን ውስጥ ያሉትን ጊዜያት እንዴት እንደሚያከፋፍሉት እንዲያስቡና እንዲወያዩ ማድረግ።

- ከዚህም በኋላ ተማሪዎች የከፋፈሉት ተግባራትና በቀን ውስጥ ያሉትን ጊዜያት እንዲጠቀሙበት የተዘጋጀውን ተግባራዊ ክንዋኔን ግንዛቤ እንዲይዙ ማስረዳትና በተግባር እንዲሰሩ ማድረግ።

- ለህፃን ልጅ ልብሱን ወላጆቹ እንደሚያለብሱት ምግቡንም እንደሚያበሉት ማስተዋላቸውንና እነሱም ህፃን በነበሩበት ወቅት ቤተሰቦቻቸው ያለብሱዋቸው እንደነበር በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር።
- አሁን ልብሳቸውን ማን እንደሚያለብሳቸውና ትምህርት ቤት በራሳቸው መምጣት እንደቻሉ መጠየቅ።
- ልጆቹ እያደጉ ሲሄዱ የሚፈልጉትን ነገር እራሳቸው መስራት እንደሚጀምሩ ማስረዳት።

- ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ደብተራቸውና ብዕራቸው ማን እንደሚጠብቅላቸው በመጠየቅና በቤት ውስጥ ማንም ሳይረዳቸው የሚሰሩትን ስራ በዝርዝር ጽፈው ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ ማድረግ።
- በመንደራቸው የሚኖሩ ሰዎች በጋራ በመሆን ሲያከናውኗቸው የተመለከቱትን የተለያዩ ተግባራት በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር።
- የግለሰቦች አስተዋፅኦ የቡድን አሰተዋፅኦ በመሆን የማህበረሰቡ እንቅስቃሴ አካል እንደሆነ ማሳየት።

- ከማህብረሰቡ እንቅስቃሴ ጋር በሳምንት ወይም በወር ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የግል እንቅስቃሴ ያደረጉትን እንዲናገሩ ተማሪዎችን መጠየቅ። ለምሳሌ የአካባቢ ፅዳት፣ችግኞችን መትከል የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህም በኋላ በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን ተሳትፎ የተመለከተ በሣምንት ወይም በወር ዕቅድ እንዲያወጡ መርዳት።
- የተማሪዎችን የክበብ ተሳትፎ በመጠየቅ እንዲወያዩ በማድረግ ትናንሽ ክበቦች እንዴት ማቋቋም እንደሚቻል ሃሳብ በማፍለቅ መርዳት።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ♦ የህብረተሰብን ተሳትፎ የሚያሳይ ፎቶ፣ፖስተሮች ወይም ስዕል፣
- ♦ የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ የተዘጋጀ ቻርት፣
- ♦ የተለያዩ የትምህርት ቤት ክበባት ፖስተር ወይም ፓምፕሌት።

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ♦ በህብረተሰቡ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ስላላቸው ፍላጎት መጠየቅ፤
- ♦ የዕለት እንቅስቃሴያቸው ዕቅድ እንዲያወጡ በማድረግ መገምገም፤
- ♦ በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉት ክበባት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፤
- ♦ በክበባት ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት መገምገምና አባል ያልሆኑት አባል ለመሆን የሚያስችላቸውን ሁኔታ እንዴት መፍጠር እንዳለባቸው መጠየቅ።

## 6. የመልመጃ 2.2 መልሶች

| | |
|---|---|
| ሀ/ 1. እውነት | ለ/ 1. ዕቅድ |
| 2. እውነት | 2. የጊዜ |
| 3. ሐሰት | 3. ጊዜን |
| 4. እውነት | 4. የህብረተሰቡን እንቅስቃሴ |
| 5. ሐሰት | |

## 2.3. ህብረተሰባችን ኃይል ያስፈልገዋል

የተመደበለትክፍለ ጊዜ-**12**

## 1. ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- ኃይል ለህብረተሰቡ ምን ዓይነት ጥቅም እንደሚሰጥ ይገልፃሉ።
- የኃይል ምንጮችን ስም ይዘረዝራሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- የኃይል ፍላጎት
- የኃይል ምንጭ

## 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ይህንን ትምህርት ኃይል ለምን እንደሚያስፈልገን በመጠየቅ ይጀምሩና ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ይገፋፏቸው። የሚሰጡትን መልስ በማድነቅ ከተቀበሉ በኋላ ከቤታቸው በመጀመር ኃይል ምግብ ለማብሰልና ቤታችንን ለማሞቅ እንደሚያስችለንና የረጠቡ ልበንሶቻችንን በፀሀይ ኃይል ማድረቅ እንደምንችል አትኩሮት በመስጠት ማስረዳት ተገቢ ነው።

- ለመጓጓዣነት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎችና የተለያዩ መሣሪያዎች ኃይል እንደሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ከቤንዚንና ከናፍጣ ኃይላቸውን እንደሚያገኙ በመጠቆም አብዛኛዎቹ መሣሪያዎች ግን የኤሌክትሪክ ኃይልን እንደሚጠቀሙ ማስረዳት።
- ተማሪዎች የኃይል ምንጮች ምን እንደሆኑ እንዲወያዩ በማድረግ ኃይልን ከተለያዩ ምንጮች ልናገኝ እንደምንችል ገለፃ መስጠት።

  - በአጠቃላይ የኃይል ምንጮች የምንላቸውን በሶስት እንመድባቸዋለን፤
    - የሀገር ውስጥ የኃይል ምንጮች

      ምሳሌ ማገዶ፣ የድንጋይ ከሰል
    - የመጓጓዣ የኃይል ምንጮች

      ምሳሌ ናፍጣና ቤንዚን
    - የተፈጥሮ የኃይል ምንጭ

- ኤሌክትሪክ የኃይል ምንጭ እንዳልሆነና ለአጠቃም በሚመች መልኩ ተቀይሮ የምናገኘው ኃይል እንደሆነ በማስረዳት ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ።
- ከዚህም በመቀጠል ለእያንዳንዱ የኃይል ምንጭ ዘርዘር ያለ መወያያ ሀሳብና ገለፃ በተማሪዎች መፃፍ ላይ ተካትቷል። በእያንዳንዱ የኃይል ምንጭ ሥር የተሰጡትን የመወያያ ጥያቄ ካወያዩዋቸው በኋላ የማጠናከሪያ ገለፃ ያድርጉላቸው።
- በመጨረሻም አራት ተግባራዊ ክንዋኔዎችና የተግባር ጥያቄዎች በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተቀምጧል። እነዚህ የተግባር ክንዋኔዎችን ተማሪዎች በቤታቸውና በቤተ ሙከራዎች ውስጥ እንዲተገብሯቸው ጥያቄውንም እንዲመልሱ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነው።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የኃይል ምንጮችን የሚገልፅ ሥዕላዊ መግለጫ
- ኩራዝ፣ የባትሪ ድንጋይ፣ ኤሌክትሪክ ገመድ፣ የባትሪ ዓይን ወይም አምፑል፣ ስስ ወረቀት፣ የኩራዝ ክር፣ ናፍጣ፣ ክብሪትና የእጅ ሌንስ ለተግባራዊ ክንዋኔዎች የሚረዱ ናቸው።

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ኃይል ለምን እንደሚያስፈልግ በመጠየቅ መገምገም፣
- የኃይል ምንጮችን ለይተው እንዲናገሩና እንዲያስረዱ ማድረግ፣
- ሰውነታችን ኃይል ለምን እንደሚያስፈልገው በመጠየቅ መገምገም፣
- ተግባራዊ ክንዋኔውን በቤተ ሙከራ ከተማሩ በኋላ በቤታቸው እንዲሞክሩት የቤት ሥራ መስጠትና ተግባራዊ ክንዋኔዎችን መልስ እንዲሰጡ በማድረግ መገምገም፣

## የመልመጃ 2.3 መልሶች

1. እውነት
2. ሀሰት
3. ሀሰት

4. እውነት
5. እውነት

1. መ
2. ሀ
3. መ
4. ሐ
5. መ

## 2.4 ምስሎችን ከሽክላ አፈር ከፕላስቲክ ጭቃና ከወረቀት መስራት

### 1. ዝርዝር ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የምስሎችን የመጀመሪያ ንድፍ ማሳየት ይችላሉ።
- ማጣበቂያዎችን በመጠቀም በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉ በወረቀት ጌጦችን ይሰራሉ።
- ቀላል የሆኑ ምስሎችን ከሸክላ አፈር - ከፕላስቲክ ጭቃና ወረቀት መስራት ይችላሉ።

### 2. ዝርዝር ይዘቶች

- የንድፍ ሥራ
- ማስጌጥ
- ምስሎችን መስራት

### 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በመጀመሪያ ተማሪዎችን ሳጥን፣ በር፣ መስኮትና ጎጆ መሳል እንደሚችሉ በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምራሉ። አንድ እቃ ከመስራታችን በፊት ዕቃውን ወይም ቁሱን የሚመስል ወረቀት ላይ ይሳላል። ይህ በወረቀት ላይ የሚሳለው ስዕል መሰል ስራ ንድፍ ይባላል። የሚለውን ሀሳብ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ።
- አንድ ነገር ቅርጻ ቅርፆችን ንድፍ ለማሳየት መስመሮችን መጠቀም እንደሚገባና መስመሮችን በማስመሪያና ያለ ማስመሪያ እንዴት መስራት እንደሚችሉ ግንዛቤ ማስጨበጥ።
- መስመሮችን የማስመር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ በተግባራዊ ክንዋኔዎች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እያንዳንዱ ተማሪ በክፍል ውስጥ በማስመሪያና ያለ ማስመሪያ መስመሮችን እንዲሰሩ ማድረግ።
- ቀጥሎ በተግባራዊ ክንዋኔ 2.7 እና 2.8 ላይ የተሰጡትን ባለ ጎነ ስስትና ባለ አራት ምስሎችን መስራት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱት ማድረግ።
- ማስጌጫዎችን ከወረቀት፣ ከአፈርና ከሸክላ ጭቃ መስራት እንዲሚቻል ግንዛቤ ማስጨበጥ።

- ማስጌጫዎችን ከወረቀት እንዴት እንደሚሰራና ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በተማሪዎች መማሪያ መፃህፍት ላይ ተቀምጧል።
- ከወረቀቶች ፖስታንና ሆላንዶን እንዴት መስራት እንደሚቻል በተግባራዊ ክንዋኔ ውስጥ ተካትቷል። ይህንንም ተማሪዎች በተግባር በክፍል ውስጥ ልምምድ እንደሚያደርጉ መረዳት።
- ተማሪዎች ስለሸክላ ስራና በሸክላ አፈር ምን ምን እንደሚሰራ ግንዛቤ እንዲይዙ ማብራሪያ በመስጠት ተማሪዎችን መርዳት። ተማሪዎችም በአከባቢያቸው ያሉትን ከሸክላ አፈር የተሰሩ ቁሳቁሶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- ለወረቀት ሥራ የሚያገለግሉ መቀስ፣ ኮላ፣ ወረቀት፣ መርፌ፣ ክር ገመድ፣ ከለር፣ ማስመሪያ።
- የሸክላ ድስት፣ ጀበና ገንቦ ጣባና ጡብ ፣
- የፕላስቲክ ጭቃ፣
- የሸክላ አፈር

## 5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- የአንድን ነገር ንድፍ መስራት እንደሚችሉ በማሳየት ብቃታቸውን መገምገም።
- ማጣበቂያዎችን በመጠቀም በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉ በወረቀት ጌጦችን እንዲሰሩ በማስረደግ መገምገም።
- ቀላል የሆኑ ቅርፃ ቅርጾችን ከሸክላ፣ ከፕላስቲክና ከወረቀት እንዲሰሩ በማዘዝ መገምገም።

ክፍለ ትምህርት - ሶስት

## 3. የአከባቢያችን ተፈጥሮ

የተመደበው ጊዜ 58 ክ/ጊዜ

መግቢያ

ክፍለ ትምህርት ሶስት የሚከተሉት ንዑስ ርዕሶች አሉት። እነሱም የተፈጥሮ ክስተት፣ የተፈጥሮ ክስተትን መመልከት፣ የህይወት ምዕራፎች፣ ቁሳቁሶችን መመደብ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የተፈጥሮ ዓይነቶች፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት ዓይነቶች፣ የተፈጥሮ ጥበቃ፣ የተፈጥሮ ጥበቃ በቤትና በትምህርት

ቤት፣ በአከባቢያችን የሚገኙ እፅዋት ክፍሎችን መሰብሰብና ማስቀመጥ፣ እፅዋቶችን ማሳደግ፣ እፅዋት ለማደግ ምን ያስፈልጋቸዋል፣ እፅዋትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮች፣ በአከባቢያችን የሚገኙ እንሰሳት፣ እንሰሳትን መመደብ፣ የእንሰሳት ተዋፅኦ፣ ለእንሰሳት እርባታ የሚስፈልጉ መሣሪያዎች፣ በህይወት ላሉ እንሰሳት አክብሮት መስጠት፤ የሚሉ በዝርዝር መጤን የሚገባቸው ትምህርቶች ናቸው።

በዚህ መሠረት መምህራን በክፍል ትምህርቱ የተጠቀሱትን በመከታተል የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ተማሪዎቹ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

አጠቃላይ ዓላማ

ተማሪዎቹ ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

1. አንዳንድ የተፈጥሮ ክስተቶች ተፈጥሮአዊ ዑደት ያላቸው መሆኑንና አንዳንዶቹ ደግሞ በድንገት የሚከሰቱ መሆናቸውን ይገልፃሉ።
2. የመለኪያ መሣሪያዎችን መጠናቸውን ይለያሉ፣ ባህላዊና ዘመናዊ በማለትም ይመድባሉ።
3. የተለያዩ ነገሮችን በተፈጥሮ የሚገኙና ሰው ሰራሽ በማለት ይለያሉ።
4. የተፈጥሮ ሀብትን ዓይነት፣ አጠቃቀምና ጥበቃን ያስረዳሉ።
5. የእፅዋትን ክፍሎች ያሣያሉ፣ የእፅዋትን ክፍሎች ይሰበስባሉ፣ የተለያዩ የእፅዋት ክፍሎችን ተግባር ይዘረዝራሉ።
6. ዘሮች ለማደግ ምን ምን እንደሚያስፈልጋቸው ይገልፃሉ።
7. እንሰሳትን በመዋለጃቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በአኗኗራቸውና በሰውነት ሽፋናቸው ላይ መሰረት ያደረገ ምደባ ያደርጋሉ።
8. የእንሰሳት ተዋፅኦ የሆኑ የተለያዩ ምርቶችና ለእንስሳት እርባታ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ይገልፃሉ።
9. ሣይንሳዊ የሆኑ ክህሎቶችን ለምሣሌ፡- አካባቢን መመልከት፣ መመደብ፣ መጠበቅ፣ መመዝገብ፣ ግንኙነትን፣ ምስል መስራትንና በጋራ መስራት መቻልን ወዘተ በተግባር ያሳያሉ።

## 3.1 የተፈጥሮ ክስተት

የተመደበው ጊዜ **17** ክ/ጊዜ

## 1. ዝርዝር ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ወቅቶችን፣ ቀንና ሌሊትን እንዲሁም የህይወት ደረጃ የተፈትሮ ዑደት መሆናቸውን ይመረምራሉ።
- ቀስተ ደመና፣ ድርቅና የጎርፍ መጥለቅለቅ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ መሆናቸውን ይመረምራሉ።
- የርዝመት፣ የክብደትና የጊዜ መለኪያዎችን ይገልፃሉ።
- መለኪያዎችን ዘመናዊና ባህላዊ በማለት ይከፍላሉ።
- ቁሳቁሶችን ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሰራሽ ብለው ይገልፃሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

የተፈጥሮ ክስተቶችን መመልከት

- ቀንና ሌሊት
- ወቅቶች
- ድርቅ
- ቀስተደመና

የህይወት ምዕራፎች

- መለኪያዎች
  - የርዝመት
  - የመጠን
  - የጊዜ
  - ዘመናዊና ባህላዊ መለኪያዎች
  - ቁሣቁሶችን መመደብ

## 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ በቅድሚያ ዋናውን ርዕስ ያስተዋውቁና በክፍለ ትምህርቱ ርዕስ ሥር የሚያገኙዋቸውን ቁልፍ ቃላትን በማንበብ እንዲያቁዋቸው ያድርጉ። ከዚያም የመጀመሪያውን ንዑስ ርዕስ ያቅርቡና ለማነቃቂያነት በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎቹ እንዲናገሩና ለመመለስ እንዲሞክሩ ጊዜ ይስጧቸው። ይህንን ሲያደርጉ ጥያቄዎቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ወይም በማንበብ ሊሆን ይችላል።

ከዚያም የተማሪዎቹን ምላሽ ያሰባስቡ፣ ስለተሣተፎአቸው ያመስግኑና ስለ ክስተት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እንተብራራው ክስተት ሰው በስሜት ህዋሳቶቹ (ዓይን፣ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ወዘተ) ሊረዳው (ሊቀበለው) የሚችልና በዚህም ምክንያት በሰው አእምሮ ውስጥ የሚፈጠረውን ምስል የሚያሳይ ጊዜን ጠብቆ የሚከሰት ወይም በድንገት (በአጋጣሚ) የሚከሰት ነገር መሆኑን በዑደት ለሚከሰት ቀንና ሌሊትን፣ በድንገት ለሚከሰት ደግሞ ድርቅን እንደምሳሌ ጠቅሰው ያስረዱዋቸው።

## 3.1.1 የተፈጥሮ ክስተትን መመልከት

የተፈጥሮ ክስተት ዓይነትን በተመለከተ የተፈጥሮ ክስተት ዓይነት ልክ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ በተገለፀው መሰረት በዝርዝር ጥቁር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ከዚያም በዑደትና በድንገት የሚከሰቱትን ተማሪዎቹ ለይተው እንዲናገሩ ያድርጉና ምላሻቸውን ይቀበሉ። ትክክለኛውን ምላሽ መሠረት በማድረግ በዑደት የሚከሰቱት የተፈጥሮ ክስተቶች፣ ቀንና ሌሊት፣ ወቅቶችና የህይወት ምዕራፎች፣ ወዘተ መሆናቸውንና በአጋጣሚ የሚከሰቱት ደግሞ ድርቅ፣ የጎርፍ መጥለቅለቅና ቀስተ ደመና፣ ወዘተ እንደሆኑ አብራርተው ያስረዱዋቸው። በተጨማሪም ተማሪዎቹ ስለወቅቶች፣ ቀንና ሌሊት፣ ድርቅና የጎርፍ መጥለቅለቅ መንስኤና የሚደርሰውን ጉዳት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስለ እያንዳንዱ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን መጠየቅና ምላሽ (ማብራሪያ) መስጠት አስፈላጊ ነው።

በመጨረሻም ስለቀስተደመና አፈጣጠርና ቀለማት ተማሪዎቹ እንዲገልፁ ያድርጉና የቀስተደመናን ሥዕል የቀለማቱን አቀማመጥ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ሥለው እንዲያቀርቡ በማድረግ በንዑስ ርዕሱ ውስጥ የተጠቀሱትን ይዘቶች እንደገና ጠቅሰው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

## 3.1.2 የህይወት ምዕራፎች /ደረጃዎች/

ትምህርቱን ሲጀምሩ ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ እንዲሞክሩና እንዲመልሱ ያድርጉ። ይህንንም ሲያደርጉ ጥያቄዎቹን በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ከዚያም የተማሪዎቹን ምላሽ ያሰባስቡና ልክ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በተገለፀው መሠረት የህይወት ደረጃ ማለት ህይወት በተለያዩ የእድገት ደረጃ (ጊዜ) ውስጥ መሆኑን

ያስረዱዋቸው። በተጨማሪም በሥዕል 3.4 የቢራቢሮ እድገት ደረጃንና በሥዕል 3.5 የእጽዋት እድገት ደረጃን በሚገባ እንዲያጤኑ ያድርጉ።

በመጨረሻም የህይወት ምዕራፎች የተፈጥሮ ክስተት መሆናቸውን እያንዳንዱ የህይወት ምዕራፍ የራሱ የሆነ ባህሪይ ያለውና በሁሉም ህይወት ያለው ነገር ላይ የሚንፀባረቅ መሆኑን ገልፀው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

### **3.1.3** መለኪያዎች

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ተማሪዎቹን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይጀምሩ። በአከባቢቸው ሰዎች እንዴት እንደሚገበያዩ ይጠይቋቸው። ለምሣሌ፡- ሱቅ ውስጥ ብትን ነገሮችን (ጨው፣ ስኳር፣ ቡና፣ ወዘተ) እንዴት እንደሚሸጡና እንደሚገዙ፣ ልብስ ለማሰፋት ሲፈልጉ ልብስ ስፌት ቤት ሄደው እንዴት እንደሚያሰፉ፣ ማስመሪያቸውን ለምን እንሚጠቀሙበት፣ ወዘተ ይጠይቋቸው። ከዚያም ለማነቃቂያነት የቀረቡትን ጥያቄዎች በተጨማሪ ይጠይቋቸውና ጊዜ ሰጥተው መልሶቻቸውን ይቀበሉዋቸው። አያይዘውም ዋና ዋና የመለኪያ ዓይነቶች፡- የርዝመት፣ የመጠን ወይም የክብደትና የጊዜ መሆናቸውን ያስረዱዋቸው።

የእያንዳንዱን መለኪያ መጠን (ትንሹንና ትልቁን) ለይተው ያስረዱዋቸው። በተለይ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተገለፁትን ተግባራዊ ክንዋኔዎች አስፈላጊው መለኪያ በክፍል ውስጥ ቀርቦ አሰራሩን ተማሪዎቹ እንዲተገብሩ ማድረግ ትምህርቱን ተጨባጭ የሚያደርግ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው።

የጊዜን መለኪያ በተመለከተ፡- ጊዜ እንደርዝማኔው በተለያየ መንገድ እንደሚለካ ማስረዳት ያስፈልጋል። ለምሣሌም፡- በሰኮንድ፣ በደቂቃ፣ በሰዓት፣ በቀናት፣ በሳምንታት፣ በዓመታት፣ ወዘተ መለካት እንደሚቻል እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

መለኪያዎች ዘመናዊና ባህላዊ (ተለምዶ) ተብለው በሁለት የሚመደቡ መሆኑን መግለፅ። ልዩነታቸውንም ዘመናዊ መለኪያ መሣሪያ የልኬት መጠኑ (ቁጥሩ) በላይ ላይ የተገለፀ መሆኑን፣ የተለምዶ መለኪያ ደግሞ ሰዎች የተለያዩ የአካል ክፍላቸውን (እጅና እግር)፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን የሚለኩበት ዘዴ እንደሆነ የተለያዩ

የተለምዶ መለኪያዎችን (ሥንዝር፣ ክንድ፣ እርምጃ፣ ቁና፣ ጋሻ፣ ወዘተ) በመጥቀስ ማስረዳት ይጠበቃል።

### **3.1.4** ቁሳቁሶችን መመደብ

የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ዓላማ ተማሪዎቹ አከባቢያቸውን በሚገባ ተረድተው በአከባቢቸው የሚገኙ ነገሮችን ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ መመደብ እንዲችሉ ለማድረግ ስለሆነ ትምህርቱን ሲጀምሩ ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ በማድረግ ትክክለኛውን መልስ በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ በተገለፀው መሠረት በተፈጥሮ አከባቢችን የሚገኙ ነገሮች፡- ህይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸው፣ በተፈጥሮ የሚገኙና ሰው ሰራሽ ህይወት የሌላቸው፣ ህይወት ያላቸው ደግሞ እፅዋትና እንስሳት እያልን የምንመድባቸው መሆኑን ለእያንዳንዱ ምድብ ምሳሌ በመጥቀስ አብራርተው ያስረዱዋቸው።

በተጨማሪም የስሜት ህዋሶቻችንን በመጠቀም የተለያዩ በአከባቢችን የሚገኙ ነገሮችን ባህሪይ መለየት የሚቻል መሆኑን ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

ይህንንም ሲያደርጉ ተማሪዎችን ስንት የስሜት ህዋሳቶች እንዳሏቸውና የእያንዳንዱን የስሜት ህዋስ ተግባር እንዲገልጹ ያድርጉ። ከዚያም አንድ ተማሪን በማስነሳት ዓይኑን በመሀረብ (ሻሽ) እንዲሸፍን በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን (ጥቁር ሠሌዳ፣ ዴስካቸውን፣ ግድግዳውን፣ ብዕሮችን፣ እርሳሶችን፣ ወዘተ) በእጆቹ እየዳሰሰ (እየነካ) ምን እንደተሰማው እንዲናገር (እንዲገልፅ) ያድርጉ። በመጨረሻም በመቅመስ ነገሮችን ለመለየት መሞከር ለጉዳት የሚዳርግ በመሆኑ ያልታወቁ ነገሮችን እንዳይቀምሱ በማስረዳት ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

## **4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለያዩ ሥዕሎች
    - የርዝመት
    - የመጠን
    - የጊዜ መለኪያ ሥዕሎች

## **5.** የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ወራትን (ወቅቶች)፣ ቀንና ሌሊት ተፈጥሮአዊ ክስተቶች መሆናቸውን ማወቃቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገመገም።
- ቀስተደመናና የውሃ መጥለቅለቅ በአጋጣሚ የሚከሰቱ ሁኔታዎች መሆናቸውን ማወቃቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገመገም።
- የርዝመት፣ የመጠን ወይም የክብደትና የጊዜ መለኪያዎችን ለይተው ማወቃቸውን ጥያቄ ጠይቆ መገምገም።
- በአከባቢቸው የሚገኙ የተለያዩ ነገሮችን ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ በማለት መመደብ መቻላቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- መለኪያዎችን ባህላዊ (የተለምዶ) ና ዘመናዊ በማለት መመደብና ምሣሌ መስጠት መቻላቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።

የመልመጃ **3/1** መልሶች

ሀ/

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት

ለ/

1. ሐ
2. መ
3. ለ
4. ረ
5. ሀ

ሐ/

1. ድርቅ፣ የውሃ መትለቅለቅና ቀስተደመና
2. ቀንና ሌሊት፣ የህይወት ደረጃዎች
3. ቀን፡- ብርሃንማ፣ ሞቃት፣ ከፍተኛ ድምፅ፣ ወዘተ
   ሌሊት፡- ጨለማማ፣ ቀዝቃዛ፣ ዝቅተኛ ድምፅ፣ ወዘተ
4. ድርቅ፡- በዝናብ እጥረት(ለረጅም ጊዜ)፣ በበጋው መራዘም
   የጎርፍ መጥለቅለቅ፡- ረዘም ላላ ሰዓት ከባድ ዝናብ መጣልና በዚህም የተነሳ ወንዞች ከመጠን በላይ ሞልተው ሲፈሱ ወዘተ የሚከሰት።
5. ይህንን ጥያቄ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያለውን ሥዕል ወይም ከሌላ ቦታ የቀስተ ደመና ሥዕል አስመስለው መሣል ይጠበቅባቸዋል።

**የመልመጃ 3/2 መልሶች**

ሀ/

1. እንቁላል
2. አራት
3. ውሃ፣ አየር፣ (ኦክስጂን)ና ሙቀት
4. በዑደት የሚከሰቱ
5. የአበበ ዛፍ

**የመልመጃ 3/3 መልሶች**

ሀ/

1. 17 ኪሎ ግራም
2. 40.000 መ $^2$
3. በአብዛኛው ግማሽ ሜትር (50 ሣ.ሜ) ሲሆን እንደላኪው ክንድ ርዝመት ይለያያል።
4. $24\times60 =$ 1440 ደቂቃ

ለ/

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት

**የመልመጃ 3/4 መልሶች**

ሀ/

1. በሁለት
2. በሁለት
3. በቆዳችን የስሜት ህዋስ (በመዳሰስ)
4. በመቅመስ
5. በማየት

ለ/

1. ድንጋይ፣ አፈር፣ አየር፣ ወዘተ
2. ወንበር፣ መስታወት፣ ሬድዮ፣ መኪና፣ ወዘተ
3. ጠንካራ፣ ሸካራ፣ ለስላሣ፣ ወዘተ

## **3.2** የተፈጥሮ ሀብት

የተመደበው ጊዜ **13** ክ/ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-
   - በአከባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይዘረዝራሉ።
   - በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ይገልፃሉ።
   - የአከባቢያችን ህብረተሰብ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ተሣትፎን ይገልፃሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

- የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች
- የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም
- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ
- ተፈጥሮአዊ ጉዳት ዓይነቶች
- የተፈጥሮ ጥበቃ በቤትና በትምህርት ቤት

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

### **3.2.1** የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችና ጥቅማቸው።

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ተማሪዎቹ የተፈጥሮ ሀብት ምንነትና የተፈጥሮ ሀብት የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ እንዲገልፁ ጥያቄ ይጠይቁና ጊዜ ሰጥተው ለመመለስ እንዲሞክሩ ያበረታቱአቸው። ከዚያም የተማሪዎቹን ምላሽ ይቀበሉና ትክክለኛ ወይም ተቀራራቢ ምላሽ የመለሱትን አሞግሰው የተፈጥሮ ሀብት ትርጉምና ዓይነት በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ያስረዱዋቸው። በተጨማሪም እያንዳንዱን የተፈጥሮ ሀብት በመጥቀስ ምንነታቸውንና ጥቅማቸውን አብራርተው ያስረዱዋቸው። በማያያዝም እፅዋት ሰው የሚተክላቸውና በተፈጥሮ የሚገኙ ሆነው ለሁሉም እፅዋት በል እንስሳት በምግብ ምንጭነት እንደሚያገለግሉ ያብራሩላቸው።

እንሰሳትን በተመለከተለ፡- እንሰሳት የዱርና የቤት ተብለው በሁለት እንደሚመደቡና የቤት (ለማዳ) እንሰሳት ከሰው ጋር ተላምደው በቤትና በቤት አካባቢ ከሰው ጋር የሚኖሩ ሰውን በምግብ ምንጭነት፣ በጉልበት፣ ለጥበቃ፣ ወዘተ አገልግሎት እንደሚጠቅሙ በሚገባ አብራርቶ ማስረዳት ያስፈልጋል።

ውሃ ከሁለት የተለያዩ ጋሶች የተሰራ ውህድ ፈሳሽ የተፈጥሮ ሀብት እንደሆነና ለሁሉም ህይወት ላለው ነገር ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዱዋቸው። አያይዘውም ውሃ ከዝናብ፣ ከወንዝ፣ ከሐይቅ፣ ውቅያኖስ፣ መሬት ውስጥ ሊገኝ እንደሚችልና በተለይ ለሰው ልጅ፡- ለመጠጥ፣ ምግብ ለማዘጋጀት ገላን ለመታጠብና ልብስን ለማፅዳት እንደሚያገለግለው ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

አየር የተለያዩ ጋሶች ድብልቅ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት መሆኑንና ለሁሉም ህይወት ላለው ነገር ሁሉ አስፈላጊ መሆኑን እንዲያውቁት ማድረግ ይገባል።

አፈር ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚፈጠር፣ ለምን ለምን እንደሚጠቅም ተማሪዎቹ እንዲናገሩ ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያድርጉዋቸው። ከዚያም ልክ በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ እንደተገለፀው አፈር ከምን እንደተሰራ እንዴት እንደተሰራ፣ ለምን እንደሚጠቅም እንዲሁም ሦስቱን የአፈር ዓይነቶች፡- ሸክላማ፣ አሸዋማና ለም አፈር ሆናቸውን ያስረዱዋቸው።

ደን፡- መጠለያን ለመሥራት፣ ለዱር እንሰሳት መጠለያነት፣ የተለያየ የሀገር ኢኮኖሚ ምንጭ የሆኑ ነገሮችን (ሙጫ፣ ወረቀት፣ ለቤትና ቢሮ መገልገያዎች የሚሆኑ ቁሳቁሶችን፣ ወዘተ ለመሥራት የሚያገልግል የተፈጥሮ ሀብት መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ማዕድናት፡- ማዕድናትን በተመለከተ በተማሪዎች ዘንድ ሊታወቁ የሚችሉ እንደ፡- ወርቅ፣ ብር፣ መዳብ፣ ብረት፣ ወዘተ ያሉትን በምሣሌነት በመጥቀስ ማዕድናት ከፍተኛ የሀገር ኢኮኖሚ መሠረት የሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች መሆናቸውን ሥዕል 3.17 ውስጥ የተጠቀሱትን በዋቢነት በማሳየት ማስረዳት ይጠበቃል። በተጨማሪም ለጠቅላላ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ሥዕል 3.10፣ 3.11፣ 3.12፣ 3.13፣ 3.14፣ 3.15፣ 3.16፣ 3.17፣ 3.18፣ 3.19(ን) መሠረት ያደረገ ማብራሪያ መስጠት ስለ ተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ግንዛቤ አስተዋፅኦው የላቀ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

የመልመጃ **3.5** መልሶች

ሀ/

1. መ

2. ለ

3. ሐ

4. መ

5. ሀ

ለ/

1. ዝናብ፣ ወንዝ፣ ሐይቅ፣ ውቅያኖስ፣ ቢንቢ፣ ወዘተ ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ ከተጠቀሰ በቂ ነው።
2. ሸክላማ አፈር፣ አሸዋማ አፈር፣ ለም አፈር።
3. ተክሎች፣ አፈር፣ ማዕድናት፣ (ወርቅ፣ ብርመ ብረት፣ ነዳጅ፣ ወዘተ)
4. ቀይ ቀበሮ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ዋሊያ፣ ወዘተ
5. ለመጠጥ፣ ለምግብ ዝግጅት፣ ገላን መታጠብ፣ ልብስ እጥበት፣ ወዘተ)

ሐ/

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት

## 3.2.3 የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ለማነቃቂያነት የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ይጀምሩ። ጥያቄዎቹን በጥቁር ሠሌዳው ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ አስበው እንዲመልሱ ጊዜ ይሥጧቸው። መልሶቻቸውንም ያሰባስቡ። እግረ መንድዎንም ቀደም ሲል የተማሩዋቸውን የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን በዝርዝር ይጥቀሱላቸው። ከዚያም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት የተፈጥሮ ሀብትን በጥንቃቄና በእንክብካቤ ይዞ መጠቀም ማለት እንደሆነ ያስረዱዋቸው። አያይዘውም እነዚህን ሀብቶች ትኩረት ከነፈግናቸው ለአደጋ እንደሚጋለጡና መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎት እንደሚያቆሙ ያስረዱዋቸው። ይህንንም ሲያደርጉ የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት ዓይነቶችን ማለትም፡-

- የአየር ብክለት፣
- የውሃ ብክለት፣
- የደን መጨርጨፍ
- የአፈር መሸርሸርን በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ይህን ካደረጉ በኋላ እያንዳንዱን የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት መንስኤና መፍትሔ (መከላከያ

መንገዱን) ልክ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተገለፀው መሠረት አብራርተው ያስረዱዋቸው።

### **3.2.3.1** የተፈጥሮ ጥበቃ በቤትና በትምህርት ቤት

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ እያንዳንዱ ቤተሰብ አከባቢውን (ደጅአፉን) ካፀዳ አከባቢው የፀዳ (ፅዱ) እንደሚሆን ማወቅ እንደሚገባቸው በማብራራት ይጀምሩና እያንዳንዱ ሰው በቤቱና በአከባቢው የተፈጥሮ ጥበቃ ሥራ ከሰራ የተፈጥሮ አከባቢው ደህንነት የተጠበቀ እንደሚሆን ያስረዱዋቸው። እያይዘውም የተፈጥሮ ጥበቃ፡-

ሀ. በቤት ሊሰራ የሚችለው ጥንቃቄ የተሞላበት የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓትን በመከተል፣ ተክሎችን ተክሎ ተንከባክቦ በማሣደግና በጎርፍ መሄጃ ቦይ ውስጥ እርከን በመሥራት፣

ለ. በትምህርት ቤት ደግሞ፡- ቆሻሻ የትም አለመጣልና የተጣለውን ቆሻሻ ሰብስቦ በጥንቃቄ በማስወገድ፣ በባዶ ቦታዎች ይህንንም በቤታቸውና በትምህርት ቤታቸው ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በአፅንኦት ያስረዱዋቸው።

### **4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

| | |
|---|---|
| ፖስተሮች ለምሣሌ፡- | - የመሬት መራቆትን የሚያሳይ በደን ቃጠሎ ምክንያት የሚበተኑ የዱር እንሰሳትን የሚያሳይ |
| ሥዕሎች<br>የተማሪው መጽሐፍ | - ሰዎች አከባቢያቸውን ሲንከባከቡ እጽዋቶችን ሲተክሉ እርከን ሲሰሩ የሚሳይ |

### **5.** የመከታተያማ መገምገሚያ ዘዴዎች፡-

- የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን እንዲጠቅሱ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- የተፈጥሮ ሀብት ጥቅምን እንዲዘረዘሩ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴን እንዲገልፁ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴን እንዲገልጹ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- የተፈጥሮ ጉዳት ዓይነቶችንና መንስኤያቸውን እንዲገልጹ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።

- የተፈጥሮ ጥበቃን በቤትና በትምህርት ቤት እንዴት መተግበር እንደሚቻል እንዲገልፁ ጥጣቄ በመጠየቅ መገምገም።

የመልመጃ **3/6** መልሶች

ሀ/

1. ሀ. የደን መጨፍጨፍ

   ለ. የውሃ ብክለት

   ሐ. የአፈር መሸርሸር

   መ. የአየር ብክለት

   ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱ ከተጠቀሰ በቂ ነው።

2. የሰደድ እሣትን መጠበቅና መከላከል

   ደን እንዳይቆረጥ ጥበቃ ማድረግ። ከተቆረጠም በምትኩ ሌላ መትከል።

   ማስታወሻ፡- አንዳንድ ንቁ ተማሪዎች የሰደድ እሣት ምንድነው እንዴትስ ይነሳል ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ ካጋጠመ፡- የሰደድ እሣት ማለት ሰፊ በሆነ የደን ሀብት ላይ የሚዳሰስ ቃጠሎ እንደ ሆነና መንስኤውም፡-

   ሀ. ሁለት የተጠጋጉ ዛፎች (ቅርንጫፎች) ነፋስ ሲያነቃንቃቸው በሚፈጥሩት ፊትግያ በሚፈጠር እሳት፣

   ለ. ግዴለሽ ግለሰቦች በሚያቀጣጥሉት እሳት፣

   ሐ. እንዲሁም ግዴለሽ ሰዎች (መንገደኞች) አጭሰው በሚወረውሩት የሲጋራ ቁራጭ እሳት አማካኝነት ሊፈጠር እንደሚችል ማስረዳት ያስፈልጋል።

3. ሀ. እፅዋቶችን መተክል

   ለ. እርከን መሥራት

4. እፅዋቶች አፈርን በስሮቻቸው አቅፈው ስለሚይዙ አፈር በቀላሉ አይካላም (አይነሳም)

5. ሀ. እፅዋቶችን በመትከል የአፈርን መሸርሸር መከላከል።

   ለ. ቆሻሻን የትም አለመጣልና የተጣለውን አንስቶ በአግባቡ ማስወገድ፡

   ሐ. አከባቢን ማስዋብ

ለ/

1. መ
2. ሀ
3. ሐ
4. ለ

**3.3** በአከባቢያችን የሚገኙ እፅዋቶች

የተመደበው ጊዜ 15 ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የእፅዋትን ክፍል ስም ይናገራሉ፣ ያሳያሉ፡
- የእፅዋትን ክፍሎች ተግባር ይናገራሉ።
- እፅዋትን በመሰብሰብ ክፍሎቻቸውን ማስቀመጥ ይችላሉ።
- እፅዋት ለማደግ ምን ምን እንደሚያስፈልጋቸው ይናገራሉ።
- እፅዋትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማመልከት ወይም መናገር ይችላሉ።

2. ዝርዝር ይዘቶች

- የእፅዋትን ክፍልና ተግባራቸው (ግንድ፣ ቅጠል፣ አበባና ሥር)
- የተለያዩ የእፅዋትን ክፍሎችን ማሰባሰብና ማስቀመጥ።
- እፅዋትን ማሳደግ፣
- እፅዋት ለማደግ ምን ያስፈልጋቸዋል።
- እፅዋትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ሁኔታዎች።

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

**3.3.1** የእፅዋት ክፍልና ተግባራቸው

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ በቅድሚያ የትምህርቱን ርዕስ ጎላ አድርገው በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ከዚያም የአንድ ተክል ሙሉ ክፍሉን (ሥር፣ ግንድ፣ ቅጠል፣ አበባና ፍሬ) የሚያሳይ ሥዕል በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይሳሉላቸው። ይህንን ካደረጉ በኋላ ከመጽሐፋቸው ውስጥ ሥዕል 3.25 እንዲመለከቱ ያድርጉ በመቀጠልም ተማሪዎቹ የተክሎችን ክፍሎች አንድ በአንድ እንዲጠሩ ያድርጉ። ይህንን ሲያደርጉ ተማሪዎቹ በቀላሉ የተክሎቹን ክፍሎች እንዲያውቁ እንዳደረጉ መረዳት አስፈላጊ ነው። ከዚያም ከታችኛው የተክል ክፍል (ሥር) በመጀመር የሥር ዓይነትና ተግባር በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ በተለጸው መሠረት ያስረዱዋቸው። በሥር ዓይነት መለያ ላይ እንዲሰራ የቀረበውን ተግባራዊ ክንዋኔም፡- በማስተማር ሂደት ላይ እያሉ ወይም በቅድሚያ የተመረጡ ሁለት ወይም ሶስት ተማሪዎችን ከትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የተለያዩ ትናንሽ ተክሎችን (አረም) ከለስላሳ ቦታ በጥንቃቄ ስሮቻቸው ሣይበጣጠሱ ነቅለው እንዲያመጡ በማድረግ ሁለቱን የሥር ዓይነቶች እንዲያውቁ ማድረግ ትምህርቱን ህያው እንደሚያደርግ መረዳት ተገቢ ነው።

ከመሬት በላይ ያለውን የተክል ክፍልን ተግባርን በተመለከተ ደግሞ፡- ከግንድ በመጀመር በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ሥዕል 3.27 እንዲመለከቱ አድርገው ያስረዱዋቸው። የተክል ግንድን የተመለከተ ተግባራዊ ክንዋኔን የሥር ዓይነትና ተግባር ለማስረዳት የጠቀሙበትን ዘዴ እዚህም ይጠቀሙበትና ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ በቡድን እንዲሰሩ ይዘዟቸው። ሠንጠረዥ 3.5(ትን) ሁሉም ተማሪዎች በትክክል እንዲሰሩ ያበረታቱዋቸው። የግንድን ተግባር ከመማሪያ መፅሐፋቸው እንዲያነቡና ያልገባቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁ ይንገሯቸው።

አያይዘውም የተክል ቅጠል ዋና የተክሉ ምግብ ማምረቻ ፋብሪካ መሆኑን ያስረዱዋቸው። ቅጠሎች በብዙ መንገድ የሚለያዩ መሆኑን ተማሪዎቹ በደንብ እንዲረዱ ሥዕል 3.28 መሠረት ያደረገ ተግባራዊ ክንዋኔን በሠንጠረዥ 3.6 ውስጥ እንዲተገብሩ ያደርጉዋቸው። በተለይ በሥዕል 3.28 ውስጥ የተጠቀሱትን ቅጠሎች ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት በቅድሚያ አሰባስበው ለማስተማሪያ መርጃነት ቢጠቀሙበት ትምህርቱን ለማስረፅ እንደሚረዳ መረዳት አስፈላጊ ነው።

የተክል አበባ የዘር ፍሬ ማፍሪያ ክፍል ነው። ይህንን የተክል ክፍል ሲያስተምሩ በተማሪዎች ሊታወቅ ይችላል ብለው የሚገምቱትን አበባ ወደ ክፍል ይዘው ይግቡ። ምን እንደሆነ ይጠይቋቸው። የሚያውቋቸውን የአበባ ዓይነትና ቀለም እንዲናገሩ

ያድርጓቸው። አበባ ለተክልና ለሰው ልጅ ያለውን ጠቀሜታ እንዲገልፁ ያድርጉዋቸው። ይህንንም ሲያደርጉ የተለያየ ምላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። ነገር ግን በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ በተገለፀው መሠረት አበባ ለተክሉም ሆነ ለሰው ልጅ አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዱዋቸው።

የመልመጃ **3.7** መልሶች

ሀ/

1. ሐ
2. ሐ
3. ሐ

ለ/

1. ተራዘምና ድራድር
2. እንጨት ያለውና ሣር ያለው ግንድ
3. ለተክሉ ፍሬና ዘር ማፍራት
   - ለንቦች ምግብ የሚሆን ወለላ ማዘጋጀት
   - ለንቦች ምግብ የሚሆን ወለላ ማዘጋጀት
   - ለቤትና አካባቢ ውበት (ድመቀት) መስጠት
   - ከሶስቱ ሁለቱን ከመለሱ በቂ ነው።
4. የተዘጋጀ ምግብ ለታችኛው የተክል ክፍል ማቀበል።
   - ውሃና የሚሙ ማዕድናትን ከታች ወደ ላይ ማስተላለፍ።
   - ከመሬት በላይ ያለውን የተክሉን አካል መሸከም።

ሐ/

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. ሐሰት - የራሳቸውን ምግብ ማዘጋጀት የሚችሉት አረንጓዴ እጽዋት ብቻ ናቸው።
   - የራሳቸውን ምግብ ማዘጋጀት የማይችሉ ተክሎች እንዳሉ ለምሣሌ ፈንገስን ማስረዳት አስፈላጊ ነው።
4. እውነት
5. እውነት

### 3.3.2 የእፅዋት ክፍሎችን ማሰባሰብና ማስቀመጥ

ይህን ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ አንድ ሣምንት በፊት የተለያዩ የዕፅዋት ክፍሎችን በማኀበር አዘጋጅተው ይዘው ወደ ክፍል ይግቡና እያሣ ማስተማር ይጀምሩ። ይህን ማድረግዎ ተማሪዎቹ ትምህርቱን መቀበል ብቻ ሣይሆን ራሳቸውም ተግባራዊ ክንውኑን ለመሥራት ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በቀረበው ተግባራዊ ኩብዋኔ መሠረት በቅድሚያ ራስዎ ሰርተው ያሳዩዋቸው፤ አስፈላጊነቱንም በመፀሐፋቸው ውስጥ በተገለፀው መሠረት ያስረዱዋቸው። ከዚያም ተግባራዊ ክንዋኔውን በቡድን (ከሶስት እስከ አምስት) ሆነው እንዲሰሩ ያድርጉዋቸው። ለአሰራሩም ሥዕል 3.30 እንዲከተሉ ይምከሩዋቸው።

### 3.3.3 እጽዋትን ማሣደግ

ይህንን ትምህርት ለማነቃቂያነት የቀረበውን ጥያቄ (ተክሎች ለማደግ ምን ምን ያስፈልጋቸዋል□) የሚለውን ይጠይቋቸውና ምላሻቸውን ይቀበሉ (አሰባስበው ይመዝግቡ)። ከዚያም ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሊሰጥ በሚችል ዓይነት የተዘጋጀውን የተግባር ክንዋኔ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በተመረጠ ቦታ እንዲሰሩ ያድርጉና ከአንድ ሣምንት በኋላ ተክሎቹን ወደ ክፍል በማምጣት ጠረጴዛ ላይ ለሁሉም ተማሪ ሊታይ በሚችል ቦታ እንዲቀመጥ ያድርጉ። ከዚያም ተማሪዎች በተክሎቹ ላይ ያለውን ለውጥ ከመነሻው ጋር በማነፃፀር እንዲናገሩ ያድርጉ። በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ የተጠየቁ አራቱንም ጥያቄዎች ተክሎቹን እያዩ እንዲመልሱ ይደረግ። ይህንንም ሲያደርጉ ለተክል እድገት አስፈላጊ የሆኑት ውሃ፣ አፈር፣ የፀሐይ ብርሃንና አየር መሆናቸውን በማረጋገጥ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸውና ትምህርቱን ያጠናቁ።

### 3.3.4 እፅዋት ለማደግ ምን ያስፈልጋቸዋል□

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ከሰሩት ተግባራዊ ክንዋኔ ያገኙትን እውቀት መጠቀም እንዲችሉ ያድርጉ። ይህንንም የሚያደርጉት ርዕሱን "እፅዋት ለማደግ ምን ያስፈልጋቸዋል□" የሚለውን ጥያቄ መልክ በማቅረብ ይሆናል። ከዚያም ምላሻቸውን ይቀበሉና ተክሎች ለማደግ ውሃ፣ አየር፣ የፀሐይ ብርሃን እንደሚያስፈልጋቸው ይግለፁላቸው። አረንጓዴ ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት ካርቦንዳይኦክሳይድ የተባለ ጋስና ውሃን እንደሚጠቀሙና የፀሐይ ብርሃን ደግሞ ሁለቱን ለማቀነባበር እንደሚስፈልጋቸው ያስረዱዋቸው።

### 3.3.5 እፅዋትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮች

ይህንን ትምህርት አንድ ገበሬ ጥሩ ምርት ለማምረት ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲናገሩ በመጠየቅ ይጀምሩና ምላሻቸውን ይቀበሉ። ከዚያም በተመሣሣይ መልኩ ተክሎችን (የጓሮ አትክልትን) ለማልማት አፈሩ በሚገባ መቆፈርና መለስለስ እንደሚገባው ያስረዱዋቸው። ይህንንም ለማድረግ የተለያዩ ቀላል የእጅ መሣሪያዎች እንደሚያስፈልጉ ያስረዱዋቸው። እነዚህ የእጅ መሣሪያዎችም፡- ዶማ፣ መኮትኮቻ (ሥዕል 3.31 ሀናለ)፣ ማለስለሺያና መስመር ማውጫ፣ ውሃ መጠጫ፣ ወዘተ መሆናቸውን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ያስረዱዋቸው። በመጨረሻም ለተክል እድገት ሊደረግለት ከሚገባው እንክብካቤ ውስጥ፡-

- ውሃን ጥዋትን ማታ ማጠጣት
- መኮትኮትና ማረም
- ከበሽታ መጠበቅ ተጠቃሽ መሆናቸውን ገልፀው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

### 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-

- ሥዕሎች
- የተለያዩ ተክሎች
- የተክል ክፍሎች

### 5. የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

- የእፅዋትን ክፍልና ተግባራቸውን እንዲናገሩ በመጠየቅ መገምገም።
- እፅዋት ለማድግ ምን እንደሚያስፈልጋቸው እንዲናገሩ በመጠየቅ መገምገም።
- እፅዋት ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ሁኔታዎች እንዲናገሩ በመጠየቅ መገምገም።

የመልመጃ **3.8** መልሶች

ሀ/

1. የተክልን ሥር አቅፎ መያዝ፣
   - ለተክሉ አስፈላጊ የሆኑ ማዕድናትንና ውሃን ማቅረብ፣
2. ኦክስጂን የተባለ ጋስ፣
3. ካርቦንዳይ ኦክሳይድ፣
4. ውሃ፣ አየር፣ የፀሐይ ብርሃን፣

5. ተክሉ የሚተከልበትን ቦታ በሚገባ አለስልሶ ማዘጋጀት፣

6. መቆፈሪያ (ዶማ፣ ጀማባ፣ ወዘተ)

7. ጥዋት ወይም ማታ (ምክንያቱም በፀሐይ ካጠጣን ውሃው ስለሚተን ተክሉ የሚያስፈልገውን ያህል ውሃ ሊያገኝ አይችልም።

8. - ውሃ ማጠጣት

   - መኮትኮትና ማረም
   - ከበሽታ መጠበቅ

## 3.4 በአከባቢያችን የሚገኙ እንሰሳት

የተመደበው ጊዜ 13 ክ/ጊዜ

1. ዝርዝር ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-
   - እንሰሳትን በመዋለጃቸው፣ በእንቅስቃሴቸው፣ በአመጋገባቸው ሁኔታ፣ በአኗኗራቸውና የሰውነት ሽፋማቸው ይመደባሉ።
   - ከእንሰሳት የሚገኙ የተለያዩ ተዋፅኦዎችን መለየት ይችላሉ።
   - ለእንሰሳት እርባታ የሚያስፈልግ መሣሪያዎችን ለይተው ይናገራሉ።
   - እንሰሳትን ለመንከባከብ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ያሣያሉ ይገልፃሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች
   - እንሰሳትን መመደብ
   - የእንሰሳት ተዋጽኦ
   - ለእንሰሳት እርባታ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች (መሣሪያዎች)
   - በህይወት ላሉ እንሰሳት አክብሮት መስጠት።

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

### 3.4.1 እንሰሳትን መመደብ

ይህንን ትምህርት ተማሪዎቹ በአከባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንዴት ሲመደቡ እንደነበር በመጠየቅ ይጀምሩ። ከዚያም መልሳቸውን መቀበልና ቀደም ሲል የተማሩትን የመመደብ እውቀት እንደገና እንዲያስታውሱ በማድረግ በአከባቢችን የሚገኙ ነገሮች፡- ህይወት ያላቸውና የሌላቸው ተብለው በሁለት እንደሚመደቡ፣ ህይወት ያላቸው ነገሮች ደግሞ

እንሰሳትና እፅዋት ተብለው በሁለት የሚመደቡ መሆናቸውን አብራርተው ማስረዳት ይጠበቃል።

ከዚያም ቀደም ሲል ስለ እፅዋት ባህሪይ (ተፈጥሮ) የተማሩ መሆኑንና በእንሰሳትና እፅዋት መካከል ያለውን ልዩነት የተወሰኑትን ለምሣሌ፡- እጽዋት ምግባቸውን ማዘጋጀት የሚችሉ ሲሆን እንሰሳት የማይችሉ መሆኑን፣ እንሰሳት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በአካል መንቀሳቀስ የሚችሉና እፅዋት ግን የማይችሉ መሆኑን ማስረዳት በመቀጠልም ከዚህ በኋላ ስለ እንሰሳት ባህሪይና አመዳደብ የሚማሩ መሆኑን በማስረዳት ስለ እንሰሳት ምን ምን እንደሚያውቁ በመጠየቅ ጠቅላላ አስተሳሰባቸውን ወደ እንስሳት ዓለም ውስጥ ለማምጣት መሞከር። ከዚያም የተለያዩ እንሰሳትን (የሚያውቁዋቸውን) እንዲጠሩ ማድረግ። ለምሣሌ፡- ላም፣ ፍየል፣ ውሻ፣ ዶሮ፣ ወፎች (የተለያዩ)፣ በራሪ ነፍሳትን፡- ቢራቢሮ፣ የእሳት እራት፣ ዝንብ፣ የሌሊት ወፍ፣ አንበሳ፣ ጅብ፣ አይጥ፣ ድመት፣ ወዘተ ስማቸውን ሲጠቅሱ በጥቁር ሠሌዳው ላይ በመፃፍ (በመደርደር) እንዲመለከቱዋቸው ማድረግ። ከዚያም እነዚህ እንሰሳት ያላቸውን ልዩነት እንዲናገሩ ያድርጉዋቸው። መልሣቸውንም በመሰብሰብ ምላሻቸውን ምን ያህል ከትምህርቱ ጋር (ወደፊት) እንዲማሩ ከሚፈለገው ጋር እንደሚጣጣም (እንደሚቀራረብ) ማመዛዘን የተማሪዎቹንጥረት ማድነቅ።

ከዚያም በአጠቃላይ እንሰሳት በአረባባቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገብ ባህሪያቸው፣ በአኗኗራቸውና በሰውነት ሽፋናቸው ልዩነት መሠረት የሚመደቡ መሆኑን በማስገንዘብ የተማሪዎቹን ትኩረት ወደ ሚፈለገው የእንስሳት ልዩነትና አመዳደብ እንዲያነጣጥሩ ማድረግና ወደ እያንዳንዱ ልዩነት መግባት አስፈላጊ ነው።

ሀ. የእንሰሳት አመዳደብ

ትምህርቱን ሲጀምሩ እንሰሳት በአረባብ ተፈጥሮአቸው በሁለት የሚመደቡ መሆናቸውን ይግለፁላቸው። ከዚያም እነዚህን ሁለቱን ምድቦች ተማሪዎቹ እንዲጠቅሱ እድሉን ይስጧቸውና መልሳቸውን ይቀበሉዋቸው። እያይዘውም ሁለቱንም ምድቦች በጥቁር ሠሌዳው ላይ፡-

- እንቁላል የሚጥሉና
- ህይወት ያለውን መሰላቸውን የሚወልዱ በማለት ለይተው ይፃፉላቸው።

እንቁላል የሚጥሉ፡-

እንቁላላቸውን በመጣል ስለሚራቡ እንሰሳት ሲያስተምሩ በመጀመሪያ ለማነቃቂያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጊዜ ሰጥተው እንዲመልሱ ያድጉዋቸው። ከዚያም

ምላሻቸውን ይቀበሉና ሥዕል 3.35(ትን) በሚገባ እንዲመለከቱ በማድረግ በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ በተገለጸው መሠረት ያስረድዋቸው።

**ልጅ (መሠላቸውን) የሚወልዱ፡-**

ይህንን ትምህርት ሲያስተምሩ አብዛኛውን ጊዜ ዕድሉን (መናገሩን) ለተማሪዎች ይሰጡና እርስም ለመነሻነት የሚያገልግሉ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ለምሣሌ፡-

- መሠላቸውን የሚወልዱ የትኞቹ ናቸው?
- የተወለዱትን ሰዎች ምን ብለው ይጠሩዋቸዋል?
- ምን መግበው ያሳድጉዋቸዋል?
- ምን ዓይነት ጥንቃቄስ ደርጉላቸዋል?
- በውሃ ውስጥ የሚኖር አጥቢ የቱ ነው?
- በራሪ አጥቢስ ታውቃላችሁ? ወዘተ

ከዚያም መላሻቸውን በጥቁር ሠሌዳው ላይ በመፃፍ ሁሉም መሰላቸውን ስለሚወልዱ እንሰሳት ግንዛቤ እንዲያገኙ ያድርጉ። በመጨራሻም ሥዕል 3.35(ትን) በደንብ እንዲመለከቱ በማሳሰብ ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

እንሰሳትን በእንቅሥቃሴያቸው መመደብ

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ርዕሱን ጎላ አድርገው በጠቅር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ከዚያም ከቦታ ቦታመንቀሳቀስ እንሰሳትን ከእጽዋት የሚለይ አንዱ ባህሪይ መሆኑን ያስረዱዋቸው። ይሁን እንጂ ይህ የእንሰሳት እንቅስቃሴ እንደመነቀሳቀሻው የሰውነት ክፍልና ቁጥር የሚለይ መሆኑን ያስረዱዋቸውና የተለያዩ እንሰሳት ከሰው ጭምር እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ይጠይቋቸው። ለምሣሌ፡-

- በአራት እግራቸው የሚንቀሳቀሱ፣
- በሁለት እግራቸው የሚንቀሳቀሱ፣
- በመዋኘት የሚንቀሳቀሱ፣
- በክንፋቸው የሚበሩ፣
- በመሣብና በመራመድ የሚንቀሳቀሱ፣ ወዘተ

የትኞችም እንደሆኑ ለይተው እንዲገልፁ ያድርጓቸው። ምላሻቸውንም ይቀበሉና በአተቃላይ እንሰሳት በመንቀሳቀሻ አካላቸው እንደሚለያዩና ለዚህም በመፅሐፋቸው ውስጥ ሥዕል 3.36 እስከ 3.38 ያለውን እንደዲመለከቱ በማሳሰብ ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

እንሰሳትን በአመጋገብ ባህሪያቸው መመደብ

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ርዕሱን አስቀድመው በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ከዚያም እንሰሳት በአመጋገብ ባህሪያቸው በሶስት ምድብ እንደሚመደቡና እነሱም፡-

- እፅዋት በል
- ሥጋ በል
- እፅዋትና ሥጋ በል መሆናቸውን በጥቁር ሠሌዳው ፅፈው

ያስረዱዋቸው። ከዚያም እድሉን ለተማሪዎቹ በመስጠት፡-

- እፅዋት በል የትኞቹ እንደሆኑ፣
- ሥጋ በል የትኞቹ እንደሆኑ፣
- እፅዋትና ሥጋ በል የሆኑ የትኞቹ እንደሆኑ በአከባቢያቸው

ከሚያውቁዋቸው እንሰሳት ውስጥ እንዲጠቅሱ ያድርጉዋቸው። አያይዘውም ሥዕል 3.39፣ 3፣40፣ 3.41(ትን) እንዲመለከቱና የሶስቱንም ምድብ ምሣሌ በማስታወሻቸው እንዲወስዱ አድርገው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

እንሰሳትን በአኗኗራቸው መመደብ

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ተማሪዎቹ በአከባቢያቸው የሚገኙ እንሰሳት የት የት እንደሚኖሩ እንዲናገሩ በመጠየቅ ይጀምሩ። ጊዜ ይስጧቸውና እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው መልሶቻቸውንም ያሰባስቡ። ተሳትፎአቸውንም ያድንቁ። ከዚያም በአጠቃላይ እንስሳት በመኖሪያ አከባቢያቸው እንደሚለያዩ ምሣሌ ጠቅሰው ያስረዱዋቸው። በሚሰጡት ምሣሌ ውስጥም፡-

- ውሃ ውስጥ የሚኖሩ
- በመሬት ላይ የሚኖሩ
- በመሬትና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ
- በቤት(ከሰው) ጋርና በጫካ የሚኖሩ ቢያንስ ሁለት 3.42፣ 3.43፣ 3.44፣ (ትን)እንዲመለከቱ መክረው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

እንሰሳትን በቆዳ ሽፋናቸው መመደብ

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ርዕሱን ከፃፉላቸው በኋላ ተማሪዎቹ በአከባቢያቸው የሚኖሩ እንሰሳት ቆዳቸው በምን እንደተሸፈነ እንዲናገሩ ያድርጉ። ለምሣሌ፡- ዶሮ (ወፎች)፣ በግ፣ ፍየል፣ ውሻ፣ ድመት፣ አንበሳ፣ እንሽላሊት፣ አሣ፣ እባብ፣ አዞ፣ ወዘተ ከዚያም ጊዜ ሰጥተው እንዲመልሱ ያበረታቱአቸው። ሙከራቸውንም ያድንቁላቸው። አያይዘውም እንስሳት በቆዳ ሽፋናቸው ልዩነት በሶስት እንደሚመደቡና እነሱም፡-

- በፀጉር የተሸፈነ
- በላባ የተሸፈነ
- በቅርፊት የተሸፈኑ መሆናቸውን ያስረዱቸው። በመጨረሻም ሥዕል 3.45፣ 3.46 እና 3.47(ትን) እንዲመለከቱና ለእያንዳንዱ ሁለት፣ ሁለት ምሣሌ በደብተራቸው ጽፈው እንዲወስዱ በማድረግ ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

3.4.2 የእንስሳት ተዋፅኦ

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ርዕሱን በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ከዚያም የእንሰሳት ተዋፅኦ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲናገሩ ይጠይቁዋቸው። ከዚያም የእንሰሳት ተዋፅኦ ማለት ሰው ከእንሰሳት የሚያገኛቸው የተለያዩ ጥቅሞችን ማለት እንደሆነ ያስረዱዋቸው። አያይዘውም ሰው ከእንሰሳት የሚያገኛቸው የተለያዩ ጥቅሞች ለምሣሌ፡-

- ከወተት፡- ቅቤ፣ አይብና እርጎ
- ከቆዳ፡- ጫማ፣ ጃኬት፣ ኮት፣ ቀበቶ፣ ወዘተ
- ከቀንዳቸው፡- የተለያየ የቤት ጌጣጌጦችን፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን (ጭልፋ፣ ማንኪያ፣ መጠጪያና የልብስ ቁልፍ)
- ከፀጉራቸው፡- ብርድ ልብስ፣ ሹራብ፣ መሥራት የሚጠቀሱ መሆናቸውን አስረድተው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

**3.4.3** ለእንሰሳት እርባታ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች

ይህንን ትምህርት ሲጀምሩ ለእንሰሳት እርባታ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችና ሁኔታዎች ለምሣሌ፡-

- ለማጠብ የሚያስችል ብሩሽ
- የምግብ ማስቀመጫ (መያዣ)
- ሣርና የተደባለቀ ምግብ መሆናቸውን በዝርዝር በመግለፅ ይጀምሩ።

ከዚያም የእያንዳንዱን መሣሪያ ጥቅም ያብራሩላቸው። በመጨረሻም በህይወት ላሉ እንሰሳት አክብሮት መስጠትና አለመተናኮል አስፈላጊ እንደሆነ አስረድተው ትምህርቱን ያጠናቁላቸው።

**4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- ሥዕሎች
- ተዛማጅነት ያላቸውና ገላጭ የሆኑ ሌሎች ነገሮችንም መጠቀም አስፈላጊ ነው።

**5.** የመከታተያና መገምገሚያ ዘዴዎች

- እንስሳትን በመዋለጃቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በአኗኗራቸውና በቆዳ ሽፋናቸው ለይቶ መመደብ መቻላቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- የእንስሳትን ተዋፅኦ እንዲዘረዝሩ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።
- ለእንስሳት እርባታ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን እንዲጠቅሱ ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም።

የመልመጃ **3/9** መልሶች

ሀ/

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት

ለ/

1. አሣ በውሃ ውስጥ የሚተነፍሰው የሚሟሟ ኦክስጂንን ነው። ወደ መሬት ሲወጣ የመተንፈሻ አካሉ (ስንጥቡ) ስለሚደርቅና በመሬት ላይ ያለው አየር ጋስ በመሆኑ መተንፈስ አይችልም። በመሆኑም ታፍኖ ይሞታል።
2. አዎ፦ አንደኛ ለእርባታ፣ ሁለተኛ የአከባቢውን አየር ፀባይ ለመቋቋም፣ ሦስተኛ ከጠላት ለመሠወር።
3. አለው (ለማብራሪያው ለጥያቄ ሁለት የተሰጠውን መልስ ይመልከቱ)
4. አየሩ የሚሟ፣ የሚያገኙት ከአከባቢው ውሃ አካል።
5. እንቁራሪቶች ወደ ውሃ ሲገቡ የሚተነፍሱት በቆዳቸው ነው። ቆዳቸው ትናንሽ ቀዳዳዎች ስላሉት የሚሟሟ ኦክስጂን በዚያ ቀዳዳ በኩል ወደ ደም ስሮቻቸው ይተናሉ።

ክፍለ ትምህርት - አራት

## 4. ወረዳችን /ክፍለ ከተማችን

የተመደበው ጊዜ 49 ክ/ጊዜ

መግቢያ

ይህ ክፍለ ትምህርት አራት ዋና ዋና ርዕሶችና በርካታ ንዕስ ርዕሶችን ያካተተ ነው። ክፍለ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ ተማሪዎች ስለ ወረዳቸው ግንዛቤ እንዲይዙ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። በውስጡም ስለ ወረዳቸው አቅጣጫ፣ የወረዳቸው መሬት አቀማመጥ፣ በወረዳቸው የሚገኙ መስሪያ ቤቶችና የወረዳ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚሉ አራት ዋና ዋና ርዕሶች አሉት። ለተማሪዎች ስለ ወረዳቸው አቅጣጫ ስናስተምራቸው የምናነሳቸው አራቱ አብይት አቅጣጫዎች፣ የወረዳቸው አቀማመጥ ከሌሎቹ አዋሳኝ ወረዳዎች ጋር ሲታይና የወረዳቸውን ጠቃሚ ቦታዎች በሚል በተዘጋጀው ንዑስ ርዕሶች ጋር በማዛመድ ይሆናል። ቀጥሎም የወረዳቸውን መሬት አቀማመጥና ገጽታ ግንዛቤ እንዲይዙና እንዲያውቁ በማድረግ በወረዳቸው የሚገኙ መስሪያ ቤቶችን ተግባራቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይጠበቅብናል። በመጨረሻም የወረዳቸውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ስለዚህ መምህራን ክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን በመከታተል የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ማድረስና ተማሪዎቹ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባችኋል።

### አጠቃላይ ዓላማ

ተማሪዎቹ ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

1. ወረዳቸውንና ተፈላጊ የሆኑ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ቦታዎችን ያመለክታሉ።
2. የመሬት አቀማመጥና ያላቸውን ሁኔታ ይለያሉ።
3. በወረዳቸው የሚገኙ መስሪያ ቤቶችንና የሥራ ተግባራቸውን ይገልፃሉ።
4. በወረዳቸው የሚከናወኑ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ይለያሉ። በአከባቢያቸው ስለሚከናወኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ምሣሌ ይሰጣሉ።
5. ለወረዳቸው እድገት ሥራ ያለውን አስተዋፅኦ ይገልፃሉ። እነሱም በእድሜያቸው ተመጣጣኝ የሆነ ስራ ለመሥራት ቃል ይገባሉ።
6. እስከ ትምህርቱ ማብቂያ ድረስ ሳይንሳዊ ክህሎትን ያዳብራሉ። አከባቢን መመልከት፣ መመዝገብ፣ መመደብ፣ መጠየቅ፣ መለካት፣ ግንኙነት ምስል መስራትና አብሮ መስራት ናቸው።

## 4.1 የወረዳችን አቅጣጫ

የተመደበው ጊዜ 13 ክ/ጊዜ

### 1. ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- አራቱን አቅጣጫዎች ያመለክታሉ።
- ታሪካዊ ቦታዎችን መለየት ይችላሉ።

### 2. ዝርዝር ይዘቶች

4.1 የወረዳችን አቅጣጫ

4.1.1 አራቱ አቅጣጫዎች /ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ/

4.1.2 የወረዳችን አቀማመጥ ከሌሎች አዋሳኝ ወረዳዎች ጋር ሲታይ

4.1.3 በወረዳችን ጠቃሚ ቦታዎች /ታሪካዊ ቦታዎች/

- ታሪካዊ ቦታዎችን ታሪክ ማወቅ

### 3. የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በመጀመሪያ ክፍለ ትምህርቱንና ዋናውን ርዕስ ያስተዋውቁና በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የሚያገኟቸውን መታወስ የሚገባቸው /ቁልፍ ነጥቦችን/ ቃላትና አላማን በማንበብ እንዲያውቋቸው ያድርጉላቸው።
- ከዚያም በክፍለ ትምህርቱ መግቢያ ላይ የተቀመጠውን ለማነቃቂያ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲነጋገሩና ለመመለስ እንዲሞክሩ ጊዜ ይስጧቸው። ጥያቄዎቹን በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመፃፍ ወይም በማንበብ ሊሆን ይችላል።
- በመቀጠል ወረዳ /ክፍለ ከተማ/ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በደንብ እንዲረዱ ለማድረግ ማስረዳት ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው።
- ትምህርት ቤታቸው የሚገኝበት ወረዳ ምን እንደሚባል በመጠየቅና እንዲመልሱ በማድረግ ወደ ሚቀጥለው ዋና ርዕስ መሸጋገር ያስፈልጋል።
- በርዕሱ የተቀመጡትን ቁልፍ ቃላት እንዲያውቋቸው በማድረግ በስሩ የተቀመጡትን የማነቃቂያ ጥያቄዎች ለተማሪች በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመፃፍ ማቅረብ አስፈላጊ ነው። በመቀጠልም ተማሪዎቹ የመለሱትን መልስ በማዳመጥ ዝርዝር ሀሳቡን ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

- ተማሪዎች ተራ በተራ በመነሳት አቅጣጫቸውን ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ በማለት እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል።
- በመቀጠል በንዑስ ርዕስ 4.1.2 ላይ የተቀመጠውን የማነቃቂያ ጥያቄዎች በማቅረብ ተማሪዎቹ እንዲወያዩ ማድረግ። ጥያቄውን በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ወይም በቃል በማንበብ ሊሆን ይችላል። መልሳቸውን ተራ በተራ በመቀበል ማበረታታት ያስፈልጋል።
- በአቅራቢያቸው ካለው ወረዳ ጋር ሲነፃፀር የወረዳቸውን መገኛ እንዴት መግለጽ እንደሚችሉ በተማሪዎቹ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እንደቀረበው ማስረዳት ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች በመቀመጫቸው ላይ ተቀምጠው እንዳሉ ከግራቸው፣ ከቀኛቸው፣ ከኃላቸውና ከፊታቸው እነ ማን እንደተቀመጡ ስም እየጠሩ እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው አጎራባች የሆኑ የተለያዩ አካባቢዎችን እንዲያውቁ ማድረግ። ይህንን እንደ ጨዋታ በማድረግ መምህር በትምህርት ቤታቸው አካባቢ የሚገኝ አንድ መስሪያ ቤትን በሚጠሩበት ጊዜ ተማሪዎች የመስሪያ ቤቱን መገኛ አቅጣጫ በመናገር እየተጫወቱ አቅጣጫዎችን እንዲያውቁ ማድረግ።
- ተማሪዎች በወረዳው የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን ስም መዘርዘርና ያላቸውን ታሪካዊ ጠቀሜታ እንዲገልፁ ማድረግ ይጠበቃል።
- ተማሪዎች ታላላቆቻቸውን በመጠየቅ ስለወረዳቸው አጠቃላይ ታሪክ እንዲያውቁና እንዲያቀርቡ ማድረግ።

## 4. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስለ አራቱ አበይት አቅጣጫዎች የሚገልጽ አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ ከእንጨት በመስራት መጠቀም።
- የወረዳው ካርታ (ከለላ ማዘጋጀት)
- የወረዳውን ታሪካዊ ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ፣ ፖስተር፣ ስዕልና የመሳሰሉትን መጠቀም።

5. የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- የወረዳውን የመሬት አቀማመጥ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በማገናኘት እንዲናገሩ ማድረግና መገምገም።
- የትምህርት ቤታቸውም መገኛ ከሌሎች በአከባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ጋር በማገናኘት እንዲናገሩ በማድረግ መገምግም።
- ተራ በተራ እየተነሱ ያሉበትን አቅጣጫ ከሌሎች ተማሪዎች አንፃር እንዲገልፁ በማድረግ መገምገም።
- የወረዳቸውን ታሪካዊ ጠቃሚ ቦታዎችን መለየት እንዲናገሩ በማድረግ ያላቸውን ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

### የመልመጃ **4/1** መልስ

1. ሰሜን
2. ደቡብ
3. ምዕራብ

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት

ሀ እውነት /ሐሰት

5. እውነት

ለ. ባዶ ቦታ ሙላ

4.

ሐ. በአጭሩ መልሱ

1. ደቡብ፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ
2. አንድን ነገር (ወረዳን) ከሌላ ነገር (ወረዳ) ጋር በማነፃፀር አንፃራዊ መገኛውን መናገር እንችላለን።
3. ከብዙ ዓመታት በፊት አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተከናወኑባቸው ቦታዎች ሁሉ ታሪካዊ ስፍራ ይባላሉ። ለምሳሌ የቀደምት ሰዎች መኖሪያ የነበሩ ዋሻዎች፣ መሰብሰቢያ አዳራሾችና አደባባዮች፣ የጦር ሜዳዎች፣ ምሽጎችና የመሳሰሉት ናቸው።

### **4.2** የወረዳችን መሬት አቀማመጥ

የተመደበለት ጊዜ **10** ክፍለ ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- በወረዳቸው የሚገኙ የተለያዩ የመሬት አቀማመጥን ይለያሉ።
- የተለያዩ የመሬት አቀማመጥ ገጽታዎችን ይገልፃሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

5.2.1 የመሬት አቀማመጥ

5.2.2 የመሬት አቀማመጥ ገጽታዎች

**3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በመጀመሪያ ርዕሱን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። ከዚያም በኋላ በርዕሱ ስር የተጠቀሰውን የማነቃቂያ ጥያቄ እንዲመልሱ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች በወረዳቸው የሚገኙ የተለያዩ የመሬት አቀማመጦችን እንዲለዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።
- በተለያዩ የመሬት አቀማመጥ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ እንደተቀመጠው በደንብ ማስረዳት ያስፈልጋል። ከተረዱት የመሬት አቀማመጦች /ቅርፆች/ መካከል በይበልጥ የወረዳውን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ የሚገልፀው የቱ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች የተለያዩ ቦታዎችን በመጎብኘት የመሬት አቀማመጥ ቅርፆችን እንዲያዩ ማድረግ።
- በመቀጠልም የወረዳቸው የመሬት አቀማመጥ ገፅታዎች ምን ምን እንደሆኑ እንዲያውቋቸው ማስረዳት ያስፈልጋል። ይኸውም ደኖች፣ በውሃ የተያዙ መሬቶችና በውሃ የተሸረሸሩ ቦታዎች ማለት ይሆናል።
- ተማሪዎች በቡድን በመሆን በፕላስቲክ ጭቃ ወይም የሸክላ ጭቃ የወረዳቸውን ካርታ በመሥራት የመሬት አቀማመጡንም ጭምር እንዲያውቁ ማድረግ።

**4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- ተራራማ መሬትን የሚያሳይ ስዕል ወይም ካርታ። በተጨማሪ በአከባቢ የሚገኙ ተራራማ ቦታዎችን መጠቀም።
- ሸለቆማ ቦታዎችን የሚያሳይ ስዕል ወይም ካርታ። በአከባቢ የሚገኙ ሸለቆማ ቦታ ካለ ማስጎብኘት።
- ሜዳማ ቦታዎችን የሚያሳይ ስዕል ወይም ካርታ። በአከባቢ ካለ ማሳየት።
- የመሬት ተፈጥሮአዊ ገጽታን የሚያሳይ ስዕል ወይም ካርታ።

**5.** የመከታተያና የመገምገሚ ዘዴዎች

- የወረዳቸውን የመሬት አቀማመጥ እንዲናገሩና እንዲያሳዩ በማድረግ መገምገም።
- የወረዳቸውን የመሬት ገጽታ እንዲናገሩና እንዲያሳዩ በማድረግ መገምገም።

የመልመጃ **4/2** መልሶች

ሀ**.** እውነት/ሐሰት

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት

ለ. ባዶ ቦታ ሙሉ

1. ሜዳ
2. ፕላቶአማ
3. ተራራ
4. ሸለቆ

ሐ. በአጭሩ መልሱ

1. የተራቆተ መሬት
2. ወንዝ፣ ሀይቅ፣ ባህር፣ ውቅያኖስና የመሳሰሉት።

**4.3** በወረዳችን የሚገኙ መስሪያ ቤቶች

የተመደበለት ጊዜ **9** ክ/ጊዜ

**1.** ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን መመዝገብ ይችላሉ።
- በወረዳቸው የሚገኙ መሥሪያ ቤቶች ምን ምን እንደሚሰሩ ያውቃሉ።

**2.** ዝርዝር ይዘቶች

4.3.1 መስሪያ ቤቶች

4.3.2 የመስሪያ ቤቶቹ ተግባር

- በወረዳው ማን ምን ይሰራል።

**3.** የመማር ማስተማር ክንዋኔ

- ርዕሱን በማስተዋወቅ ከጀመሩ በኋላ በወረዳቸው ወይም ክፍለ ከተማቸው የሚገኙን መስሪያ ቤቶች ስማቸውን እንዲዘረዝሩ ተራ በተራ እድል በመስጠት መጠየቅ። ጥያቄውን በቃል ወይም በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመፃፍ መጠየቅ ይቻላል።

- በመቀጠልም መስሪያ ቤቶችን የምንላቸው ለወረዳው /ክፍለ ከተማው/ ያላቸውን ጠቀሜታ በመግለፅ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ። በተጨማሪም በወረዳዎች ውስጥ መስሪያ ቤቶችን የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ በማለት መግለፅ እንደሚችሉ ማስረዳት።
- በወረዳው ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ውጭ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግል ድርጅቶችና የእምነት ተቋማት እንደሚገኙ ማስረዳት። እነዚህ መስሪያ ቤቶች ያላቸውን ተግባራት እንዲያውቁ ማድረግ።
- ይህንን ተግባር ስናከናውን በወረዳ ማን ምን ይሰራል በሚል የማነቃቂያ ጥያቄዎች በመስጠት መጀመርና ማወያየት።
- የህዝብ ተወካዮች እንዴት እንደሚመረጡ በመጠየቅ የምረ3ጫ ሂደቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ። ተማሪዎች በቤታቸው ያላቸውን ተግባራት በቡድን በመከፋፈል ለክፍሉ ተማሪ እንዲያቀርቡ ማድረግ። ቤተሰቦቻቸውም በምን አይነት መሥሪያ ቤትና ምን ሥራ እንደሚሰሩ እንዲገልፁ መጠየቅ።
- በወረዳው የሚገኙትን መስሪያ ቤቶች ፖሊስ ጣቢያ፣ ፍርድ ቤት፣ የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግል ድርጅቶችና የእምነት ተቋማት ተግባር ምን እንደሆነ ማወያየትና መልሳቸውን ተራ በተራ መቀበል።

**4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የእምነት ተቋማትን የሚያሳይ ስዕል /መስጊድ፣ ቤተክርስቲያን/
- ለህዝብ ተወካዮች ህዝብ ድምፅ ሲሰጥ የሚያሳይ ፎቶግረፍ /ሥዕል/።
- የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ተግባራትን የሚያሳይ ቻርት።

**5.** የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ዋና ዋና በወረዳው የሚገኙ መስሪያ ቤቶችን እንዲዘረዝሩ በማድረግ መገምገም።
- በወረዳቸው የሚገኙ ዋና ዋና መስሪያ ቤቶችን ተግባር እንዲናገሩ በማድረግ መገምገም።

የመልመጃ **4/3** መልስ

ሀ. እውነት /ሐሰት

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት

ለ. ምርጫ

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. ለ
5. ሀ
6. ለ

ሐ. በአጭሩ ግለፁ

1. - ለህብረተሰቡ ሰብዓዊ እርዳታ መስጠት።
   - የልማት ሥራዎችን መስራትና የመሳሰሉት።
2. ሆቴል፣ ኢንዱስትሪ፣ ፋብሪካ፣ የሸቀጣሸቀጥ መደብሮችና የመሳሰሉት።
3. መስጊድ፣ ቤተክርስቲያንና የመሳሰሉት

## **4.4** የወረዳው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

የተመደበለት ጊዜ **17** ክፍለ ጊዜ

### **1.** ዝርዝር ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦

- የወረዳቸውን ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይዘረዝራሉ።
- ለቴክኒዮሎጂ ውጤቶችንና ጠቃሚ ተግባራትን ምሣሌ ይሰጣሉ።
- ሥራ ለወረዳው በምን በምን መልክ ለእድገት እንደሚጠቅም ያስረዳሉ።
- በዕድሜያቸው መጠን ስራ ለመሥራት ፍላጎት ያሣያሉ።

### **2.** ዝርዝር ይዘቶች

4.4.1 የወረዳ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

4.4.2 የቴክኒዮሎጂ ውጤቶችና ጠቃሚ ተግባራት

4.4.3 ለወረዳው እድገት መሥራት

4.4.4 ለሁሉም ሥራ አድናቆት መስጠት አስፈላጊነቱን ማወቅ

### **3.** የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ንዑሱን በማስረዋወቅ መጀመርና ከዚያም በኋላ ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የወረዳቸውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በመጠየቅና በማዘጋጀት ለተቀሩት የክፍል ተማሪዎች በቃላቸው እንዲቀርቡ ማድረግ።
- ተማሪዎች የሚያቀርቡትን የወረዳቸውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከሰማችሁ በኋላ የወረዳውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በቡድን መከፋፈል። ይኸውም ግብርና፣ ንግድ፣ መጓጓዣ፣ ኢንዱስትሪና የእጅ ሥራ በማለት ይሆናል።
- ተማሪዎች የተለያዩ የስራ መስኮች እንዳሉ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ ያስፈልጋል።

- በሀገራችን የሚገኙ እንዲሁም በአከባቢያቸው አብዛኛው ሰው የት እንደሚኖር በማወያየት በገጠር መሆኑን በማስረዳት የኢኮኖሚ ምንጭም ግብርና እንደሆነ ማስረዳት።
- በአከባቢቸው በብዛት ስለሚመረቱ የግብርና ምርቶች መጠየቅ። ይህንንም የእርሻ ምርቶች የሰብል በማለት መወሰን ያስፈልጋል። በመቀጠልም የሚመረተው ሰብል አይነት ከቦታ ቦታ እንደሚለያይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል።
- በአከባቢያቸው ገበሬው ከሚያመርተው ምርት ለምግብነት ከሚውሉት ውጪ ምን እንደሚያመርት በመጠየቅ ማወያየትና መልሱን ለክፍላቸው ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ።
- የእርሻ ምርቶች ከምግብነት አልፈው ተርፈው ለፋብሪካ /ኢንዱስትሪ ውስጥ እንደምንጠቀማቸው መግለፅ። ምሳሌ ጥጥ፣ የሸንኮራ አገዳና ቆዳና ሌጦ።
- ብዙ ፋብሪካዎች ቢኖሩ ቢከፈቱ ለገበሬው ያለውን ጥቅም እንዲወያዩ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ንግድ የሚለውን ንዑስ ርዕስ ስንጀምር ቀድመን የማነቃቂያ ጥያቄዎችን ተራ በተራ እንዲመልሱ ማድረግ። ይህንን ስናደርግ ጥያቄውን በቃል ወይም በሰሌዳ ላይ በማቅረብ ይሆናል።
- ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚያውቋቸውን የንግድ ዘርፎች እንዲዘረዝሩና እንዲመዘግቡ ማድረግና በአካባቢቸው በአብዛኛው ሰው ተሰማርቶ የሚኖረው በየትኛው የንግድ ሥራ እንደሆነ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት በቡድን እንዲያደርጉ ማድረግ።
- የመጓጓዣ አይነቶችን ከጥንት ጀምሮ ያሉትን እንዲዘረዝሩ ማድረግና ሰዎች ከገጠር ወደ ከተማ በአካቢያቸው በምን እንደሚጠቀሙ መጠየቅ።
- ለመጓጓዣ የምንጠቀምባቸውን የጋማ እንስሳት ስም እንዲዘረዝሩ ማድረግ።
- ዘመናዊ የሚባሉትን የመጓጓዣ አይነቶችን እንዲጠሩ ማድረግ።
- በአከባቢያቸው የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ካለ እንዲናገሩ ማድረግ መጀመር።
- የተለያዩ ፋብሪካዎችን በምሳሌነት በማንሳት ተግባራቸውንና ጥሬ እቃዎችን ከየት እንደሚያገኙ ማስረዳት።
- በክልላችን የሚገኙትን የኢንዱስትሪ/ የፋብሪካዎችን መገኛ ከተሞችንና የሚሰሩትን ሥራ እንዲሁም ጥሬ እቃዎቹ ምን እንደሆኑ ማስረዳት።
- በአከባቢያቸው የሚገኙ የእጅ ሥራ ውጤቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ ይህም ሲባል እንደ ጋቢ፣ የጥበብ ልብሶችና የመሳሰሉትን ያካትታል።
- በቤታቸው ውስጥ የሚጠቀሙበትን ቁሳቁሶች /ወንበር፣ ኩርሲና ጠረጴዛ/ ማን እንደሰራው በመጠየቅ የእጅ ሥራ ውጤት እንደሆነ እንዲያውቁት ማድረግ።
- በስዕል 4/19 የተገለጹትን የእጅ ስራ ውጤቶች ከምን እንደተሰሩ እንዲዘረዝሩ ማድረግ።

- ክር በመጠላለፍና በተለያዩ መንገዶች የእጅ ሥራ ውጤቶችን እንደሚሰሩ በመንገር ለተግባራቸውም እገዛ ማድረግ።
- በወረዳቸው የሚገኙትን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ መልሳቸውን ተራ በተራ መቀበል ያስፈልጋል።
- በወረዳቸው በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንደሚገኙ ምሳሌ በመስጠት ማስረዳት ያስፈልጋል።
- በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ በስዕል 4/21 የተጠቀሱትን እያንዳንዱን የቴክኖሎጂ ውጤት ለምን ለምን እንደሚጠቅሙ ተራ በተራ በመጠየቅ እንዲመልሱ ማበረታታት።
- ተማሪዎች በወረዳቸው አንዳንድ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅም ምን እንደሆነ ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይኸውም የሚያጠቃልለው ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ምድጃ፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ /ጀኔሬተር/ ካውያ /የኤሌክትሪክ/ ስልክ /ተንቀሳቃሽ ስልክ/ ይሆናል።
- ተማሪዎች የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ከአሮጌ ጋዜጣና መጽሔት በመሰብሰብ ለኤግዚቢሽን እንዲያዘጋጁ መርዳት።
- ተማሪዎች በስልክ ጠቀሜታ ላይ የተመሰረተ ድራማ በመሥራት እንዲያሳዩ ማድረግ።
- ተማሪዎች ማንኛውም የወረዳ ነዋሪ ለእድገት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ወይም ሥራ ጠቃሚና ሊበረታታ እንደሚገባ እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸውም ሐኪም ጤና እንዲኖር እንደሚያደርግ ሁሉ የመንገድ ጠራጊውም በሥራው የበሽታ አምጪ ህዋሳት እንዳይኖሩ በማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ ጠራጊውና ሐኪሙ ለወረዳቸው እኩል ተግባራትን አከናውነዋል ማለት ነው።
- ተማሪዎች የወረዳው ሠራተኞች ሁሉ ሥራ ቢያቆሙ ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን በማንሳት እንዲወያዩበት ማድረግ ይህም የሚያጠቃልለው ፖሊስ፣ የጤና ሠራተኞችና መምህራን።
- ከላይ ስለተጠቀሱት ስራዎች ጥቅም ማወያየትና ለእያንዳንዱ የወረዳ ነዋሪ ቤተሰቦች የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲያውቁ ማድረግ።

**4.** የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የቆዳ ውጤቶችን የሚሳይ ስዕል፣
- የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን የሚያሳይ ስዕል፣
- የኢንዱስትሪ ውጤቶችን የሚያሳይ ስዕል፣

**5.** የመከታተያና የመገምገሚያ ዘዴዎች

- ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን እንዲገልፁ ማድረግ መገምገም።
- ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ተግባራቸውን /ጠቀሜታቸውን በመጠየቅ መገምገም።
- ጠቃሚ ስለሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ምሳሌ በመስጠት ጥቅማቸውን መዘርዘር መቻላቸውን መገምገም።
- የስራ ጥቅምና ክቡርነት ማወቃቸውን መከታተልና መገምገም።
- ሥራ ለመስራት ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን መገምገም።

የመልመጃ **4.4** መልሶች

ሀ. እውነት /ሐሰት

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት

ለ. ምርጫ

1. ሐ
2. መ
3. መ
4. መ
5. መ

ሐ. በአጭሩ መልስ ስጡ

1. በቅሎ፣ ፈረስ፣ አህያ፣ ግመልና የመሳሰሉት
2. አርብቶ-አደር
3. ገበሩ
4. ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ
5. ጋቢ፣ የጥበብ ቀሚስ፣ ኩርሲ፣ ወንበር፣ ዱካና የመሳሰሉት ናቸው።